# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 236 ሚያዝያ 26 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






ፎቶ ፡- አዩብ ተፈሪ

ዶክተር ታምራት ሃይሌ

## በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት በተዘጋጀው «የለውጥ ጎዳና» መጽሐፍ ላይ ውይይት ተካሄደ

ሞገስ ተስፋ

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በለውጡ ሂደት የነበሩ ዐበይት ሁነቶችን ሰንዶ የያዘው "የለውጥ ጎዳና" የተሰኘ መጽሐፍ ለታሪክ ተመራማሪዎች ብቻ ሳይሆን ሁነቶችን ለማወቅና ለማንበብ ለሚፈልገው ትውልድ አስፈላጊ መሆኑን ምሑራን ተገለጹ። በትናትናው ዕለት በአብርኆት ቤተ መጻሕፍት "የለውጥ ጎዳና" በተሰኘ መጽሐፍ ላይ ውይይት ተካሄዷል።

በለውጡ ሂደት የነበሩ ዐበይት ሁነቶችን ሰንዶ የያዘው እና በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የተዘጋጀው "የለውጥ ጎዳና" የተሰኘ መጽሐፍ ላይ ውይይት በተካሄደበት ወቅት ስለመጽሐፉ

በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የአርበኞችን የድል ተምሳሌትነትና አንድነት
### በልማት ሥራዎች መድገም ይገባል

በዳግማዊት ግርማና ልጅዓለም ፍቅሬ

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የአርበኞችን የድል ተምሳሌትነት አንድነትን በማጽናትና በልማት ሥራዎች ላይ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ መድገም ይገባል ሲሉ የጥንታዊ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ፕሬዚዳንት ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን ተናገሩ።

ጀግኖች አርበኞች ፋሽስት ጣልያንን ያሸነፉበት የድል በዓል ሚያዝያ 27 ቀን 2015 ዓ.ም የበዓሉን ክብር በሚመጥን መልኩ በአራት ኪሎ የድል ሐውልት እንደሚከበር ተገልጿል።

ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ትውልዱ የአርበኞችን የድል ታሪክ በኢኮኖሚው፣በትምህርት፣ በሥራና በሌሎች ዘርፎች ውጤት በማስመዝገብ እንዲሁም የሀገርን አንድነትና ሉዓላዊነት በማስጠበቅ ሊደግመው ይገባል።

የአርበኞችን ጀብድ በአዲሱ ትውልድ መድገም

የአርበኞችን የድል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን









በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

## በታንዛኒያ
ሲካሄድ የቆየው የሰላም ውይይት የመጀመሪያ ምዕራፍ ተጠናቀቀ

ገጽ 4

## በኢትዮጵያ ታምርት
ንቅናቄ በከተማዋ 677 አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርጓል

- ሁለተኛው ዙር የአምራች ኢንዱስትሪዎች ንቅናቄ ማስጀመሪያ መድረክ ዛሬ ይካሄዳል

ገጽ 4




# ድርቅን በዘላቂነት ለመከላከል የተጠናከረ ሥራ ያስፈልጋል

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡ በሀገሪቱ በተደጋጋሚ የሚከሰተውን ድርቅ በዘላቂነት ለመቋቋምና ለመከላከል የተጠናከረ ሥራ እንደሚያስፈልግ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር አስታወቀ።

ሚኒስቴሩ በቆላማ፣ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ላይ የሚከሰት ድርቅን በዘላቂነት መቋቋምና መከላከልን የተመለከተ ውይይት ከባለድርሻ አካላት ጋር አካሂዷል።

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር እንድሪያስ ጌታ እንደገለጹት፤ ሀገሪቱ ሰፊ ለም መሬት ፣የውሀ ፣የማዕድንና የእንስሳት ሀብት ቢኖራም ባለፉት ዓመታት በቆላማ አካባቢ የሚኖሩ ማኅበረሰቦች በተደጋጋሚ በድርቅ ሲጠቁ ተስተውሏል።

በርካታ ዜጎች በድርቁ የተነሳ ለምግብ እጦት ተጋልጠዋል፤ በተጨማሪ የእንስሳት ምርት ቀንሷል። ችግር በዘላቂነት ለመፍታትና የአርብቶ አደሩን ኑሮ በማሻሻል ረገድ ጠንካራ ሥራ ያስፈልጋል ብለዋል።

በተለይም በሶማሌ ክልል ፣አፋር ክልል፣ ምዕራባዊ እና ምሥራቃዊ ኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች እንዲሁም በደቡብ ክልል ከፍተኛ የድርቅ ችግር ያጋጥማል ያሉት ዶክተር እንድሪያስ፤ ችግሩን ለመቆጣጠር በዕቅድ ላይ የተመሠረተ የዝግጅት ሥራ ማከናወን ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

በዘላቂነት የልማት ሥራዎች በማቀድ የአየር ንብረት ለውጥ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ማጠናቀር ይገባል። የተለያዩ የመስኖ አማራጮች በስፋት በመጠቀም፣ እርከንን በስፋት በመሥራት እንዲሁም የውሀ ማቆርና ግድብ ሥራዎች በማከናወን በየአካባቢው የውሀ ሀብት በአግባቡ መጠቀም እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

በተያዘው ዓመትም ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ለድርቅ አደጋ አስቸኳይ ምላሽና ለዘላቂ ልማት የሚውል ከ600 መቶ ሚሊዮን ብር በላይ በመመደብ ድርቅ በተከሰተባቸው አካባቢዎች የውሀ ልማት፣ የመስኖ የመኖ ልማት ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን አስታውቀዋል።

ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ ለድርቅ አደጋ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎችን የውሀ ሀብትን ማሳደግና መስኖን በስፋት በመጠቀም የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል ብለዋል።

በተጨማሪ የእንስሳት መኖ ምርት የማሳደግና ዘላቂ የኑሮ ማሻሻያዎችን የማከናወን ጥረቶች መጠናከራቸውን ገልጸዋል።

በውይይቱ ላይ በግብርና ሚኒስቴር ተወካይ የድርቅ ማቋቋምና ዘላቂ የኅብረተሰብ ማሻሻያ ብሔራዊ አስተባባሪ አቶ ጀማል አሊ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ በስፋት በምሥራቅ አፍሪካ አካባቢዎች ላይ በተደጋጋሚ የሚከሰተውን ድርቅ ለመከላከል ተቋማት የተቀናጀ አሠራር ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው።

በሀገሪቱ በተደጋጋሚ በሚከሰተው ድርቅ በአካባቢው የሚገኙ አርብቶ አደሮች ከፍተኛ ለሆነ ድርቅ እና የእንስሳት ሞት ተጋልጠዋል። ድርቅ ከሚከሰትባቸው ምክንያች አንዱ የዝናብ እጥረት ቢሆንም ከዛ ባለፈ በየአካባቢው የሚገኘው የውሀ ሀብት አጠቃቀም ላይ በስፋት መሥራት አለበት ብለዋል።

ለአርብቶ አደሩም ማኅበረሰብ በአካባቢው ያሉ መሬቶችና የውሀ ሀብቶች አጠቃቀም ላይ የተሻለ ውጤት ማምጣት የሚያስችል ግንዛቤ መፍጠር ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

# በሀገራዊ ምክክሩ የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ማሳደግ ይገባል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ሂደት የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ተገለጸ።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ምክር ቤት፣ የሰላም ሚኒስቴር እንዲሁም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በጋራ «በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ ማሳደግ» በሚል መሪ ሀሳብ ውይይት አካሂደዋል።

የሰላም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታዬ ደንደዓ በውይይቱ መክፈቻ ላይ እንደገለጹት፤ ሀገራዊ ምክክሩ ውጤታማ እንዲሆንና ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ማሳደግ ተገቢ ነው።

ከሀገራዊ ምክክሩ ዐቢይ ዓላማዎች መካከል አንዱ አሳታፊነት ነው ያሉት አቶ ታዬ፤ ምክክሩ አካል ጉዳተኞችን ያካተተ በማድረግ ሂደቱን የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን ያግዛል ብለዋል።

እንደ አቶ ታዬ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ካለችበት ሁኔታ አንጻር የሀገራዊ ምክክሩ ለሰላም ግንባታ ወሳኝ ነው። የአካል ጉዳተኞች በሀገራዊ ጉዳይ ላይ መሳተፍ ብቻ ሳይሆን ለሀገራቸው ጠቃሚ ሀሳብ እንዲያበረክቱ ማመቻቸት ያስፈልጋል።

አካል ጉዳተኝነት አለመቻል እንዳልሆነ ሁሉም ማኅበረሰብ ተገንዝቦ በኢትዮጵያ የሚገኙ ከ21 ሚሊዮን በላይ አካል ጉዳተኛ ዜጎች ወደ በሀገራዊ አጀንዳዎች ላይ ያላቸውን ተሳትፎ እንዲያሳድጉ መሥራት ይገባል ብለዋል።


አቶ ታዬ ደንደዓ


አቶ ሔኖክ መለሰ

ሚኒስትር ዴኤታው እንደተናገሩት፣ በሃይማኖት ተቋማት፣በትምህርት ቤቶች፣ በንግድ ተቋማትና በተለያዩ ተቋማት የአካል ጉዳተኞችን አስተዋፅዖ ማስፋት ይገባል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ምክር ቤት ዋና ዳይሬክተር አቶ ሔኖክ መለሰ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍሎች አሳታፊ ካላደረገ ውጤታማ ሊሆን ስለማይችል የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ከወዲሁ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

እንደ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በሀገሪቱ በሚኖሩ የሰላም ግንባታ እንቅስቃሴዎች ላይ አሳታፊ ሁነቶች እንዲከናወኑ የበኩላችንን ጥረት እናደርጋለን ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ አካል ጉዳተኞች ጠቃሚ የሆኑ መፍትሔ የማምጣት አቅማቸውን በሀገራዊ ምክክሩ ላይ ተግባራዊ እንዲያደርጉ አስፈላጊው እገዛ ይደረጋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ራሄል ባፌ (ዶክተር) በበኩላቸው፤ አካል ጉዳተኞች በሀገራዊ ምክክሩ እንዲሳተፉ መደረጉ ለማበረታታት ወይም ለመርዳት ሳይሆን በሀገራቸው ጉዳይ የራሳቸው ድርሻ እንዲወጡ ለማስቻል ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የፖለቲካ ፓርቲዎችና መንግሥት የአካል ጉዳተኞችን አደረጃጀቶች አዋቅረው ሲሠሩ እንደነበር አስታውሰው፤ በቀጣይም በሀገራዊ ምክክሩ የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ለማረጋገጥ ጥረት ማድረግ እንደሚገባቸው ጠቁመዋል።

በውይይት መድረኩ በሀገራዊ ምክክሩ የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ ማሳደግ በሚል ርዕስ በቀረበ የመነሻ ጽሑፍ በኢትዮጵያ ከ21 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የአካል ጉዳተኛ በመሆናቸው ሀገራዊ ምክክሩ ያለ አካል ጉዳተኞች ሙሉ ሊሆን እንደማይችል ተመላክቷል።


አቶ ክርስቲያን ታደሰ


መሠረት ዳምጤ


ዶክተር ሊያ ታደሰ

# ጤና ሚኒስቴር በፈንድ አጠቃቀም ፍትሐዊነት ላይ አተኩሮ እንዲሠራ ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የጤና ሚኒስቴር የኤች.አይ.ቪ ኤድስ ፈንድ ስርጭት እና አጠቃቀም ፍትሐዊነት ላይ ትኩረት ሰጥቶ ሊሠራ ይገባል ሲል የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰቧል።

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በትናንትናው ዕለት የፌዴራል ኤች.አይ.ቪ ኤድስ መቆጣጠሪያ እና መከላከል ጽሕፈት ቤት ፈንድ አጠቃቀም እና አፈጻጸም በተመለከተ የ2013/14 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ላይ ውይይት አድርጓል።

የክዋኔ ኦዲቱን አስመልክቶ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ክርስቲያን ታደለ እንደገለጹት፤ ጽሕፈት ቤቱ ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተሰበሰበው ፈንድ ሥራ ላይ መዋሉን ባግባቡ እያረጋገጠ ባለመሆኑ በየክልሎች ያልተወራረዱ ሂሳቦች መኖራቸው በኦዲት ሪፖርቱ ተመላክቷል። በዚህም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የፈንድ ስርጭት እና አጠቃቀም ፍትሐዊነት እና ተደራሽነት ላይ ትኩረት አድርጎ ሊሠራ ይገባል።

በኦዲት ሪፖርቱ ጽሕፈት ቤቱ በክልሎች ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተሰበሰበው ፈንድ ውጤታማ በሆነ መልኩ መጠቀም እንዲቻል ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑን ያሳያል ያሉት አቶ ክርስቲያን፤ የፈንድ አሰባሰብ ስትራቴጂ ተግባራዊ ሆኖ ሥራ ላይ ሊውል ይገባል ሲሉም አሳስበዋል።

የፌዴራል ዋና ኦዲት መሥሪያ ቤት ዋና ኦዲተር መሠረት ዳምጤ በበኩላቸው፤ የኤች አይ ቪ ኤድስ መቆጣጠሪያ እና መከላከል ጽሕፈት ቤት ወደ ጤና ሚኒስቴር ከመጣ በኋላ በክዋኔ ኦዲት የተገኙትን ግኝቶች መነሻ አድርጎ የሚሠራ ከሆነ ያሉትን ችግሮች ሊቀርፍ ይችላል።

በውይይቱ ላይ ማብራሪያና ምላሽ የሰጡት የጤና ሚኒስትሯ ዶክተር ሊያ ታደሰ፤ ሥልጠናዎችን፣ የአሠራር ሥርዓቶችን ለማጠናከር እና ለማኅበረሰቡ ግንዛቤ ለመስጠት ወደ ክልል የሚወርዱ ፈንዶች አሉ። ፈንዶቹ ከበሽታው ስርጭት እና ከክልሎች ሕዝብ ብዛት አንጻር ተሰልተው ነው የሚወርዱት። ነገር ግን በሚፈለገው ልክ ሥራዎች ተሠርተው ገንዘቡን የማወራረድ ሥራ በየጊዜው ክልሎች ላይ ያለው አቅም እየተሻሻለ ቢመጣም ብዙ ክፍቶች አሉበት። ክፍተቶቹም ተጠያቂነት እንዲኖራቸው ለማድረግ የጤና ሚኒስቴር የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል።

ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ የኤች አይ ቪ መቆጣጠር እና መከላከል የተለያዩ ፈንዶችን በመሰብሰብ ነው ሃገራዊ ፕሮግራሙን ተግባራዊ የሚያደርገው ያሉት ዶክተር ሊያ፤ የኤች አይ ቪ መቆጣጠር እና መከላከል ብሔራዊ ስትራቴጂ ከ2010ዓ.ም ጀምሮ ተቀርጾ እየተሠራበት እንደሚገኝ አስታውሰው፤ ይህ ብሔራዊ ስትራቴጂም በፌዴራል ብቻ ሳይሆን በክልሎች የምንሠራበት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው የኤች አይ ቪ ኤድስ መቆጣጠሪያ እና መከላከል ጽሕፈት ቤት ወደ ጤና ሚኒስቴር በአዲስ አደረጃጀት ከመቀላቀሉ በፊት ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ የተገኙትንም የኦዲት ግኝቶች አሁን ባለው አዲስ አደረጃጀት የሚፈቱ ይሆናል ብለዋል።

ቋሚ ኮሚቴው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የኦዲት ማሻሻያ መርሐ ግብሩን በአስር ቀናት ውስጥ እንዲልክ አቅጣጫ አስቀምጧል።

ዜና



# «የኢትዮጵያ የተሳካ ሰላም ስምምነት ሂደት ለሱዳን ትምህርት የሚሰጥ ነው»

- በፓኪስታን የኢፌዲሪ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ጀማል በከር

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡-በሰሜን ኢትዮጵያ ተከስቶ የነበረው ጦርነት ለመቋጨት የተደረሰው የሰላም ስምምነት ሂደት ለሱዳን ትምህርት የሚሰጥ ነው ሲሉ በፓኪስታን የኢፌዲሪ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ጀማል በከር አስታወቁ፡፡

በኢስላማባድ የኢትዮጵያ ኤምባሲ በፓኪስታን የሱዳን ልዩ መልዕክተኛ መቀመጫቸውን በኢስላማባድ ላደረጉ የምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) አባል ሀገራት አምባሳደሮች በሱዳን ስላለው ወቅታዊ ሁኔታ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

በፓኪስታን የኢፌዲሪ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ጀማል በከር በወቅቱ እንደተናገሩት፤ ሱዳን ከኢትዮጵያ ውጤታማ የሰላም ስምምነት ሂደት ትምህርት በመውሰድ ሶስተኛ ሳምንቱን ግጭቷን ማስቆም ትችላለች፡፡ ግጭቶችን ለመፍታትና በቀጣናው ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ውይይት ብቸኛው አማራጭ ነው ፡፡

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የኢትዮጵያን የሰላም ሂደት አስመልክቶ አስተዋፅዖ ላበረከቱ አካላት ሽልማት በሰጡበት ወቅት በሱዳን የሚገኙ ተፋላሚ ወገኖች ከኢትዮጵያ የሰላም ሂደት ትምህርት እንዲወስዱና ግጭት እንዲያቆሙና መግለጻቸውን አምባሳደር ጀማል አስታውሰዋል፡፡

ኢትዮጵያ አሁን ሱዳን የገጠማት ተመሳሳይ ችግር ገጥሟት እንደነበር አምባሳደር ጀማል መናገራቸውን የጠቆመው መግለጫው፤ ኢትዮጵያ እንዳደረገችው ሁሉ በሱዳን ዘላቂ ሰላም ለማምጣት የሁሉም ባለድርሻ አካላት ብቸኛው አማራጭ ሰላማዊ ድርድር ነው ሲሉ ማስረዳታቸውን ኤምባሲው አስታውቋል፡፡

ኢትዮጵያ በሰሜኑ ጦርነት አፍሪካ በተለይም ኢትዮጵያ ምን ያህል ዋጋ እንደከፈለች በታሪክ መዝገብ ላይ የሰፈረ ጉዳይ መሆኑን የገለጹት አምባሳደሩ፤ ከግጭቱ እንድንወጣ ያገዘን የሕዝባችን ቁርጠኝነት እና የመላው አፍሪካ እንዲሁም የሌሎች ዓለም አቀፍ አጋሮች ድጋፍ ነው ማለታቸውን በመግለጫው ተመላክቷል፡፡

በተመሳሳይ ሱዳን በሀገሯ ያለውን ግጭት በውይይት መቋጨት ይኖርባታል ያሉት አምባሳደሩ፤ የሱዳን ሰላም ለመላው አፍሪካ ሰላም አስፈላጊ በመሆኑ ኢትዮጵያም ሱዳን ችግሮቿን በሰላማዊ መንገድ እንድትፈታ ለመርዳት ፍላጎት አላት ሲሉ መናገራቸውን ኤምባሲው በመግለጫው ጠቁሟል፡፡

ኢትዮጵያ በሱዳን ግጭት ምክንያት ችግር ላይ ያሉ ዜጎችን ከሀገሪቷ በማስወጣት ሂደት ብቻ ሳይሆን ለሱዳን ሕዝብ የሰብዓዊ ድጋፎችን በማቅረብ እያገዘች መሆኗን ማስታወቃቸውን በመግለጫው ሰፍሯል፡፡

ማንኛውም አካል ከጦርነትና ግጭት ተጠቃሚ መሆን አይችልም፡፡ ጦርነት ትርፉ ሞት፣ ረሃብ፣ ድህነትና ሥራ አጥነት መሆኑን የጠቆሙት አምባሳደሩ፤ ኢትዮጵያም በሰሜኑ ጦርነት ለመፍታት የሄደችበትን ውጤታማ የሰላም ስምምነት ለሌሎችም ትምህርት የሚሰጥ ማለታቸውን ኤምባሲው አስታውቋል፡፡

እንደ መግለጫው ከሆነ፤ በኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍል ሰላም ለማምጣት የተጀመረውን የሰላም ሂደት በተሳካ ሁኔታ መፈጸሙን አምባሳደር ጀማል ገልጸዋል፤ ጦርነቱ ዜጎችን ለሞት፣ ለረሃብ፣ ለድህነት እና ለሥራ አጥነት ዳረገ እንጂ ማንም ሰው ከዚህ ትርፍ አያገኝም ሲሉ ተናግረዋል፡፡

አምባሳደል ጀማል የአፍሪካ ኅብረት በኢትዮጵያ መንግሥት እና በሕወሓት መካከል የሰላም ስምምነት ተፈጻሚ እንዲሆን ያበረከተውን ሚና ማድነቃቸውን በመግለጫው ተመላክቷል፡፡

ኢትዮጵያ፣ ሱዳን፣ ጂቡቲ፣ ኬንያ፣ ሶማሊያ፣ ደቡብ ሱዳን እና ዩጋንዳ በምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) በአባልነት ተሳትፎ እያደረጉ የሚገኙ ሀገራት ናቸው፡፡

# መንግሥት ለመልሶ ማቋቋም ሥራዎች ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው



አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ሰላምን ለማፅናትና እና የመልሶ ማቋቋም ሥራዎችን መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ተናገሩ፡፡

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከአፍሪካ ልማት ኤጀንሲ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ናርዶስ በቀለ ጋር ትናንት ተወያይተዋል፡፡

አቶ ደመቀ መኮንን በኔፓድ የልማት መርሐ ግብሮች አተገባበር እና የሀገራት ሚና ላይ ያተኮረው ውይይት ላይ እንደገለፁት የኔፓድ የልማት መርሐግብሮች በአፍሪካ ድህነትን ለመቀነስ እየተደረገ ላለው ጥረት ጉልህ እገዛ አለው፡፡

ለልማት መርሐ ግብሮቹ ተፈፃሚነት ኢትዮጵያ የምታደርገውን ድጋፍ አጠናክራ እንደምትቀጥልም አረጋግጠዋል፡፡

የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታን አስመልክቶም አቶ ደመቀ ለዋና ሥራ አስፈጻሚዋ ገለፃ ያደረጉ ሲሆን ሰላምን የማፅናት እና የመልሶ ማቋቋም ሥራዎችን መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን አብራርተዋል፡፡ ኔፓድ በአህጉሪቱ የሚያከናውናቸውን የልማት ተግባራት አጠናክሮ እንዲቀጥልም ጠይቀዋል፡፡

የአፍሪካ ልማት ኤጀንሲ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ናርዶስ በቀለ በበኩላቸው የኔፓድ መርሐ ግብሮች የአፍሪካ ኅብረት አጀንዳ 2063 በሚል ለያዛቸው የእድገት እቅዶች መሳካት ወሳኝ ድርሻ እንደሚኖረው ተናግረዋል፡፡

ኔፓድ የወጠናቸውን እቅዶች ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ያሉ የፋይናንስ ጉድለቶችን ለመሙላት የሃብት ማሰባሰብ ሥራ አስፈላጊ መሆኑን ዋና ሥራ አስፈፃሚዋ ገልፀዋል፡፡

ኔፓድ ከኢትዮጵያ ጋር ባለው የልማት ትብብር በግብርና፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም መሰል የልማት መስኮች በትብብር እንደሚሠሩ በውይይቱ ተገልጿል፡፡

# የሽብር ወንጀል ለመፈፀም ቦንብ ደብቀው ተይዘዋል በተባሉ ተጠርጣሪዎች ላይ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ተፈቀደ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ የሽብር ወንጀል ለመፈፀም በማሰብ 10 ቦንቦችን በቤት ውስጥ ደብቀው ተይዘዋል በተባሉ ተጠርጣሪዎች ላይ ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ የ12 ቀናት ጊዜ ፈቀደ ፡፡

ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለማፍረስ በኢ-መደበኛ አደረጃጀት ተደራጅተው በአዲስ አበባ ከተማ የሽብር ወንጀል ለመፈፀም በማሰብ ከአማራ ክልል 10 ቦንቦችን በማምጣት በየካ ክፍለ ከተማ በተከራዩበት መኖሪያ ቤት ውስጥ ቦንቦችን ደብቀው ተይዘዋል በተባሉ ተጠርጣሪዎች ላይ ነው ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግባቸው ለፖሊስ የ12 ቀን ጊዜ የተፈቀደው፡፡

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ጊዜ ቀጠሮ ችሎት ከትላንት በስቲያ ክርክር በተካሄደባቸው ሁለት የጊዜ ቀጠሮ መዝገቦች ተመልክቶ ትላንት ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግባቸው ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን መርማሪ በአዲስ አበባ ከተማ ሁከትና ብጥብጥ በማስነሳት፣ የሽብር ወንጀል ለመፈፀም በማሰብ በተከራዩበት መኖሪያ ቤት 10 ቦንቦችን ደብቀው የተያዙ ሞላልኝ ሲሳይ እና አብርሃም ጌትነት በተባሉ ተጠርጣሪዎች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የምርመራ ጊዜ ውስጥ የምስክሮችን ቃል መቀበሉ፤ እንዲሁም ከተጠረጠሩበት የወንጀል ድርጊት ጋር የተያያዙ በርካታ ማስረጃዎችን መሰብሰቡን የተጠርጣሪዎችንም ቃል መቀበሉን ለችሎቱ አስረድቶ ነበር ፡፡

በሁለተኛው መዝገብ ደግሞ ማለትም በአማራ ክልል አመፅ፣ ሁከትና ብጥብጥ በማስነሳት በሰውና በንብረት ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ፣ አንዱ ሕዝብ በአንዱ ሕዝብ ላይ መተማመን እንዳይኖረው ለመከፋፈል ሲሠሩ ነበሩ ተብለው የተጠረጠሩ ሰይፈ ተስፋዬ፣ ማስረሻ እንየው፣ ጌታቸው ወርቁ፣ አንደበት ተሻገር፣ ታደሰ ወዳይነው፣ በተባሉ አምስት ተጠርጣሪዎች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው ጊዜ ቀጠሮ የሠራውን የምርመራ ሥራ ለችሎቱ አቅርቧል፡፡

በዚህም የምስክሮችን ቃል መቀበሉን፣ ማስረጃዎችን መሰብሰቡን፣ በተጠርጣሪዎች እጅ የተገኘ ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ እንዲመረመር ለሚመለከተው አካል መላኩን፣ አጠቃላይ የተደረገ የገንዘብ ዝውውርን ለማጣራት ለባንኮች ማስረጃ እንዲላክለት መጠየቁን ገልጿል፡፡

መርማሪ ፖሊስ በሁለቱም መዝገቦች ቀሪ ሥራዎችን አከናውኖ የምርመራ ማጣሪያ አድርጎ ለመቅረብ ተጨማሪ የ14 ቀን ጊዜ እንዲሰጠው ጠይቆ ነበር፡፡

በሁለቱም መዝገብ የተሰየሙ የተጠርጣሪ ጠበቆችም ተጨማሪ ጊዜ ቀጠሮ መፈቀድ የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የተጠርጣሪዎች የዋስትና መብት እንዲፈቀድ ጊዜ ቀጠሮ ችሎቱን ጠይቀዋል፡፡

መርማሪ ፖሊስ የተጠርጣሪዎች የዋስትና ጥያቄን በመቃወም ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙን ክርክር ያዳመጠው ጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ የምርመራ መዝገቡን አስቀርቦ ከተመለከተ በኋላ ፖሊስ በርካታ የምርመራ ሥራ ማከናወኑንና ማስረጃዎችን መሰብሰቡን መመልከቱን በትላንትናው ቀጠሮ አብራርቷል፡፡

ፖሊስ ቀሪ ከሚሠራው የምርመራ ሥራ አኳያ ተጨማሪ ጊዜ እንደሚያስፈልገው መታመኑን በጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ ተገልጿል፡፡

በዚህም መሠረት የተጠርጣሪዎችን ዋስትና ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ሞላልኝ ሲሳይ እና አብርሃም ጌትነትን በሚመለከት ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ ፍርድ ቤቱ ለፖሊስ የ12 ቀን ጊዜ ፈቅዷል፡፡

ሁከትና ብጥብጥ በማስነሳት ወንጀል የተጠረጠሩት እነ ሰይፈ ተስፋዬ አምስት ሰዎች ያሉበት ጊዜ ቀጠሮ መዝገብን በሚመለከት ተጨማሪ ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል በማለት ፍርድ ቤቱ የ10 ቀናትን ተጨማሪ ጊዜን ለፖሊስ ፈቅዷል፡፡

በዚሁ መዝገብ ተካተው የነበሩ ታደለ መንግሥቱና (ዶ/ር) እና አሰፋ አዳነ የተባሉ ተጠርጣሪዎችን በሚመለከት ተጨማሪ ጊዜ መስጠት አስፈላጊ አይደለም ሲል ፍርድ ቤቱ እያንዳንዳቸው በ15 ሺህ ብር ዋስትና ከእስር እንዲፈቱ አዟል፡፡

በተመሳሳይ ዜናም መንግሥት በወሰደው ሕግ የማስከበር ሥራ በሽብር ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የዋሉ አምስት ግለሰቦች ላይ የ14 ቀን የምርመራ ጊዜ ለፖሊስ ፈቅዷል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ ጊዜ ቀጠሮ ችሎት መንግሥት በወሰደው ሕግ ማስከበር ሥራ በሽብር ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የዋሉ አምስት ግለሰቦችን የጥርጣሬ የመነሻ የጊዜ ቀጠሮ መዝገብን ተመልክቶ ነው የ14 ቀን የምርመራ ጊዜ የፈቀደው፡፡ ተጠርጣሪዎቹ መንበረ ዓለሙ ተከታይ፣ ሲሳይ መልካሙ አበበ፣ ዶ/ር ገብርዓብ ዓለሙ ዘሪሁን፣ ተስፋዬ መኩሪያው አበባው እና ወንዶሰን ተገኘ ተስፋዬ ይባላሉ፡፡

የፌደራል ፖሊስ መርማሪ ተጠርጣሪዎቹ በአመራሮች ላይ ጥቃት ለመፈፀም እና ግድያን ለማስቀጠል፣ ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለማፍረስ በማሰብ በኢ-መደበኛ አደረጃጀት በመፍጠር ሲንቀሳቀሱ እንደነበር ጠቅሶ ፤ከትናንት በስቲያ ከሰዓት በኋላ በነበረ ቀጠሮ ለችሎቱ አብራርቶ ነበር፡፡

በተለይም 1ኛና 2ኛ ጠርጣሪዎች በአማራ ክልል አመፅና ብጥብጥ እንዲነሳ በተለያዩ ዩኒቨርስቲና በሌሎች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለወንጀል ተግባር የሚሳተፉ ተማሪዎችን ሲያደራጁ እና ሲያሰለጥኑ ነበር በማለት መርማሪ ፖሊስ ለጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ አስረድቷል፡፡

በተጠረጠሩበት የሽብር ወንጀል ሲንቀሳቀሱ መንግሥት በወሰደው የሕግ ማስከበር ሥራ አራቱ ግለሰቦች በአማራ ክልል አንዱ ተጠርጣሪ ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ በቁጥጥር ስር መዋላቸው መርማሪ ፖሊስ ገልጿል፡፡

የተጀመረውን የምርመራ ሥራ አጠናክሮ ተጨማሪ ማስረጃ አካቶ ለመቅረብ የ14 ቀን የምርመራ ጊዜ እንዲሰጠው ፖሊስ ጠይቆ ነበር፡፡

ተጠርጣሪዎቹ በፖሊስ በተገለፀው የሽብር ተግባር ውስጥ ተሳትፎ የለንም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የዋስ መብታቸው እንዲከበር ፍርድ ቤቱን ጠይቀዋል፡፡ የተጠርጣሪዎችን የጊዜ ቀጠሮ መዝገብ በይደር የተመለከተው የጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ ተጨማሪ የምርመራ ማጣሪያ ያስፈልገዋል በማለት በትላንትናው እለት የ14 ቀን ጊዜ ለፖሊስ ፈቅዷል፡፡

# በታንዛኒያ ሲካሄድ የቆየው የሰላም ውይይት የመጀመሪያ ምዕራፍ ተጠናቀቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል ያለውን ግጭት በማስወገድ ሰላምን ለማምጣት ያለመው እና በታንዛኒያ ሲካሄድ የቆየው የሰላም ውይይት የመጀመሪያ ምዕራፍ ዛሬ መጠናቀቁን የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ትናንት ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ ውይይቱ በአብዛኛው በአዎንታዊ መልኩ የተከናወነ ቢሆንም በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ግን በመጀመሪያው የውይይት ምዕራፍ ስምምነት ላይ ለመድረስ አልተቻለም ብሏል።

ግጭቱን በዘላቂነትና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለማስቆም እንዲቻል ሁለቱም አካላት የሰላም ውይይቱን መቀጠል አስፈላጊ መሆኑ ላይ ተግባብተዋል ብሏል መግለጫው።

በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥትና እስካሁን ሲመራባቸው በነበሩ መሠረታዊ መርሆዎች መሠረት ግጭቱን በሰላማዊ መልኩ ለመፍታት መንግሥት የጸና አቋም እንዳለውም ነው የተገለጸው።

አገልግሎቱ በመግለጫው ይህንን መልካም አጋጣሚና በውይይት ችግሮችን የመፍታት በጎ ጅምር በመጠቀም፣ ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ የኢትዮጵያ መንግሥት ያለውን ጽኑ አቋም ዳግም ያረጋግጣል ብሏል።

የሰላም ውይይቱን ላመቻቹና ላስተናገዱ አካላትም የኢፌዴሪ መንግሥት ምስጋናውን ማቅረቡን ገልጿል።

# በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ በከተማዋ 677 አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርጓል

## - ሁለተኛው ዙር የአምራች ኢንዱስትሪዎች ንቅናቄ ማስጀመሪያ መድረክ ዛሬ ይካሄዳል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ ለአንድ ዓመት በተከናወነው የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ አዲስ 677 አነስተኛ-መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ እንዲገቡ መደረጉን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ አስታወቀ። በአዲስ አበባ ከተማ «ኢትዮጵያ ታምርት» የአንድ ዓመት ንቅናቄ ማጠቃለያና ሁለተኛው ዙር ንቅናቄ ማስጀመሪያ መድረክ በዛሬው ዕለት ይካሄዳል።

በቢሮ ኃላፊ ደረጃ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ኢዘዲን ሙስባህ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በከተማዋ ለአንድ ዓመት ሲካሄድ በቆየው የኢትዮጵያ ታምርት እንቅስቃሴ በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመለየት ደረጃ በደረጃ በመፍታት በኩል ውጤታማ ሥራ ተሠርቷል።

በዚህም አዲስ 677 አነስተኛ-መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርጓል ያሉት አቶ ኢዘዲን፤ በተለያዩ ምክንያቶች ሥራ አቁመው ከነበሩ 49 ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 43ቱን ወደ ሥራ ማስገባት ተችሏል ብለዋል።

በንቅናቄው በተደረገው ድጋፍና ክትትል 210 አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርታቸውን ወደ ውጭ መላክ መጀመራቸውን የጠቆሙት ኃላፊው፤ ተኪ ምርትን የሚያመርቱ አንድ ሺ 926 ኢንዱስትሪዎችን ማፍራት እንደተቻለም አመላክተዋል።

የማምረቻ ቦታ ችግር፣ ፋይናንስ እጥረት፣ የኃይል አቅርቦት፣ የገበያ ትስስር አለመኖርና የጥሬ እቃ አቅርቦት



አቶ ኢዘዲን ሙስባህ

ችግር እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ እጥረት በዘርፉ በማነቆነት የሚነሱ ችግሮች መሆናቸውን የጠቆሙት አቶ ኢዘዲን፤ ችግሮችን ደረጃ በደረጃ ለመፍታት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

ከቦታ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮችን ለመቅረፍም 7 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር በከተማ አስተዳደሩ ተመድቦ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ላይ 93 ሄክታር መሬት ላይ ሼድ ግንባታ እየተካሄደ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህም 800 ለሚደርሱ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን የቦታ እጥረት ይቀርፋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የአንድ ጊዜ መድረክ ኩነት ሆኖ የሚያልፍ ሳይሆን ለ10 ዓመታት የሚዘልቅ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ኢዘዲን፤ በዛሬው ዕለትም የመጀመሪያው ዙር ንቅናቄ ማጠቃለያና የሁለተኛው ዙር ንቅናቄ ማስጀመሪያ መርሐ ግብር ይከናወናል ነው ያሉት።

በተከታታይ ዓመታት በሚከናወኑ ሥራዎች አሁን ላይ እንደ አገር 30 በመቶ ብቻ የሚሸፍነውን የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪ ምርት ፍጆታ ወደ 60 በመቶ ለማሳደግ መታቀዱን አመልክተዋል።

በዛሬው ዕለት በሚካሄደው መድረክም ባለፈው ዓመት የተካሄደውን የንቅናቄ መድረክ ተከትሎ በአምራች ኢንዱስትሪዎች ዘንድ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን ለመፍታት የተሠሩ ሥራዎችን ምን ውጤት እንዳስገኙና በቀጣይነትስ ምን ላይ ትኩረት መደረግ አለበት የሚሉትን ጉዳዮች ለመለየትና ቀጣይ አቅጣጫዎችን ለማስቀመጥ ያስችላል ብለዋል።

በመርሐ ግብሩ የ86 አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርትና የቴክኖሎጂ ውጤት የሚያሳይ አውደ ርዕይ ለዕይታ እንደሚቀርብ ጠቅሰው፤ ይህም በኢንዱስትሪዎች መካከል ተሞክሮ ለመለዋወጥና የሥራ ትስስር ለመፍጠር እንደሚያግዝ ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ችግር በመቅረፍ ውጤት እንዲመዘገብ ያደረጉ ባለድርሻ አካላትና ተኪ ምርት በማምረትና ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ ተጨባጭ ውጤት ላስመዘገቡ ኢንዱስትሪዎች እውቅና እንደሚሰጥም አስታውቀው፤ ከዚህም በተጨማሪ 750 ባለድርሻ አካላትና ኢንዱስትሪያሊስቶች የሚሳተፉበት የምክክር መድረክ እንደሚካሄድም ገልጸዋል።

# የአርበኞችን የድል...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የሚቻለው በማንበብና በመመራመር የቅድመ አያቶቹን ታላቅ ተጋድሎ በመረዳት ወደፊት በማስቀጠልም ጭምር ነው ሲሉ ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል።

ጀግንነት በጦርነት ሜዳ ላይ ብቻ ሳይሆን በየሙያ ዓይነቱ የሚገለጥ መሆኑን የጠቆሙት ልጅ ዳንኤል፤ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የዚህ ዘመን የጀግንነት መገለጫ የሆነውን ጠንክሮ የመሥራት ባህልን በሕይወቱ ውስጥ የሁልጊዜ ተግባሩ ሊያደርግ እንደሚገባውም አመልክተዋል።

ኢትዮጵያውያን በብሔር፣ በዘር፣ በቋንቋና በሐይማኖት ሳይለያዩ በአንድነት ስሜት በመታገላቸው የኢትዮጵያን የግዛት ሉዓላዊነትና የሰንደቅ ዓላማውን ክብር አስጠብቀዋል ያሉት ፕሬዚዳንቱ ፤ አሁንም አንድነትን በማጠናከር የውስጥና የውጭ ችግሮችን መፍታት ይገባል ሲሉ አስረድተዋል።

በቀደመው ጊዜ ኢትዮጵያውያንን ለማጥፋትና ሀገሪቷን ለመቀራመት ፋሽሽት ጣሊያን ብዙ ጥረት ቢያደርግም አልተሳካለትም ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ አሁን ላይ በዓሉ የሚከበረው ወጣቱ ካለፈ ታሪኩ እንዲማርና አንድነቱን አስጠብቆ እንዲቀጥል ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ጀግኖች አርበኞች ፋሽስት ጣሊያንን ያሸነፉበት የሚያዚያ 27 የድል በዓል ክብሩን በሚመጥን መልኩ በአራት ኪሎ የድል ሐውልት ይከበራልም ብለዋል። አርበኞች ለአምስት ዓመት ሙሉ ስለ አንዲት ኢትዮጵያ ተጋድለው ጀብድ የሠሩበት የድል በዓልን በታላቅ ሥርዓት ለማክበር እንዲቻል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ዝግጅት መጠናቀቁን ጠቁመዋል።

በዓሉ የሀገርን ኅብረ-ብሔራዊ አንድነት የሚያጎለብትና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት የሚያጠናክር መሆኑን የገለጹት ልጅ ዳንኤል፤ የድል በዓሉ ከነሙሉ ክብሩ ለትውልድ እንዲተላለፍ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር በትኩረት እየሠራ መሆኑንም ተናግረዋል።

የበዓል አከባበሩ ሚያዚያ 27 ቀን 2015 ዓ.ም ከንጋቱ 12 ሰዓት ላይ 21 ጊዜ መድፍ በመተኮስ የሚጀመር ሲሆን፤ በበዓሉ የፌደራልና የክልል ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ ከ30 በላይ የውጭ ሀገር እንግዶች እንዲሁም የሀገር ውስጥ ተሳታፊዎች በተገኙበት እንደሚከበር አስታውቀዋል።

በዓሉ ከድል ታሪክነቱ በተጨማሪ ለአሁኑ ትውልድ በኢኮኖሚያዊ፣ በማኅበራዊ እንዲሁም በፖለቲካዊ ጉዳዮች በጽናትና በአብሮነት መቆም እንዳለበት በሚያሳስቡ መልዕክቶች እንደሚተላለፉበት ገልጸዋል። አዲሱ ትውልድ የኢትዮጵያ የድል በዓል በትክክል እንዲገነዘብ ማስተማርና በቦታው ተገኝቶ እንዲያከብር ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ ልጅ ዳንኤል ጆቴ ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብም የድል በዓሉን ሲያከብር ፍጹም ሰላማዊ በሆነ መንገድና የበዓሉን ታሪካዊ ዳራ በማይሸረሽር መልኩ መሆን እንዳለበት መልዕክት አስተላልፈዋል።

ፋሽስት ጣሊያን ዓድዋ ላይ የደረሰበትን ሽንፈት ለመበቀል ለ40 ዓመታት ዝግጅት በማድረግ በ1928 ዓ.ም በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ከፈጸመ በኋላ ለአምስት ዓመታት አርበኞች በዱር በገደሉ ተጋድለው ሚያዚያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ድል ማድረጋቸው የሚታወስ ነው።

# በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት በተዘጋጀው «የለውጥ ጎዳና» ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የታሪክ ባለሙያው ዶክተር ታምራት ሃይሌ በሰጡት ትንታኔ፤ መጽሐፉ ከየካቲት 6 ቀን 2010 እስከ ጳጉሜ 2011 ዓም ድረስ ባሉት የለውጥ ጊዜያት የተከናወኑ ሁለንተናዊ ሁነቶችን የያዘ ነው። መጽሐፉ ከአንድ ሺ 400 በላይ አገራዊና ቀጠናዊ ሁነቶችን በሁለት ምዕራፍ አካቶ፤ በየቀኑ የተከናወኑ ሁነቶችን ሰንዶ የያዘ መሆኑን አመልክተዋል።

የታሪክ ባለሙያው፤መጽሐፉ ከይዘት አንጻር ከ2010 ጀምሮ እስከ 2011 ባሉት ጊዜያት የተከናወኑ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ኹነቶችን እና ተግዳሮቶችንም ጭምር በማካተት ሰንዶ የያዘ ነው። የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ ከኢሕአዴግ ሊቀመንበርነትና ጠቅላይ ሚኒስትርነት በፈቃዳቸው ለመልቀቅ ያቀረቡትን ጥያቄን ጨምሮ ያሉትን ተከታታይ ሁነቶች የሰነደ ስለመሆኑ አብራርተዋል።

«የለውጡ ጎዳና» የተሰኘው መጽሐፍ በየቀኑ ያሉ ኹነቶችን በተከታታይ በመዘገብ የያዘ በመሆኑ ከዜና መዋዕል ይለያል ያሉት የታሪክ ባለሙያው፤ ዜና መዋዕል ብዙ ጊዜ የነገሥታትን ሥራ እንቅስቃሴ ብቻ የሚዘግብና የሚሰንድ ነው። ይህ መጽሐፍ ግን ሁሉን አቀፍ ሀገራዊና ቀጠናዊ ሁነቶችን በተገቢው መንገድ በጊዜ ቅደም ተከተል ያስቀመጠ ነው። ይህም ለታሪክ ጥናት ትልቅ ግብዓት ሆኖ የሚያገለግል ነው።

ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ የተሠሩ የማሻሻያ ሥራዎችንና ፈተናዎችን በተገቢው መንገድ የሰነደ ትልቅ ሃገራዊ መረጃ መሆኑን ያብራሩት ዶክተር ታምራት፤ በለውጡ ሂደት የፖለቲካ ምሕዳሩን መስፋትና የተደረጉ አገራዊ የማሻሻያ ሥራዎችንና ሌሎች ሁነቶችን የሚያሳይ ነው። በተጨማሪም ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካ እንደመገኘቷ መጠን የተካሄደው የለውጥ ሂደት ለአጥኚዎችና ተመራማሪዎች ትልቅ ግብዓት ሆኖ የሚያገለግል ነው ብለዋል።

የለውጡ ተዋናዮች የለውጥ ሂደቱና የተሠሩ የማሻሻያ ሥራዎችን መለስ ብሎ ለማየት ግብዓት ሆኖ ያገለግላል ያሉት የታሪክ ባለሙያው፤ በለውጥ ሂደት ውስጥ የተከሰቱ ሁነቶች እንዴት እንደታለፉ መለስ ብለው እንዲመለከቱ ዕድል የሚሰጥ ነው። ቀጣይም ለሚደረጉ የለውጥ ሥራዎች የሚያግዝ ነው። በኢትዮጵያ አሁናዊ ፖለቲካ ላይ ትንተና ለሚሰጡና ለሚሠሩ ባለሙያዎች ቀጥተኛ የሆነ ግብዓት ሆነው የሚያገለግሉ መረጃዎችን የያዘ በመሆኑ እንደ ማጣቀሻ ሆኖ ስለሚገለግል ፋይዳው ከፍተኛ ነው።

የሃገራዊ ምክር ኮሚሽን ሰብሳቢ ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ በበኩላቸው በየጊዜው የሚከናወኑ ሀገራዊ ሁነቶች ተሰንደው መቀመጣቸው ለተለያዩ ውሳኔዎች እንደ መነሻ ሆነው ያገለግላሉ። እንደ ሃገር ብቻ ሳይሆን እንደ ተቋም ሲታይ የሚጋጥመው ችግር ተቋሙን እነማን መቼ እንዳቋቋሙት የሚታወቅበት ሁኔታ አለመኖሩ ነው። በዚህም ምክንያት ግምት ይሰጣል። ይህም የታሪክ ክፍተት ይፈጥራል ብለዋል።

ታሪክ በሚገባ እየተሰነደ ካልተቀመጠ የሚቀጥለው ትውልድ ምን እንደተከናወነ ግንዛቤ የሚወስድበት ሁኔታ ስለማይኖር ግምቶች ሁልጊዜ ለተሳሳተ ድምዳሜ ይዳርጋሉ። ከዚህ አንጻር የለውጥ ጎዳና የተሰኘው በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የተዘጋጀው የአንድ ዓመት ከ6 ወር ሰነድ ለታሪክ ተመራማሪዎች ብቻ ሳይሆን ሁነቱን ማወቅና ማንበብ ለሚፈልግ ትውልድ አስፈላጊ ነው። ለተመራማሪዎች፣ ለዩኒቨርሲዎችና ለሌሎች አካላት ማን ምን ሥራ ብሎ ለማወቅ ትልቅ የመረጃና የማጣቀሻ ሆኖ እንደሚያገለግል ገልጸዋል።

በለውጡ ጎዳና የተሰኘው የመጽሐፍ ከ570 ቀናት በላይ የተከናወኑ በሁለት ክፍሎች የተዘጋጁ ሁነቶችን በዝርዝር የያዘ ነው። መጽሐፉ 525 ገጾች ያሉት ነው።

በአብርኆት ቤተ መጽሐፍት እየተካሄደ ባለው አውደ ርዕይ "ጠቅላይ ሚኒስትር ቤተ ንባብ" በተባለው ክፍል ላይ ሃገራዊ ለውጡን ተከትሎ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ወደ ስልጣን ከመጡ አንስቶ ለንባብ ያበቋቸው መጻሕፍት ለአንባቢያን ቀርበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የዛሬ ሰላማችንና ክብራችን በመከላከያ ሰራዊታችን ከፍያለ የተጋድሎ ታሪክ ደምቆ የተጻፈ ነው!

ጽንፈኝነት ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱና ዋነኛው ሕዝብን ከእውነተኛ ማንነቱ ሊያፋቱ የሚችሉ የጥፋት ትርክቶችን በመፍጠር በተቻለው መጠን ሕዝባዊ መሰረት እንዲኖራቸው በሁለንተናዊ መልኩ የተጠናከረ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻዎችን ማካሄድ ነው።

ዘመቻዎቹ ጭፍን ጥላቻዎችን መሰረት ያደረጉ ፤ ሕዝቦችን ያልተገቡ ሥጋቶች ውስጥ በመክተትና ተጨባጭ በሆኑ ነባራዊ እውነታዎች ላይ ያላቸውን መታመን በመስረቅ ከስጋታቸው አትራፊ መሆን ላይ የተንጠላጠሉ ናቸው።

ጽንፈኞች የሕዝብን የዕለት ተዕለት ሕይወት የሚፈታተኑ " እንዲህና እንዲህ ሊደረግብህ ነው፤ እንዲህም ሆኖብሀል " የሚሉ የፈጠራና የስጋት ትርክቶችን ጨምሮ ነገዎችን የሚያጨልሙና ሕዝብን ለጸለምተኛ አስተሳሰቦች ሰላባ ለማድረግ የሚተጉ ናቸው።

በተለይም ኀብረ ብሄራዊነት፤ መገለጫቸው በሆኑ አገራት ፤ ለአገራቱ ሕዝቦች ውበት የሆነውን ኅብረብሄራዊ ማንነት ለጥፋት ተልእኳቸው እንደ አንድ ትልቅ እድል በመውሰድ፤ በሕዝቦች መካከል አለመተማመንና ጥርጣሪዎችን መፍጠርን የተልዕኳቸው ማዕከል ያደርጋሉ።

ሕዝብን በሕዝብ ላይ፤ ሀይማኖትን በሀይማኖት ላይ በማነሳሳት፤ በአገር ያለመረጋጋትና ሁከት እንዲፈጠር ከዚያም ባለፈ የለየለት የጦርነት አውድማ እንድትሆን በማድረግ ከሕዝቦች መከራና ስቃይ አትራፊ ለመሆን ይሰራሉ።

በማኀበረሰብ ውስጥ በተለያዩ ምክንያት የሚፈጠሩ ግጭቶችን ከአቅማቸው በላይ በማግዘፍ ያለመረጋጋትና የውጥረት ምክንያት እንዲሆኑ ከመስራት ባለፈም፤ ግጭቶቹ ሊፈቱ የሚችሉበትን ማኀበራዊ እሴቶች በማሳነስ ከግጭቶች ተጠቃሚ አስካልሆኑ ድረስ ግጭቶች ዘላቂነት እንዲላበሱ ያደርጋሉ።

በእኛም አገር ጽንፈኛ ኃይሎች መሽቶ እስኪነጋ በሚፈጥሯቸው የጥፋት ትርክቶች እያደረጉት ያለው ከዚህ የተለየ አይደለም። በተለይም ከለውጡ ማግስት ጀምሮ መንግስት አዲስ የፖለቲካ ስርአት ለመፍጠር እየሄደበት ያለው የፖለቲካ መንገድ ስጋት የሆነባቸው ኃይሎች ጽንፈኝነትን ዋነኛ የፖለቲካ ስትራቴጂ አድርገው እየተንቀሳቀሱ ነው።

በአንድ በኩል ቀደም ሲል የመጣንበት የፖለቲካ መንገድ ከውድቀት ባለፈ ያተረፈልን የለም በሚል በመንግስት በኩል የተፈጠረው ችግሮችን በውይይት በሆደ ሰፊነት ለመፍታት የመሞከር ሂደት ፤ በሌላ በኩል እነዚህ ኃይሎች ይህን የመንግስት ሆደ ሰፊነት እንደ አቅም ማጣት የማይታቸው እውነታ የሽግግር ወቅት ፈተናውን አክብዶታል።

ባለፉት አምስት ዓመታት በእነዚህ ጽንፈኛ ኃይሎች የተፈበረኩ የጥፋት ትርክቶች ሰሚ ቢያገኙ ኖሮ አገሪቱ እንደ አገር ስንት ጊዜ በአደባባይ ፈርሳ እንደነበርና አንድ ብሄር በአንዱ ላይ ተነስቶ የተፈጠሩ እልቂቶችም ብዛታቸው ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል ለየትኛውም ዜጋ የሚሰወር አይደለም።

ሕዝብ በምርጫ ካርዱ ወዶና ፈቅዶ ወደ ስልጣን ያመጣውን መንግስት በሁከትና በግርግር ከዚያም ባለፈ በጦርነት ከስልጣን ለማስወገድ የተደረጉ አንድ ሺ አንድ የከተት ጥሪዎች እነማንን በቦታው ለማምጣት ተስፋ አድርገው እንደነበርና የቱን ያህል ዋጋ እንዳስከፈሉን ለማስታወስ የሚከብድ አይደለም።

በጽንፈኞች የተሞከረው ሕዝባችንን ከእውነትና ማንነቱ የማፋታት የተጠናከረ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻም ቢሆን እንደታሰበው ሕዝባችንን ወደ አልተገባ ባህሪ ከመውሰድ ይልቅ ፤ ዋጋ እየከፈለ ዘመናት ያሻገረውን ማህበራዊ ስብዕናውን አጥብቆ እንዲይዘው አቅም ሆኖታል።

እነዚህ ኃይሎች ዛሬ ላይ የአማራ ክልልን የግጭትና የሁከት ማዕከል ለማድረግ ከቀደመው ሰፊ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ባለፈ በህቡዕ ተደራጅተው እየተንቀሳቀሱ ስለመሆናቸው መረጃዎች እያሳዩና ከዚያም ባለፈ ተጨባጭ የጽንፈኝነት ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች እየተስተዋሉ ነው። ከዚህም አልፎ በክልሉ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት ለማስፈን በክልሉ ባለው የመከላከያ ኃይል ላይ ሰፊ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ከፍተዋል።

የአማራ ሕዝብ ከወንድም እህቶቹ ኢትዮጵያውያን ጋር በአገረ መንግስት ምስረታ ባለቤት እንደመሆኑ በጽንፈኞች አስተሳሰብ መሰረት ላይ ሊዋቀር የሚችል አገረ መንግስት ይኖራል ብሎ አያምንም። አገር እንደአገር ልትመሰረትም ሆነ ጸንታ ልትቆምና ልትቀጥል የምትችለው ፤ እንደአገር የተመሰረተችበትንና ዘመናት ተሻግራ ዛሬ ላይ ፀንታ እንድትቆም ያደረጓትን መንፈሳዊ፤ ባህላዊ እና ማህበራዊ እሴቶቿን ጠብቃ ማቆየት ስትችል ብቻ እንደሆነም ይረዳል።

በርግጥም የዛሬ ሰላማችንና ክብራችን በመከላከያ ሰራዊቱ ከፍ ያለ የተጋድሎ ታሪክ ደምቆ የተጻፈ፣ የነገ ሰላምና መረጋጋታችንና የመልማት መሻታችንም ከምንም በላይ በመከላከያ ሰራዊቱ ቀጣይ ተልእኮ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ኢትዮጵያውያን ጠንቅቀው የሚያውቁት እውነት ነው!

**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ማን ነው ፌደራሊስት፤ ማነውስ የአንድነት ኃይል?

**ኃይለየሱስ ታዬ (ዶ/ር)**
**ፌደራሊዝም ጥናት ረዳት ፕሮፌሰር**
**ኢ-ሜል፡- tayehaileyesus3@gmail.com**

የአገራችን የፌደራል ስርዓት ተከትሎ በአገራችን ባለው የፖለቲካ አሰላለፍ ራሳቸውን የፌደራሊስት ኃይል ብለው የሚገልጹ ያሉትን ያህል ራሳቸውን የአንድነት ኃይል ብለው የሚገልጹ ኃይሎች ያቀፈ የፖለቲካ አሰላለፍ ይታያል፡፡ ሆኖም የፌደራሊስት እና የአንድነት ኃይል የሚለው ስያሜ ከፌደራል ስርዓት መሰረታዊ መርሆዎች እና ከአገራችን ማህበረሰባዊ ውቅር ጋር በማያያዝ ስያሜዎቹን ዝርዝር አድርጎ ማየት በማህበረሰቡ ውስጥ ከፌደራል ስርዓት ጋር ተያይዞ እየተፈጠሩ የመጡትን እና አሁንም የቀጠሉትን ብዥታዎች ለማጥራት እና ስያሜዎቹ በርግጥ ገላጭ ናቸው ወይ ብሎ ለመጠየቅ ያስችላል ፡፡

የፌደራሊዝም አስተሳሰብ ሁለት መሰረታዊ መርሆዎች አሉት፤ እነርሱም የራስ አስተዳደር እና የጋራ አስተዳደር ሲሆኑ የራስ አስተዳደር ከባቢያዊ የሆኑ አቅሞችን እና ፍላጎቶችን መሰረት አድርጎ ራስን የማስተዳደር፤ ቋንቋን ባህልን የማሳደግ፤ በቅርበት መንግስታዊ አገልገሎቶችን ማግኘትን የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል ነው። የጋራ አስተዳደር ደግሞ አገራዊ እና የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መሳተፍን፤ ለአገራዊ ልማት፤ ደህንነት፤ ሰላም፤ ሰባዊ መብቶች መከበር አስተዎጽኦ ማድረግ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡

ከነዚህ ሁለት መርሆዎች ጋር ተያይዞ ከባቢያዊ ማንነት እና አገራዊ ማንነትን አስተሳስሮ መሄድን ይጠይቃል፡፡ እንግዲህ ፌደራሊዝም ሁለቱ መርሆዎች ተሳስረው እና ሁሌ ሚዛን ጠብቀው መሄድን ታሳቢ የሚያደርግ ፍልስፍና ነው፡፡ የፌደራሊዝም ፍልስፍና መነሻው የጋራ ፍላጎትና ጉዳይ መኖር እና በጋራ በአንድነት ለመቀጠል መወሰን ነው፡፡ በመሆኑም ፌደራሊዝም የራስ አስተዳደርን ወይም የጋራ አስተዳደርን በተናጠል ይዞ የሚሄድ ፍልስፍና ሳይሆን ሁለቱን አስተሳስሮ ሁሌም ሚዛን እየጠበቁ መሄድን መሰረት ያደረገ ነው።

በውጤቱም ጠንካራ ኢኮኖሚ የገነባች፤ ሰላም እና ዴሞክራሲ የሰፈነባት፤ አካታች እና የሁሉም መብት እኩል የሚከበርባት፤ ሁሉም ማህበረሰብ የእኩል ተጠቃሚነት እድል የሚያገኝባት፤ የራሱን መብትና ነጻነት የሌሎችን መብትና ነጻነት ባከበረ መልኩ እኩል የሚከበርባት አንድ ትልቅ አገር መገንባትን ታሳቢ የሚያደርግ ፍልስፍና ነው፡፡ በመሆኑም ከፌደራሊዝም እሳቤ ስንነሳ የራስ አስተዳደር እና ከባቢያዊ ፍላጎት እና ማንነት ብቻ የሚያቀነቅን ኃይል ፌደራሊስት ኃይል ሊሆን ያለመቻሉን ያህል የጋራ ጉዳይ ላይ ብቻ የሚያቀነቅን ኃይል የአንድነት ኃይል ሊሆን የሚችልበት አጋጣሚ በፌደራል ስርዓት ውስጥ ጠባብ ነው፡፡

ምክንያቱም በፌደራል ስርዓት ሁለት ኃይሎች አንድ ወደ መሀል የሚስብ እና አንድ ወደ ውጭ የሚስብ ቢኖሩም ትክክለኛው የአንድነት እና የፌደራሊስት ኃይል የሁለቱን ሚዛን ጠብቆ መሄድ የሚችለው ኃይል መሆኑ ከፍልስፍናው መሰረታዊ መነሻዎች የሚቀዳ ነው፡፡ በዚህ መነሻነት እንደ ፀሃፊዉ እይታ ቢያንስ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ትክክለኛ የፌደራሊስት ኃይል የአንድነት ኃይል የመሆኑን ያህል ፌደራል ስርዓትን ታሳቢ ያደረገ የአንድነት ኃይልም የፌደራሊስት ኃይል ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

በመሆኑም የፌደራል ስርዓቱን መሰረት አድርገው የፌደራሊስት እና የአንድነት ኃይል በሚል ስያሜ የሚገለጹ የኃይል አሰላለፎች የፌደራሊዝም ፍልስፍና መሰረት ያደረጉ መሆናቸው አጠራጣሪ ነው፡፡ ዋናውን የስበት ማዕከል የራስ አስተዳደር ጋር ብቻ የተያያዙ ጥያቄዎች፤ መብቶች ወዘተ.. ብቻ አድርጎ የጋራ ጉዳዩን ረስቶ የሚንቀሳቀስ ኃይል የፌደራሊስት ኃይል ሊያሰኘው የሚችል አንድም ፌደራላዊ አመክኒዮ አይኖርም መነሻውም በፌደራሊዝም ላይ የያዘው እሳቤ የተሞላ አለመሆን ወይንም ፌደራሊዝምን በተሳሳተ መልኩ ለራስ ፍላጎት መጠቀሚያ ለማድረግ መፈለግ ሊሆን ይችላል፡፡

በሌላ በኩል ብዝሃነት ባለበት ሀገር ውስጥ ለብዝሃነቶች የፖለቲካ፤ ኢኮኖሚ፤ ባህላዊ፤ ማህበራዊ፤ አስተዳደራዊ ፍላጎቶቻቸውን የሚያከናውኑበትን አውድ የሆነውን የራስ አስተዳደርን በረሳ መልኩ የጋራ አስተዳደርን እና የጋራ ጉዳዮችን ብቻ ይዞ መንቀሳቀስ የአንድነት ኃይል የሚሰኝበት ፌደራላዊ አመክኒዮ የለውም፡፡ ሆኖም አሰላለፎቹ ከፌደራል ስርአት ውጭ የሚኖርን አውድ ታሳቢ ያደረገ ከሆነ እንደ አገራችን ነባራዊ ሁኔታ የፌደራሊስትም ሆነ የአንድነት ኃይል የብተና ኃይል የሚሆንበት እድሉ ሰፊ ነው፡፡

በአገራችን የፌደራል ስርዓት የአገራችን ነባራዊ ሁኔታ፤ የፌደራሊዝም ፍልስፍና እና ፌደራላዊ ፖለቲካ አደረጃጀት መሰረት አድርጎ ሁሌም በራስ አስተዳደር እና በጋራ አስተዳዳር መካከል የሚኖረውን ሚዛን ጠብቆ የሚተገብር ኃይል የፌደራሊስት እና ከዚያው ሳለም የአንድነት ኃይል ሆኖ የሚወጣበት ሁኔታ መፈጠሩ የማይቀር ነው፡፡

ዋናው ቁምነገር በፌደራል ስርዓት የበላይ ወይም የበታች የሚሆን ማህበረሰብ የሌለበት ሁሉም የራሱን ጉዳይ በራሱ በየደረጃው የሚያስተዳድርበት እና በጋራ ጉዳዮች ላይ የሚሳተፍበት እና ለጋራ አገራዊ እድገት አስተዎጽኦ የሚደረግበት እኩል እድል የሚፈጠርበት መሆኑን በመገንዘብ ለዚህ ስኬት በመነጋገር፤ በመመካከር፤ በመደጋገፍ፤ በመተባበር፤ በመከባባር፤ እውቅና በመስጠት፤ የሌሎችን ችግር እንደራስ አድርጎ በማየት፤ አሸናፊና ተሸናፊ የሚል የፖለቲካ ቁርቁስ ሳይሆን ሁሉም አሸናፊ የሚሆንበት ሚዛናዊ ሂደቶችን መከተል የሚጠይቅ መሆኑን መገንዘብ እና ለተግባራዊነቱ መትጋት ነው፡፡

የፌደራል ስርዓትን ተመራጭ የሚያደርጉትን ብዝሃነትን ለማስተናገድ ያለውን እምቅ አቅም እና በብዝሃነት የተዋበ አንድነትን ለመገንባት የስርዓቱ መኖር መሰረታዊ ምክንያት በትክክል በሚተገበርበት መልኩ የሚንቀሳቀስ ኃይል ከዚያው ሳለ የአንድነት እና የፌደራሊስት ኃይል ባህሪያትን የሚላበስበት ሀኔታ መፈጠሩ አይቀርም፡፡

ከዚህ አኳያ በአገራችን አሁን ከዚህም ከዚያም የሚሰሙት የኃይል አሰላለፍ ብያኔዎች ከፌደራል ስርዓት አመክኒዮ አንጻር ሲታዩ የተሳሳቱ እና ማህበረሰቡንም በፌደራል ስርዓት ዙሪያ ያለውን አረዳድ የበለጠ ትክክለኛ ወደ አልሆነ አቅጣጫ የሚመሩ ስርዓቱንም ከስርዓቱ ባህሪያት ወጣ ባለ መልኩ የፖለቲካ ሊህቃኑ በሚፈልጉት መልኩ የፖለቲካ ፍላጎት ማስፈጸሚያ በማድረግ በአገራችን ነባራዊ ሁኔታ በጣም ተፈላጊ የሆነውን ስርዓት በአግባቡ እንዳይተገበር እንቅፋት ከመሆን በዘለለ ፋይዳ የሌለው በመሆኑ በፌደራል ስርዓት ዙሪያ ትክክለኛ እይታዎች እንዲያድጉ እና በተግባርም እንዲውሉ የሁሉንም የጋራ ጥረት የሚጠይቁ ይሆናል፡፡

በአገራችን ከብዝሃነታችን ጋር ተያይዞ ለሚኖሩ ብዝሃ የሆኑ የፖለቲካ፤ ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊ እና አስተዳደራዊ ጥያቄዎች አንጻራዊ በሆነ መልኩ በተሻለ ሁኔታ ማስተናገድ የሚችለው የፌደራል ስርዓት የማይሆንን ከሆነ ምን አይነት ስርዓት ሊሆንን እንደሚችል ብዝሃነት እና አንድነትን መሰረት አድርጎ ሲፈተሽ አማራጩ ከመበተን የዘለለ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ውስን መሆኑ ነው፡፡

ችግሩ በአገራችን የማህበረሰባዊ ውቅር፤ አሰፋፈር፤ አኗኗር፤ አስተሳሰብ፤ ስነልቦና ወዘተ አንጻር እርስ በእርስ ከመጠፋፋት በዘለለ በሰላም የምንለያይበት አማራጮች የሉም ብሎ መደምደም የሚስያችን አውድ ያለ መሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም የፌደራሊዝም እሳቤዎችን በተገቢው መረዳት፤ የፌደራላዊ አስተዳደር ስርዓቱን በትክክለኛው መንገድ መተግበር አሳሳች የሆኑ የኃይል አሰላለፍ ብያኔዎችን መፈተሽ ፌደራል ስርዓቱን ትክክለኛ ወደ አልሆነ አቅጣጫ እንዳይመሩት በማህበረሰቡ ውስጥ የፌደራሊዝም አስተሳሰብ እና የፌደራል ፖለቲካዊ ስርዓት ላይ የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት ያደረገ ግንዛቤ እንዲኖር መስራት ይጠበቃል፡፡

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# "ደመኞቹ አውራሽና ወራሾች"

**በማናቸውም አገራዊ ጉዳዮቻችን ላይ ስንናገርም ሆነ ስንጽፍ ደመቅ እና ጫን አድርገን ሳለመግባባት የምናግተለትለው ከመፍትሔ ጥቆማ ይልቅ ጥያቄዎችን ነው። በቋንቋችን —ለምን? እንዴት? የት? መቼ? ማን?" ብለን የምንጠራቸውንና ባእዳን ደግሞ በራሳቸው ልሳን፤ Who? What? Where? When? Why? የሚሏቸውን አምስት መኮርኮሪያዎችን (5Ws እንዲሉ) ልብ ብለን ብንመረምራቸው ጥያቄዎቹ ለእኛ —ወርቃማ" የሚሰኙ የእውነት ማፈላለጊያና የጠራ መረጃ ማንጠሪያ ቁልፎች ከመሆን ይልቅ መናቆሪያና መወራወሪያ ጠጠሮቻችን ከሆኑ ሰነባብተዋል።**

እነዚህ ወርቃማ የመቆስቆሻ ጥያቄዎች ጥበብ እንዲዛቅባቸው እና የነጠረ መረጃ እንዲታፈስባቸው በማሰብ በተደራጀ መልክ ሰድሮ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ያስተማረው ተጠቃሽ መምህር ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በአንደኛው ክፍለ ዘመን ገደማ የኖረው ግሪካዊው ሄርማጎረስ (Hermagoras of Temnos) የተባለው ሞጋች ፈላስፋ ነበር። ይህንን የሩቅ ዘመናት መምህር ለማስታወስ የተፈለገው ልክ እንደ ዘመኑ ርቀት ሁሉ እኛ ኢትዮጵያውያን የምንባለው ዜጎች ጥያቄዎቹ ለእለት ተእለት አኗኗራችንም ይሁን በታሪካዊ ትርክታችን ጉዳይ ከሚያግባቡን ይልቅ እጅግ እያራራቁ ስለምን ሆድና ጀርባ እንዳደረጉን ስላልገባን ትምህርቱ እንዲብራራልን ሞጋቹን ሄርማጎረስን ለመሞገት ነው። "ሙታንም ይሞግታሉ!" ያለው ማን ነበር?

ለምሳሌ፤ አንድን ሰው ከብሔሩና ከማንነቱ ነጥለን ሃሳቡንና አመለካከቱን ከመሞገት ይልቅ "እከሌ እንደዚህ የሆነው ወይንም እጁ የገባውን ያንን ነገር ሊያገኝ የቻለው የየትኛው ብሔር አባል ቢሆን ነው? ያንን ሃሳብ ለመሰንዘር የተደፋፈረውስ ምን ቢያስብ ነው? ለምንስ ይሄን ጊዜ መረጠ? ከበስተ ጀርባው ያለው ማን ነው? አዋዋሉ ከነማን እና ለምን ጉዳይ ነው? ይህንንና ያንን ጥቅምና ስኬት ሊያገኝ የቻለውስ ከበስተጀርባው ማን ቢኖር ነው? የሚናገርው ቋንቋ ረድቶትስ እንደሆን? ወዘተ. የሚሉትን ጥያቄዎች በአብዛኛው ስንመራመርባቸው የምንውለው በንጹህ ኅሊና እውቀትና መረጃ ለማግኘት በማሰብ ሳይሆን በተቃራኒ ስሜት ውስጣችንን እያጠቆርን ነው።

በእንዲህ ዓይነት የጥርጥር ባህር ውስጥ ተዘፍቀንና ባህላችን አድርገን ተገዢ መሆን ለተከታዩ ወራሽ ትውልድ ምን "ቅርስ" አኑረን ለማለፍ ነው? መልሱ ለማናችንም የተሰወረ ስላይደለ ከኅሊናችን ጋር መሟገቱ ይበጃል። የአውራሽ እና የወራሽ የደም መስዋእት የቅብብሎሽ ታሪካችን በሙሉ ቢመረመር ከላይ የተጠቀሰውን እውነት ሳይንተራስ "በማንነትና በሰውነት ላይ ብቻ ተመስርቶ" ተፈጽሟል ለማለት ያዳግታል።

በዚህም ምክንያት የታሪክ ውርሳችንም ሆነ አወራረሳችን ምክንያታዊነትን ስለሚጠየፍ መንግሥታዊ ሥርዓቶችን ተቀብለን እሶሶ የምንለው፤ በስተመጨረሻም "ይሰቀሉ" እያልን የሆሳዕናንና የቀራኒዮን ታሪክ ስንደግም የኖርነው "ደም ሳይፈስ ስርዬት የለም" የሚለውን የቅዱሳት መጻሕፍት አንኳር ጭብጥ በተበከለ አስተሳሰብ በርዘን ነው። ሃሳቡን ዘርዘር አድርገን እንመልከተው።

**ደም ሳናፈስ ስለምን ስርየት ተነፈግን?**

አብዛኞቹ ታሪኮቻችን የተጻፉት በደም ቀለም መሆኑ ለክርክር አይቀርብም። ከደም መስዋእትነት በፊት በጥያቄዎች እየተሟገትን መፍትሔ ከመፈለግ ይልቅ በሻምላ እየተሞሻለቅን ጥሎ መውደቅን እንደምንመርጥም እንኳን ለተቀረው የዓለም ማሕበረሰብ ቀርቶ ለእኛ ለራሳችንም ለባለታሪኮቹም ቢሆን የገባን አይመስለንም። "ወርቃማ ጥቄዎቹ" ከእኛ ጋር እየኖሩ ያሉት በባይተዋርነትና በባእድነት እንጂ በጉዳዮቻችን ውስጥ መፍትሔ አመንጪ እንዳልሆኑም ከውጤታቸው ማረጋገጥ ይቻላል።

ማሳያዎቻችን የሩቆቹ ብቻ ሳይሆኑ የቅርቦቹም ታሪኮቻችን ናቸው። ወደ ኋላ ብዙ ከመንደርደር ይልቅ የትናንቶቹን ብቻ አስታውሰን ሙግታችንን ደርዝ እናሲዘው። መንግሥታዊ ሥርዓቶቻችን በሙሉ ይዘውት የሚነሱት መሪ ሃሳብ አማላይና አጓጊ ብቻ ሳይሆኑ ኑሯችንን ወደ ገነትነት የሚለውጡ ተደርገው የሚቀረጹ ዓይነቶች ናቸው። እናስታውስ!

**"ያለ ምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም!"**

ይህ አማላይ "መርህ" የጊዚያዊ ወራደራዊ ጁንታ ንጉሡን ከሥልጣን መንበራቸው ላይ ገፍትሮ አገሪቱን በእጁ ባስገባበት የመጀመሪያ ወራት ጮክ ብሎ የተስተጋባ የማታለያ መፈክር ነበር። በታዳጊ የወጣትነት ዘመኔ በትንሽ በትልቁ ይፈክር የነበረውን ይህንን የደርግ ማጭበርበሪያ ባስታወስኩ ቁጥር አንድ የቤተሰቤ ወዳጅ ትዝ ይሉኛል። እኚህ ሰው በንጉሡ ዘመን የግንደበረትን ሕዝብ ወክለው ለንጉሣዊው ፓርላማ ተመርጠው ያገለገሉ የዕድሜ ባለፀጋ ነበሩ።

ይህ መፈክር አየሩን በሞላበት አንድ እለት ለእንግድነት ወደ ቤተሰቦቼ ቤት መጥተው ሲጨዋወቱ እንዲህ ነበር ያሉት። "ደርጉ ያለቦታው ደም እያለ የሚደነፋው ደም እየሸተተው ነው። ታሪኩ በደም እንደሚደመደምም በራሱ ላይ ትንቢት መናገሩ ነው።" ዋናው የሃሳባቸው ፍሬ ነገር ይህ ነበር።

እውነትም እኚያ አባት እንዳሉት ወታደራዊ መንግሥት ገና በንጉሡ ዙፋን ላይ ከመቀመጡ እጁን የታጠበው ስልሳ የሚሆኑ የንጉሣዊ ሥርዓቱን ባለሥልጣናት ጭዳ አድርጎ በግፍ ግድያ በመጨፍጨፍ ነበር። ግድያው በዚህ ብቻ ሳያቆም ኢዲዩ፣ ገንጣይና አስገንጣይ፣ "ነጭና ቀይ ሽብር" በሚል የቀለም አብዮት የደም ጅረት አገሪቱን እንዳጥለቀለቀ እጅግም ያልመሸበት ታሪካችን ምስክር ነው። እብሪትና ትምክህት ባሳበጠው ፖሊሲ ምክንያት ምን ያህል ወገን በዚያ አስከፊ ሥርዓት "ደሙ ደመ ከልብ" ሆኖ እንዳለፈ ብዙ ጉዳዮችን በመዘርዘር ማስታወስ ይቻላል።

ምክንያታዊ በሆኑ ውይይቶች ትውልዱ መተማመን ቢችል ኖሮ ያን የመሰለ አንድ ትውልድ እምሽክ አድርጎ የበላ ክስተት ባልተፈጸመ ነበር። ታሪኩ በደም ተጀምሮ በደም የተጠናቀቀውን ወታደራዊ ሥርዓት የተረከበው የሕወሓት/ኢህአዴግ ታሪክም ከዚህ ቢከፋ እንጂ የተለየ አልነበረም። በጥቂቱ እንዘክረው።

**"ሰላምና መረጋጋት"**

ከጫካ ተንደርድሮ በመምጣት የደርግ ሥርዓትን ለግባ መሬት የዳረገው ወራሹ ቡድንም በመጀመሪያው የሥልጣን ወራቱ ሕዝቡን ለመሸንገል የሞከረው "የሰላምና መረጋጋት ኮሚቴ" በሚል ሽፋን የበቀል ሜራ በመዘርጋት ነበር። በተለይም የቀዳሚውን ሥርዓት የፖለቲካ መዋቅር (ኢሠፓ - የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ) ለማፈራረስና አባላቱን ለማሽመድመድ፣ የጦር ኃይሉንና የሠራዊቱን ጀግኖች ለመበተንና ለማዋረድ የቻለው በየቀበሌውና በየመዋቅሩ "የቀይና የነጭ ሽብርን ምክንያት አሳቦ" የሰላምና መረጋጋት ኮሚቴ የሚል ኃይል በማቋቋም ነበር።

በሰላምና በመረጋጋት ስም የተሰየሙት ኮሚቴዎች እንኳንስ ግብራቸው እንደ ስማቸው ሊሆን ቀርቶ ጭርሱኑ ሳይውሉና ሳያድሩ የጭካኔ መገለጫ ሆነው የደምና የእምባ ምንጭ በመሆን ዜጎች ተሰቃይተውባቸዋል።

"ማጋለጥ" በሚል የበቀል እርምጃም ብዙዎች ተገድለዋል፣ ሺህዎች ታፍነው የደረሱበት አይታወቅም፣ ለቁጥር የሚያታክቱትም በእስራትና በእንግልት ተሰቃይተው ሊያልፉ ግድ ሆኗል። በተከታታይ ዓመታትም የግፍ ድርጊቶች በታጨቁባቸው እርምጃዎች ምክንያት ምን ያህል ወገን ለመከራና ለስቃይ እንደተዳረገና አገሪቱ እንደምን ወደ አዘቅት እንዳሽቆለቆለች የሚታወቅ ነው። የአውራሽና ወራሽ ሥርዓተ መንግሥታቱ "የጥቁር ደም" ታሪክ ገና በአግባቡ ተሰንዶ ስላልተጠናቀቀ ወደፊት ብዙ አሰቃቂ ታሪኮችን መስማታችን አይቀርም።

**"ሰይፍ፡- ሰላም፣ ፍቅር ይቅርታ፤**

ኢህአዴግ እንደ ቀዳሚዎቹ ሥርዓቶች የሞቱን ጽዋ ተጎንጭቶ የግባ መሬቱ የቀብር ሥርዓት ገና ተፈጽሞ ሳይጠናቀቅ በፊት አዲሱንና ከራሱ አብራክ የወጣውን "ለውጥ" ለማደናቀፍ የተሞከረው በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ላይ በሰኔ ወር 2010 ዓ.ም በመስቀል አደባባይ ላይ የግድያ ሙከራ በማድረግ ነበር። ለረዢም ዘመን ሲናፍቁንና ሲያስጎመጁን የኖሩት "ፍቅር፣ ይቅርታ፣ ሰላም፣ መከባበር፣ ወዘተ." የሚሉት ሃሳቦች ገና በጽንስ ላይ እያሉ ስንት አገራዊ መከራ እንደወረደብን እናስታውሳለን። የግፍ ግድያዎቹ ዓይነትና ብዛት፣ መፈናቀሉ፣ አልፎም ተርፎ ከሕወሓት ጋር በተደረገው ጦርነት ምን ያህሉ ወገን እንደረገፈ በቁጥር ሳይሆን የሚገመተው በጅምላ ነው። "ሆድ ይፍጀው!"

**ወደ ቀልባችን ተመልሰን ራሳችንን እንጠይቅ፤**

በመነጋገር፣ በመመካከር፣ በመደማመጥና ልቦናችንን ከፍተን ለመወያየት አዚም አድርጎ የተበተበን ባህል ወይንም እሥራት ምክንያቱ ምን ይሆን? እስከ መቼስ ሥርዓቶች በተፈራረቁ ቁጥር ጥቋቁር ታሪኮቻችንን ለመመዝገብ በጥቁር መዛግብቶቻችን ላይ ጥቁር አሻረ ለማሳረፍ እንሽቀዳደማለን? እስከ መቼስ እንደዚህ እንቀጥላለን።

በሥራ አጋጣሚ ከተገናኘነው አንድ የውጭ ዜጋ ጋር የተመላለስነውን አንድ ወግ ባስታውስ ለሃሳቤ ድጋፍ ይሆን ይመስለኛል። ሰውዬው የሕዝብ ቁጥሩ ይህ ልኩ የማይባል ትልቅ አገር ዜጋ ነው። ለሥራ ጉዳይ በተገናኘንበት አንድ ወቅት በአገሩ ሁለት ባቡሮች ተላትመው በሞቶዎች የሚቆጠሩ ዜጎች አልቀው የነበረበት ሣምንት ስለነበር፤ በአገሬ ወግና ሥርዓት መሠረት "በአገራችሁ በተፈጠረው የባቡር አደጋ ምክንያት ስላለቁ ዜጎቻችሁ መጽናናትን እመኝላችኋለሁ። የሀዘናችሁ ክብደትም ይሰማኛል..." ብዬ ገና ንግግሬን ሳልጨርስ፤ "ለምን ማዘን አስፈለገህ?" በማለት አፋጠጠኝ ደግሞም አሳፈረኝም።

"የሀዘኔ ምክንያቱ ስላለቁት ዜጎቻችሁ ነው" ብዬ ስመልስለትም፤ "ልታዝን አይገባም። አገሬ ባላት የሕዝብ ቁጥር በዓለም ፊት ቀዳሚ ከሚሰኙት ጥቂቶች መካከል አንዷ ነች። ስለዚህ የሚሞተው ሊሞት ግድ ነው፤ ብዙም አያስገርምም። እንዲያውም የሕዝብ ቁጥሩ ለብዙ ችግር እየዳረገን ስለሆነ እንዲህ አይነቱ አደጋ መከሰቱ ጠቃሚ ጎንም ሳይኖረው አይቀርም " በአገሬ ብሂል መሠረት ሰውዬው የመለሰልኝ መልስ "ከአንድ ሣር ቤት ላይ አንድ ሰበዝ ቢመዘዝ አያስገርመም" የሚል ብጤ መሆኑን ልብ ይሏል።

በዚህ ወግ መነሻነት ራሳችንን መፈተሹ መልካም ይሆናል። በተለያየ መልኩ የምንሰማቸው የዜጎች ሞት ስለምን ልበ ደንዳና አደረገን? "ምን ይሉት የሞራልና የመንፈስ ስብራት ቢገጥመን ነው ልባችንና መንፈሳችን የደደረው? የድንዛዜያችን ምንጬና ሰበቡ ምናልባትም "ደም ሳይፈስ ስርዬት የለም" የሚለው የተለመደ አገላለጽ ብሔራዊ መርሆዋችን ሆኖ ይሆንን?

የንጹሐንን ሞትና እልቂት ስንሰማና የአሟሟታቸው ሁኔታ ተብራርቶ ሲገለጽልን በተሰበረ ልብ ከመስማት ይልቅ እንደ አዘቦት ቀን ወግ "ነው እንዴ?" ብለን እንደ ዋዛ እንድናልፍ የሆነበት ምክንያቱ ምን ይሆን? "ዘጠኝ ሞት መጣ ቢሉት፤ አንዱን ግባ በለው" እንዳለው ነውጠኛ አውራሾቻችን ያወረሱን የቂምና በቀል ፍሬ ይሆንን?

"የደም ኪዳን" ውርሳችን ተቀዶ በንግግር፣ በውይይትና በምክንያታዊነት እየተደማመጥን መግባባት እስካልቻልን ድረስ ቀጣዩ ወራሽ ትውልድም የራሱን ዘመን በደም እያቀላ ከመኖር የሚከለክለው ተጨባጭ ምክንያት ያለ አይመስለኝም። ከትናንት ትውልዶች የውርስ ዱላውን የተቀበልነው የዛሬዎቹ ዜጎች ለነገው ወራሽ ትውልድ ማቀበል የሚገባን "ዱላውን ደም አስነክተን ሳይሆን" እንደ ጥምቀት በዓል ዘንግ በውብ ቀለማት ሽልመን ሊሆን ይገባል። እነዚያ ቀለማት "ወርቃማ ያልናቸው ጥያቄዎች" ሲሆኑ ልብ ተቀልብ ሆነን ተነጋግረን የቀዳሚውን ዘመንም ሆነ የራሳችንን ዘመን ችግሮች ለማስወገድ እጅ ለእጅ፣ ልብ ለልብ ተጨባብጠን ወደ መደማመጥ ልንመለስ ይገባል። ሰላም ለአገሬ፤ ለዜጎችም በጎ ፈቃድ።

> **ከትናንት ትውልዶች የውርስ ዱላውን የተቀበልነው የዛሬዎቹ ዜጎች ለነገው ወራሽ ትውልድ ማቀበል የሚገባን «ዱላውን ደም አስነክተን ሳይሆን» እንደ ጥምቀት በዓል ዘንግ በውብ ቀለማት ሽልመን ሊሆን ይገባል**

# «ተባብረን ተደምረን በርከት ያሉ ሃላላ ኬላዎችን መሥራት አለብን»

- ዶክተር ዐቢይ አሕመድ
  የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**



ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በኢትዮጵያ ከተከናወኑ እና በመከናወን ላይ ከሚገኙ ታላላቅ ፕሮጀክቶች መካከል ገበታ ለሸገር፣ ገበታ ለአገር እና ገበታ ለትውልድ ተጠቃሽ ናቸው። ከእነዚህ መካከል በገበታ ለአገር ፕሮግራም የሚገነቡ ፕሮጀክቶች በአማራ ክልል ጎርጎራ፣ በኦሮሚያ ክልል ወንጪ እንዲሁም በደቡብ ክልል (በአሁኑ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል) ኮይሻ የሚካሄዱ ግንባታዎች መሆናቸው ይታወቃል። ሰሞኑን ለምረቃ የበቃው የኮይሻ ፕሮጀክት አንድ አካል የሆነው በዳውሮ ዞን የሚገኘው የሃላላ ኬላ ሪዞርት ውብ በሆነ መልኩ መጠናቀቁ እውን ሆኗል።

ተጠናቆ ለምረቃ የበቃው የሀላላ ኬላ ሪዞርት ጋራና ሸንተረር፣ ወንዞችና ጅረቶች፣ አስደናቂ የመሬት አቀማመጥ፣ የዓመቱን አብዛኛውን ጊዜ ለምና አረንጓዴ በሆነ አካባቢ የሚገኝ ነው። ከ16ኛው እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን በዳውሮ ነገሥታት የተሠራው የሃላላ የደረቅ ድንጋይ ግንብ ድንቅ ታሪክና ቅርስ ያለበት ከግቤ ሦስት የኃይል ማመንጫ በተፈጠረው ሐይቅና የውሃ ላይ መዝናኛ እንዲሁም የዓሣ ምርት ያለበት እጅግ ውብ ቦታ እንደሆነም ይታወቃል። ሃላላ ኬላ የቱሪስት መስህብ እንዲሆን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በገበታ ለአገር ፕሮግራም አማካይነት እንዲገነባ ባደረጉት መሠረት ውብ ሆኖ የተሠራ ሪዞርት ነው። ሃላላ ኬላ በኢትዮጵያ ውስጥ በሪዞርት ደረጃ ከሚታወቁ ሁሉ አንድ ደረጃ የበለጠ ሆኖ የተጠናቀቀም ነው።

በምረቃ ሥነሥርዓቱ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር እና የዳውሮ አባት ያስተላለፏቸውን መልዕክቶች እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

**የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መልዕክት**

ዛሬ ትልቅ ቀን ነው። ቀኑን ከፍ አድርገን እንድናይ የሚያደርገን፤ እጅግ ሥራ ወዳድ፣ ውስጡ ሰላም የሆነ፣ አካባቢውን በታማኝነት የሚጠብቅ፣ አገሩን አብዝቶ የሚወድ፣ በፍቅር፣ በባህል በውስጠ ትልቅነት የተሞላ የዳውሮ ሕዝብ እንደዚህ ዓይነት ነገር ለሕዝቡ ተሠርቶ፤ በዚህ ቦታ ለማየት በመብቃቴ እጅግ ክብር ይሰማኛል። ለሌሎች ወንድም እና እህቶቼ ለኢትዮጵያውያን ማስተላልፍ የምፈልገው መልዕክት አዲስ አበባ ሌሎች ከተማዎች ከጨነቃችሁ፣ ከከበዳችሁ እና ሁኔታዎች ካልተመቻችሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላማዊ የሆነው ቦታ ዳውሮ ይባላል። ኑና እረፉ፤ ኑና አስቡ፤ ኑና ፃፉ፤ ለብዙ ነገር አዕምሯችሁ እንዲነቃቃ የሕዝብ እና የአካባቢ ሠላም ያለበት ስለሆነ ሃላላ ኬላን ለማየት ኑ፤ ቀጠሮ አትያዙ በማለት ጋብዣችኋለሁ።



የሃላላ ኬላ እና አካባቢው ለብዙ ዘመናት ነበር። እኛ ቦታውን አልሠራነውም፤ ቦታውን ነው ያየነው። ብዙ ጊዜ ኢትዮጵያውያን የተወሰደብን እና ልናስመልሰው የሚገባው ነገር ዓይናችንን ነው። ዓይናችን ከወንዞቻችን፣ ከመስኮቻችን፣ ከባህሎቻችን ከወንድማማችነታችን እሳቤዎች ተወስደው በጥላቻ፣ በክፋት፣ በመሰዳደብና በአልባሌ ነገሮች ላይ እንድናተኩር ሆነዋል። ያንን ዓይናችንን ማስመለስ ብንችል ከመናናቅ፣ ከመሰዳደብ፣ ከመጠላላትና ከመገፋፋት ብንወጣ ምን ዓይነት ምድር እንዳለን፤ ይህን ምድር እንዴት ማስዋብና መቀየር እንደሚቻል ባወቅን በተጠቀምን ነበር።

ይህ ስፍራ በእኛ እጅ ሆኖ ነው እምብዛም የሆነው እንጂ፤ ሌሎች አገራት እንደዚህ ዓይነት ቦታ ቢኖራቸው ምን ሊያደርጉት እንደሚችሉ ማሰብ ለብዙዎቻችሁ ከባድ አይሆንም። አንደኛ በጣም ንፁህ የሆነ ከፍተኛ ንጹህ ውሃ አለ። በግድቡ ምክንያት በጣም ከፍተኛ የሆነ ውሃ አለ። ሁለተኛ ለ100 ዓመታት የቆየ የአባቶቻችን ጀግንነት የእጅ ጥበብ የታየበት የሃላላ ኬላ ግንብ አለ። ሦስተኛ ታይተው የማይጠገቡ ተራሮች አሉ። መልክዓ ምድሩ በሁለቱም ወቅቶች በሙቀቱም በቅዝቃዜ ጊዜውም የራሱ የሆነ የተለየ ውበት አለው። ጠዋት ስንነሳ ፀሐይ እዚህ ቦታ በተለየ ሁኔታ የምትወጣ እስኪመስል የተለየ ውበት አላት። ማታ ስትጠልቅልም እንደዚሁ ሌላ አካባቢ የምትጠልቅ እስከማይመስል ድረስ በተለየ ውበት ትወጣለች።

በከተማ የምንኖር ሰዎች በወር አንድ ጊዜ ወይንም በሁለት ወር አንድ ጊዜ ወይንም በሦስት ወር ሁለት ሦስት ቀን በእንደዚህ ዓይነት ስፍራ ከብዙ ነገር ተነጥለን መዋል ብንችል ውስጣችን የመታደስ አቅም አለው። ውስጥ ይታደሳል። ልክ ቤት ቀለም እንደሚቀባው ሁሉ ውስጥም የደከሙ ሴሎች የመታደስ አቅማቸው የበዛ እንዲሆን ጉዞ ማድረግ፣ ማንበብ እንደዚህ ዓይነት ቦታ ከቤተሰብ ጋር መውጣት በእጅጉ ለሰው ልጅ ጤና አስፈላጊ ነው።

የሃላላ ኬላ ላይ ያየና በሥራ ሂደት ስንመላለስ ብዙ ሙያተኞች ሲሳተፉበት የታዘብነው፤ የዳውሮ ሕዝብ ከዚህ በላይ በርከት ያሉ ሥራዎች ቢሠሩለት የሚጓጓ ሕዝብ ነው። በጣም ሰላም የተሞላ ሥቆ የሚያስቅ፣ አብልቶ የምንጠግብ የማይመስለው ያለውን ሁሉ የሚያወጣ ሰው ለማየት፤ ሰው ሰላም ለማለት እጅግ የሚጓጓ ሕዝብ ነው። እንደዚህ ዓይነት ስፍራ መጥቶ ማየት ብቻ ሳይሆን፤ ይህን መልካምነት ሌሎች አካባቢዎች ላይ ማብዛት ማበራከት ስለሚያስፈልግ ኢትዮጵያውያን በጣም ቀላል ነው፤ አዲስ አበባ ሃዋሳ በአዲሱ መንገድ ሁለት ሦስት ሰዓት የሚወስድ ከሆነ ከሐዋሳ ወደዚህ ከሁለት እና ከሦስት ሰዓት በላይ አይወስድም። ወይም ከአዲስ አበባ አርባ ምንጭ ብንሄድ፤ ከአርባ ምንጭ ሶዶ አንድ ሰዓት ተኩል ሁለት ሰዓት ቢወስድ ነው። ከሶዶ እዚህ ድረስ ከ30 እስከ 40 ደቂቃ በላይ አይወስድም። ለጥቂት ሰዓታት በመንዳት እዚህ ስፍራ ደርሰን በውሃ ላይ ለመጫወት የአጥሩን ታሪካዊ ሁኔታ ለማየት ግድቡን ለማየት፤ ብዙ ኢትዮጵያውያን ግድቡን አያውቁትም፤ አላዩትም። ለማየት እድል ይሰጣልና መጥተን እያየን ይህን ስፍራ ሞር እንዲሰፋ እንዲያብብ እንዲበራከት ብናደርግ እጅግ ጠቃሚ እንደሚሆን እተማመናለሁ።

ከማየት በተጨማሪ የተወሰደብን ሁለተኛው ነገር ልቦና ነው። ዓይናችን ከመሰወሩም በላይ ልቦናችን ቀና ቀናውን ከማየት ተወስዶብናል። እውነት መስፈሪያዋ ግልጥ ያለና የሚታወቅ ነገር ነው። እውነትን እየንዳንዱ ሰው በራሱ መስፈሪያ ሊለካት አይችልም። የዓለም ፈላስፋዎች የተስማሙባቸው ሦስት መስፈሪያዎች እውነት አላት። አንደኛው እውነት የሚለካበትና የሚታወቅበት መንገድ ፍጹማዊነት መሆኑ ነው። ፍፁም እውነት ከሆነ አይነፃፀርም፤ አይወዳደርም እንዳለ ይወሰዳል ማለት ነው። ሁለተኛው አንጻራዊ እውነት ነው። አንጻራዊ እውነት ከሌላ እውነት ጋር ወይንም ከእርሱ ከሚቃረን ነገር ጋር ተነፃጽሮ የሚታይና የሚወሰድ ነው።

ሦስተኛው እውነት ተጨባጭ እውነት ነው። የሚታይ፣ የሚዳሰስ፣ አከራካሪ ያልሆነ፤ በምናብ የሚደረስበት ሳይሆን በዓይን ታይቶ ተገልጦ የሚዳሰስ ነገር ማለት ነው። ሃላላ ኬላ በሦስቱም መመዘኛ ቢወሰድ፤ እጅግ ውብ ስፍራ የሚለውን መመዘኛ ያሟላል። ነገር ግን ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ችግር አለ። የራስን እውነት የወል እውነት ማድረግ፤ የራስን እውቀት የብዙኃን እውቀት ማድረግ ሳይሆን፤ የራስን ውሸት በብዙኃን ላይ ጭኖ እውነት ለማድረግ መጣር የበዛበት የፖለቲካ አውድ ነው አሁን ያለው። ውሸትን በማለባበስ እውነት ማድረግ አይቻልም። እውነት መስፈሪያዋ ግልጥ ያለ ነው። ለውበትም፣ ለፖለቲካ አመለካከትም ለማንኛውም ነገር እውነትን የምንለካበት መስፈሪያ የታወቀና ለሁላችን የሚሠራ ስለሆነ በአዳዲስ እውነት፣ በአዳዲስ መስፈሪያ ውሸትን ቀባብተን እውነት ለማድረግ ብንሞክር እንደ ሃላላ ኬላ ያለ ውብ ነገር ተድብቆ እንዲኖር ከማደረግ ውጪ በተለየ ሁኔታ ጥቅም የለውም።

ኢትዮጵያ ህብረብሔራዊት ናት። የብዙ ብሔሮች፣ ባህሎች፣ ቋንቋዎች አገር ናት። ኢትዮጵያን የሚወድ ሰው ሁሉ ቅድም ያየነው የዳውሮ ባህል፣ የአጨፋፈር ስልት፣ እንግዳ የመቀበል ልምምድ ባህሌ ነው ብሎ መቀበል መቻል አለበት። ባህሌ ነው ብሎ መቀበል እንኳን ካልቻለ የዳውሮ ወንድም ሕዝቦች ባህል ነው ብሎ ማክበር አለበት። ኢትዮጵያዊነትን ከፈለግን መከባበር ያስፈልጋል። በቋንቋ፣ በባህል በእምነት ያለውን ልዩነት መቀበል ያስፈልጋል። ህብረብሔራዊት ናት ሲባል ኢትዮጵያ በእምነትና በብሔር ብቻ አይደለም። ከዚያ ባሻገር በተፈጥሮም ህብር ያላት አገር ናት። ለምሳሌ በምልክዓ ምድር ብንወስድ ዛሬ እዚህ ከፍተኛ ዝናብ ነበር። ከፍተኛ ሙቀት ያለባቸው የኢትዮጵያ ከባቢዎች አሉ። እዚህ አካባቢ ተራራማ ነው። ሜዳ ብቻ የሆኑ ተራራ የማይታይባቸው ስፍራዎች በምሥራቁ የአገራችን ክፍሎች አሉ። በመልክዓ ምድር፣ በተፈጥሮ፣ በወቅት አንዳንዱ የበዛ ውሃ ያለው፤ አንዳንዱ የበዛ የውሃ ችግር ያለበት በጣም

# ወቅታዊ

## «ተባብረን ተደምረን በርከት ያሉ ሃላላ ኬላዎችን...

በርከት ያለ ህብር የሚታይባት አገር ናት- ኢትዮጵያ።

ከእኛ የሚጠበቀው ቋንቋ እና ባህል ለማወቅ የምንተጋውን ያክል ከባቢያችንን በወጉ ተረድተን አንዳንዱ ለቱሪዝም፣ አንዳንዱን ለእርሻ አንዳንዱን ደግሞ ለአትክልት መጠቀም ብንችል ያንን በመቀያየር የበለፀገች ያደገች አገር መፍጠር ይቻላል። ሰሞኑን እንደሰማችሁት አሳዛኝ በሆነ መንገድ በሃሳብ ብልጫ መሻታቸውን ብዙኃንን አሳምነው የሚፈልጉትን ነገር መከወን ሲችሉ፤ በዚያ መንገድ አይሳካልምን ብለው ያሰቡ ሰዎች ገና ሮጦ ያልጠገበ ወጣት ለሕዝቡ፣ ለአገሩ ብዙ ሊያገለግል የሚችል፤ ልጆችና ቤተሰቦች ያሉት በሰላም ቤተሰቡን ሊጠይቅ እየነዳ የሄደ ጀግና መሳይ ፈሪዎች ተደብቀው በጥይት ገደሉት።

ይህ ዓይነት ልምምድ ለኢትዮጵያ አደገኛ ነው። ኖርንበታል ከዚህ ቀደም። በቀይ ሽብር ነጭ ሽብር ያየነው ነገር ይህ ነው። አሁን ሰው ዝም ብሎ በመኪና ውስጥ እየሄደ ገድሎ በሰላም መኖር ይቻላል ብሎ ማሰብ ያስቸግራል። ሰው ገድሎ ስልጣን ማግኘት ይቻላል ብሎ ማሰብ ያስቸግራል። ጊዜው አንደዚህ አይደለም። 21ኛው ክፍለ ዘመን የሚጠይቀው አንደኛው ሃሳብ ማመንጨት ነው። ሃሳብ ለማመንጨት ደግሞ ምቹ ቦታ አለ። ጊዜ ወስዶ ማንበብና ማሰላሰል ይጠይቃል። ሃሳብ ካመነጩ በኋላ ያንን ሃሳብ ለብዙኃን መሸጥ ነው። የተሸጠው ሃሳብ ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ፤ ስልጣንም ሌሎች ፍላጎቶችም በሰላማዊ መንገድ ሊሳኩ ይችላሉ።

በመገዳደል፣ በመሰዳደብና በመናናቅ ልናሳካ የምንፈልገው የፖለቲካ ዓላማ የከሰረና ወደድል የማይወስድ ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ላይ የምትሳተፉ ባለሀብቶች፣ በውጭ ያላችሁ ኢትዮጵያውያን፣ በአገር ውስጥ ያላችሁ ወጣቶች ደጋግማችሁ እንድታስቡ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ። መንግሥት በዚህ መሰል ጉዳዮች ከዚህ ቀደም ያለውን አቋም ይደግማል፤ ሕግ የማስከበር ኃላፊነቱን ይወጣል። ይህንን በማደረግ ሂደት ውስጥ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተባባሪ እንዲሆን፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕግ ሥርዓት ሰላማዊነት፣ ልማታዊነት በኢትዮጵያ ወጣቶች ጭንቅላት ውስጥ እንዲያብብ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ በዚሁ አጋጣሚ አደራ ለማለት እወዳለሁ።

የግርማ የሺጥላ አለአግባብ መሰዋት ብልጽግናንእና ዓላማዎቻችንን የሚያቆም ሳይሆን ይበልጥ የሚያበረታ ነው። ብዙዎችን ሰውተን ነው የመጣነው። ሰማዕታት የምናስብበት የምንዘክርበት ልምምድ ያለን ስብስቦች ነን። ይህንን መሥዕዋትነት ይበልጥ ማስፈንጠሪያ እናደርገዋለን እንጂ አንሸማቀቅም፤ አንቆምም። ወደፊትም ይበልጥ ሰብሰብ ጠንከር እያልን ዓላማችን እናሳካላን። ዓላማችን ኢትዮጵያ ህብረብሔራዊት አገር ናት። የብዙ ብሔሮች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶች፣ የአለባበስና የአዘፋፈን ዘዬዎች ያሉባት ምድር ናት። እነዚህ ሕዝቦች ተከባብረው ተዋደው፣ ተደማምጠው ተደምረው ከሠሩ የበለጸገች አገር ለልጆቻቸው መተው ይችላሉ የሚል እምነት አለን።

እኔ ብቻ ለኢትዮጵያ በተለየ መንገድ አይተኬ ነኝ የሚል ፉርሽ የሆነ ሃሳብ፤ ከእንግዲህ በኋላ በኢትዮጵያ ምድር ላይ አይሠራም። ኢትዮጵያ የሁሉም ለሁሉም ከሁሉም የምትጠይቅ አገር ስለሆነች ተባብረን ተደምረን በርከት ያሉ ሃላላ ኬላዎች መሥራት አለብን፤ የተከበረች አገር እንድንፈጥር አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

በዚሁ አገጣሚ ኮሽ ባለ ቁጥር በኢትዮጵያ ውስጣዊ ጉዳይ እየገቡ መፈትፈት የሚፈልጉ ኃይሎች በተለይም ኢትዮጵያውያን ያልሆኑ ኃይሎች፤ ከድርጊታቸው እንዲሰበሰቡ እንዲቆጠቡ ለማሳሰብ እወዳለሁ። ኢትዮጵያን በማበጣበጥ በማባላት የሚገኝ ትርፍ እንደሌለ አውቀው፤ የእኛን ጉዳይ ለእኛ ትተው፤ በርከት ያለ ያልሠሩት ጉዳይ ስላላቸው ሥራዎቻቸውን መሥራት እንዲችሉ፤ የእኛን ጉዳይ ለእኛ እንዲተዉ ማሳሰብ እፈልጋለሁ።

ይበልጥ ጠንክረን፣ ይበልጥ በርትተን ይበልጥ ተሳስረን ኢትዮጵያን ለማበልጸግና የተሻለች አገር ለልጆቻችን ለመተው እንጥራለን። ሕዝባችን ዛሬም እንደትናንቱ ከጎናችን እንዲሆን አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

በመጨረሻም የዳውሮ ዞን፣ የደቡብ ምዕራብ



ዶክተር ነጋሽ ወጊሾ



የዳውሮ አባት

ኢትዮጵያ እዚህ አካባቢ ያላችሁ ወጣቶች የሃላላ ኬላን አጥር እንደጠበቃችሁት ሁሉ ይህን ሪዞርት ጠብቃችሁ እንግዶች ተቀብላችሁ፤ አስፋፍታችሁ ባህላችሁን ታሪካችሁን ማንነታችሁን የምታስተዋውቁበት መድረክ አድርጋችሁ እንድትጠቀሙበት። ይህ ስፍራ ከዛሬ ጀምሮ የእናንተ ሀብት ስለሆነ በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት እንድትጠብቁት አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

በዚህ ስፍራ በጣም በርካታ ሰዎች በብዙ መንገድ ተሳትፈዋል። ከመንግሥት ሥራውን በኃላፊነት ተቀብሎ በርከት ያሉ ሙያተኞችን አሰማርቶ፤ ጊዜውን ሰውቶ ይህን ሥፍራ እንደዚህ አድርጎ እንዲሠራ አመራር የሰጠውን ኢንጅነር ሃብታሙ ተገኝን እጅግ ከፍ ያለ ምስጋና እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ። ሃብታሙ እና ከሃብታሙ ጋር የሠራችሁ ወጣት ኢንጅነሮች፤ ይህ የመጀመሪያችን ነው። ይህ በጣም ዝቅተኛው ስታንዳርዳችን ነው። ኢትዮጵያ ከዚህ በላይ በርከት ያለ ሰፊ ፅዱ ስፍራ ያስፈልጋታል። ለሚቀጥለው ሥራ ራሳችሁን ማዘጋጀት አለባችሁ። የሚያረካ ጅምር ነው፤ የጀመርነው፤ በጅምር እንዳንቆም ለሚቀጥለው ሥራ ራሳችንን እንድናዘጋጅ አደራ እላለሁ።

ወደ ዳውሮ እንድንመጣ፤ የዳውሮን ባህል እንድናውቅ፤ ዳውሮን እንድናስታውስ በተደጋጋሚ የሚጮሁ፣ ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ዳውሮ ዳውሮ እያሉ የሚጮሁ አንድ አባትን እጋብዛለሁ።

### ዳውሮ እንዲታወስ በየመድረኩ የሚናገሩ የነበሩ የዳውሮ አባት መልዕክት፤

እንዳከበሩኝ ፈጣሪ ወደፊትም በሰማይ፤ አሁንም በምድር ያክብርዎ፤ እግዚአብሔር ይስጥልኝ። እንዲያው አልቅሼ አልቅሼ እዚህ አድርሼ በመጨረሻ ደስታዬን ሳልተነፍስ ይሄዱ ይሆን ወይ?! ብዬ ሳምጥ ነው ጠቅላይ ሚኒስትሩ የጠሩኝ፤ ፈጣሪ በመልካም ይይዎት፤ አመሰግናለሁ።

እኔ እንዴት እንደማስረዳ አላውቅም። እድሜዬን እንደምታዩት ነው፤ አማርኛውም ሁለተኛ ሦስተኛ ቋንቋዬ ነው። ይህንን ውብና ግዙፍ የሆነን ነገር፤ ይህንን ተዓምራዊ የእግዚአብሔር ሥራ እንጂ የሰዎች የማይመስለውን ጉዳይ ፈጻሚዎቹንና የሠሩትን ሰዎች ራሳቸውን ጠቅላይ ሚኒስትሩን እንዴት እንደማመሰግን አላውቅም፤ በጣም ይጨንቀኛል።

ለማንኛውም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ክብርት ልጄ ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው፣ የየክልሉ ርዕሰ መስተዳድራን፣ ሚኒስትሮች፣ ትልልቅ ኃላፊነት ላይ ያላችሁ ሰዎች ሁሉ ቅደም ተከተሉን አትጠብቁና ሁላችሁም ለዚህ ምረቃ እንኳን በቃችሁ። እንኳን ደህና መጣችሁ እላለሁ።

በዚህ ዘመን ምስጋና የሚባለውን ቃል ‹በርታ› የሚለው ቃል፣ ‹ጎሽ› የሚለውን ቃል መስማት ብዙም አይጠበቅም፤ እንዲያውም አይባልም። ‹ቶሸሸ...›ነው ከጎሸ....ይልቅ፤ ‹ጎሽ› በዱር ያለው የበሬ ዓይነት ሳይሆን ማበረታቻ የአማርኛ ቃል ነው። ጎሽ! በዚህ ቀጥል! እደግ፤ የእኔ ልጅ! አሁን ይህቺን ብትጨምር ከፍ ትላለህ። ከፍ ታደርጋለህ ማለት ነው ጎሽ። ምስጋናም ነው ጎሽ።

ቶሸሸ...ያዝ አድርገው እንጂ... ተው እንጂ....ሰባራ ነው...ጠማማ ነው...ወደፊት እንዳይሄድ ማድረጊያ ጊዜ ነው። ምን ቢደረግ ምን ቢደረግ እርካታ የጎደለበት ጊዜ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ብዙ ነገር 2012 ዓ.ም ላይ ከተነጋገርን በኋላ ኑ! ብያለሁ። ኑ! እዩን። እኛ ጋር መምጣት ሁለት ትርጉም አለው። እኛም ረድኤት፣ በረከትና ሀብት እናገኛለን። እርስዎም በእኛ ተመርቀው ከሄዱ ደግሞ እንደዛ ዓይነት ትልቅ ነገር ያገኛሉ ኑ! ብያለሁ። ‹ፈረንጅ አገር ሥራ አለብኝ፤ አውሮፓ እወጣለሁ፤ የዚህ አገር ጉዳይም አስጨንቆኛል› አላሉም። ጥር 12 ቀን የተነጋገርነውን አንድ ወር ከ14 ቀን የካቲት 28 ላይ በዛ ወር ዳውሮ ከች አሉ።

እንደተባለው ይኸው መሪ አንድን አገር ሲጎበኝ ጸጋ ነው፤ በረከት ነው፤ ሀብት ነው፤ ሲሳይ ነው ያልኩትን ጉድ ተመልከቱ። ሆነ እኮ! ይህ ሲሳይ ነው፤ ይህ ሀብት ነው እኮ፤ የጠየቅኳቸው ዕለት ኑ! ብዬ ስነግራቸው ከእኔ ከባለቤቱ፣ ከእኔ ከተወላጁ ስለዳውሮ እና ኮንታ አንድ እና አንድ መሆኑን አሳምረው ስለሚያውቁ የጠራኋቸው የላከኝ የዳውሮ ሕዝብ ነው ብያለሁ። አልነገርኳቸውም ስለኮንታ፤ የኮንታ ልጆችም ከእኔ ጋር እዛ ቤተ መንግሥት አዳራሽ የነበሩ አላነሱም። እዬዬ ብዬ አልቅሼ የጠራኋቸው እኔ ነኝ። አንድ መሆናቸውን ስለሚያውቁ አስበው አሰላስለው ተርጫ ላይ ከተገናኘን በኋላ «ፓይለት! አቤት! ንዳው ወደኮይሻ» ብለው ወደ ኮንታ ሔዱ። ልብ አድርጉ ይህንን ችሎታ እግዚአብሔር አሁንም ይባርክልዎ። ከዛ ተጀምሮ ኮይሻ ፕሮጀክት አለ፤ ሃላላ ክላስተር አለ፤ ይኸው ሥራ ተሠራ። ትንሽ ነገር የምናገረው እንደ እነሞሶፖታሚያ፣ እንደ እነግብጽ ፒራሚድ፣ እነ ቻይና ያሉ ስልጣኔዎች ጋር የእኛ ሃላላ እኩል ሥራ የሰራ ነው የሚመስለኝ። ሰባት በሮች ሁለት ሁለት ወታደሮች ይቆሙ የነበሩም የሉም። ሃላላም የሉም። ሥርዓተ መንግሥቱም የለም፤ ጫካ ወርሶታል፤ ኬላው ግን ይታዘባል ተኝቶ። ጫካ ለብሶ፤ ውስጡ ቁም ነገር አለው። እዛ ቁም ነገር... ሃላላ ላይ፤ ሌላው ኢትዮጵያዊ የሃላላ ልጅ መጥቶ... ሃላላ ጥሎት በነበረው መሠረት ላይ ይህንን ፎቅ ማሳየቱ አውሮፓ ነው የወጣነው ያሰኛልና ተባረክ አሁንም የእኔ ጌታ እላለሁ። ተባረኩ እግዚአብሔር ይስጥልኝ።

### የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ምክትል ርዕሰመስተዳድር ዶክተር ነጋሽ ወጊሾ መልዕክት እንደበት፤

በአገራችን ኢትዮጵያ ለውጡን ተከትለው የመጡ አዳጊና አዳዲስ ፍላጎቶችን ለማስተናገድ በሚደረገው ጥረት ለአገራችን ሰላምና ለሕዝቦቿ አንድነት እንዲሁም ዘላቂ ሰላም ለማስፈን በተለይም የሰሜኑ ጦርነት በሰላም እንዲቋጭ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትርና መንግሥታችን የወሰዱት ታላቅ ርምጃ መላው የክልላችን ሕዝቦች በፍጹም ደስታ የተቀበሉት ነው። በመሆኑ በዚህ ሰላም እረፍት እንድናገኝ ዕድል ስለሰጡንና በር ስለከፈቱልን በክልሉ መንግሥትና ሕዝብ ስም የተሰማኝን ደስታ በዚሁ አጋጣሚ ለመግለጽ እወዳለሁ። ሁላችንንም ለዚህ የሰላም ጊዜ እና የሰላም ዘመን እንዲሁም የሰላም ቀን ስላደረሰን ፈጣሪን ከልብ አመሰግናለሁ።

በመቀጠልም ተፈጥሮ በርካታ ገጸ በረከቶቹን በለገሳት፣ ነዋሪዎቿም በሥራ ትጋታቸውም በሚታወቁባት እና የአያቶቹንና የቅድመ አያቶቹን ቅርስ ለዘመናት ጠብቀው ባቆዩት ምድር ይህን ለዘመናት የቆየውን ታሪክ እንድናስታውሰውና እንድንዘክረው ሐሳብ ጠንሰሰው፣ የዲዛይን ኮንሰፕት አዘጋጅተውና እና ለግንባታ የሚውል ሀብት አሰባስበው በደቡብ ምዕራብ ሕዝቦች ክልል በዳውሮ ዞን የገበታ ለአገር ኮይሻ ሃላላ ፕሮጀክት አካል የሆነውን የሃላላ ሪዞርት ወይም የሃላላ ሎጅ እንዲህ ባማረ ሁኔታ ለምረቃ እንዲበቃ በማድረግዎ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ለሕዝባችን ላበረከቱት የማይነጥፍ አሻራ በራሴና በመላ የክልላችን ሕዝብ ስም እንዳመሰግንዎ ይፈቀድልኝ። ሁላችንንም እንኳን ደስ ያለን፤ እንኳን ደስ ያላችሁ ለማለት እወዳለሁ።

የሃላላ ሪዞርት የ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የጥንታዊ የዳውሮ ነገሥታት ከሕዝባቸው ጋር በአንድነት ሆነው የግዛት አንድነታቸውን እንዴት ማስከበር እንደቻሉ እና ለአሁኑ ትውልድ እንዳስተላለፉ ሕያው ምስክር በሆነው የአንድ ሺ 200 ኪሎ ሜትር ርዝመት እና የስድስት ሜትር ከፍታ ያለው የሃላላ ኬላ ወይም የሃላላ ግንብ ባለበት ስፍራ መገንባቱ ከምንም በላይ የዘመናት ዕድሜ ይዞ ትኩረት የተነፈገው የዳውሮ ሕዝብ ታሪክ ዳግም እንዲታደስ በር የከፈተ ነው።

ሌላው ሎጁን ለየት የሚያደርገው የአገራችን ትልቁ የኃይል ማመንጫ ግድብ እና ሰው ሰራሽ ሐይቅ የሆነው ግቤ ሦስት ግድብ እና ሐይቅ የሚገኝበት አካባቢ በመሆኑ ልዩ ውበት ያጎናጽፈዋል። ከዚህም በተጨማሪ በቅርቡ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በተፈጠረው ጦርነት እና ግጭት ምክንያት ይህንን ወደሰላማዊ መንገድ ለማምጣት ከፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ቀጥሎ በዚህ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ዳውሮ ዞን ሃላላ መንግሥታችን እና የሕወሓት ኃይሎች በጋራ ሰፊ ምክክር በማድረግ ይህን ሰላም የበለጠ እንዲጸና ያደረጉበት ስለሆነ ይህም አንዱ እና ትልቁ ታሪካዊ ያደርገዋል። በዚህም አጋጣሚ ወንድማችን አቶ ጌታቸው ረዳ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጊዜያዊ አስተዳደር በመካከላችን ከእኛ ጋር ሆነው ሲያከብሩ ስናይ ፍጹም ደስታ ይሰማናልናል፤ ይህም ታሪካዊ ቦታ ነው ማለት ነው።

በዞኑ እና አጎራባች ዞኖች መካከል በተለይ ይህ ትልቁ የቱሪዝም ማዕከል በመሆን የቱሪዝም ፍሰትን በማሳለጥ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን በማፋጠን የሚጫወተው ሚና በጣም የጎላ ነው። በክልላችን የኮይሻ ገበታ ለአገር ፕሮጀክት በተለይ በኮንታ ዞን እና አካባቢ የሚሠሩ ሥራዎች ሲጠናቀቁ እንዲሁም ደግሞ በቅርቡ የታሰበው በቤንች ሸኮ ዞን ሚዛን አማን ከተማ የሚገነባው የደንቢ ቱሪስት መዳረሻ እንዲሁ ሲጠናቀቅ ክልሉን በማስተሳሰር ዓይነተኛ ሚና ይጫወታል። ስለሆነም ፕሮጀክቱ የታቀደለትን ዓላማ እንዲያሳካ የክልላችን መንግሥት ተገቢውን ድጋፍ እና ክትትል የሚሰጥ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ለማረጋገጥ እወዳለሁ።

በመጨረሻም በዚህ ሒደት ውስጥ አንድ የተማርነው ትልቅ ትምህርት ፕሮጀክትን እንዴት በጊዜ ማጠናቀቅ እንደሚቻል፣ ሐሳብ እንዴት ማመንጨት እንደሚቻል እና ሐሳቡን ወደ መሬት እንዴት ማውረድ እንደሚቻል እንደሁ መሬት ወርዶም ደግሞ በሚፈለገው ጥራት እና ብቃት እንዴት ጊዜ ጠብቆ ማጠናቀቅ እንደሚቻል ከዚህ አንድ ትልቅ ነገር የተማርንበት ነውና ምናልባት እነዚህ ኮይሻ ሃላላም ገበታ ለአገርም የወንጂም ሆነ የጎርጎራም ሌሎቹም ትልልቅ ፕሮጀክቶች አዲስ አበባ እና አካባቢው ያሉትን ስናያቸው ከእነሱ የምንማረው ምናልባት የምህንድስና ዘርፋችን፣ የፕሮጀክት ግንባታ ሥርዓታችንን መለስ ብለን እንድንቃኝ እና በዛ ዓይነት መንገድ ራሳችንን እያስተካከልን እኛ የምንመራውንም አካባቢ ክልልም በዛ ደረጃ እንድንቃኝ እድል የሚፈጥር ስለሆነ ከዚህ ትልቅ ትምህርት የወሰድኩ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ ነው። እግዚአብሔር ይስጥልኝ፤ አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## አገራዊ የኢንቨስትመንት አቅም የተዋወቀበት መድረክ

አንተነህ ቸሬ

ኢትዮጵያ በኢንቨስትመንት ዘርፍ ከፍተኛ እድገት ካስመዘገቡ አገራት መካከል ተጠቃሽ ሆና ቆይታለች። በአገሪቱ ሰፍኖ የቆየው ሰላምና መረጋጋት፣ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ መፋጠን፣ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች፣ እምቅ የተፈጥሮ ሃብት እና ሰፊ የገበያ እድል አገሪቱ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ በአፍሪካ ደረጃ ቀዳሚ ከሚባሉ አገራት መካከል አንዷ እንድትሆን አስችለዋታል። ይህም ለኢንቨስትመንት ዘርፍ ማደግ ዓይነተኛ ሚና የተጫወተ ሲሆን፣ ለአገሪቱ ምጣኔ ሀብት እድገትም ትልቅ ድርሻ አበርክቷል።

ይሁን እንጂ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የተፈጠሩት የፀጥታ ችግሮች በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተፈጠረው የኮቪድ ወረርሽኝ፣ የምጣኔ ሀብት ቀውስና ጦርነቶች ጋር ተዳምረው በአገሪቱ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድረዋል።

ከጦርነት በኋላ በሚኖር የኢንቨስትመንት አስተዳደርና አመራር ብቻም ሳይሆን በሰላም ጊዜም ቢሆን የኢንቨስትመንት አቅሞችንና አማራጮችን በማስተዋወቅ ባለሀብቶችን መሳብና ዘርፉን ማሳደግ ይገባል። ይህን ጥረት እውን ለማድረግ ደግሞ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ባለድርሻ አካላትን የሚያገናኙ፣ የኢንቨስትመንት አቅሞችንና አማራጮችን የሚያስተዋውቁ መድረኮች ከፍተኛ ሚና አላቸው። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያን የኢንቨስትመንት አቅም ለባለሀብቶች ማስተዋወቅን ዓላማ ያደረጉ ልዩ ልዩ መድረኮች መካሄዳቸው ይታወሳል። እነዚህ መድረኮችም ቀላል የማይባሉ ውጤቶችን አስገኝተዋል።

የኢትዮጵያን የኢንቨስትመንት አማራጮች በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስተዋወቅ በሕግ ስልጣን የተሰጠው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ከሌሎች አጋር የመንግሥት አካላት ጋር፣ በተለይም ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በውጭ ከሚገኙ የዲፕሎማቲክ ሚሽኖች ጋር በመተባበር ያዘጋጀው ‹‹ኢንቨስት ኢትዮጵያ›› (Invest Ethiopia 2023) የተሰኘው የኢንቨስትመንት ፎረም ባለፈው ሳምንት፣ /ከሚያዝያ 18 እስከ ሚያዝያ 20 ቀን 2015 ዓ.ም/ በአዲስ አበባ ተካሂዷል። ፎረሙ የአገሪቱን የኢንቨስትመንት አቅሞችና በዘርፉ ያሉ መልካም እድሎችን ለማስተዋወቅ አልሞ የተካሄደ ሲሆን ባለሀብቶች፣ የመንግሥትና የተቋማት የሥራ ኃላፊዎች፣ የፖሊሲ ባለሙያዎችና ሌሎች የኢንቨስትመንት ዘርፍ ባለድርሻ አካላት ተሳትፈውበታል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት በኢንቨስትመንት ዘርፍ የተከናወኑ የአሰራር ማሻሻያዎች በኮቪድ ወረርሽኝ እና በግጭቶች ምክንያት በስፋት ሳይተዋወቁ ቆይተዋል። ከአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ትግበራ ጋር ተያይዞ ኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት መዳረሻ እንድትሆን የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችና መወዳደሪያ ነጥቦች አሉ። ባለፉት ዓመታት ከ80 በላይ ለቢዝነስና ኢንቨስትመንት ስራ ማነቆ የነበሩ ህግጋት ተሻሽለዋል። ከእነዚህም መካከል ወደ ስራ የገቡት አዳዲሶቹ የኢንቨስትመንት ፖሊሲና የኢንቨስትመንት አዋጅ (1180/2012) ተጠቃሽ ናቸው።

አዳዲሶቹ ህግጋት ለኢንቨስትመንት ምቹ ከባቢ የሚፈጥሩ ቢሆኑም ለግል ባለሀብቶች በሚፈለገው ልክ ማስተዋወቅ ሳይቻል ቆይቷል። ፎረሙ እነዚህን ማሻሻያዎች ለማስተዋወቅም እድል ፈጥሯል። በአጠቃላይ ፎረሙ በኢኮኖሚ ማሻሻያው ይፋ የተደረጉ ለውጦችን እንዲሁም ባለፉት ዓመታት የተተገበሩት የኢንቨስትመንት ከባቢ ማስተካከያ ስራዎች ያመጧቸው መሰረታዊ የህግና የአሰራር ለውጦች የተዋወቁበት መድረክ ሆኗል።

ፎረሙ ቀደም ሲል በኢንቨስትመንት ላይ ተሰማርተው የቆዩ ባለሀብቶች ስራቸውን በማስፋት አዳዲስ የኢንቨስትመንት አማራጮችን እንዲመለከቱ የሚያስችል ከመሆኑም ባሻገር ባለሀብቶቹ ከፖሊሲ አውጪዎችና ውሳኔ ሰጪ የመንግሥት አካላት ጋር በነበሯቸው ግንኙነቶች ስለሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶች በቅርበት ለመወያየትም እድል ፈጥሯል።



በመድረኩ የተለያዩ ስምምነቶች ተፈርመዋል

በፎረሙ ሚኒስትሮችና ሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣናት በተገኙበት የተካሄዱ ከፍተኛ የፓናል ውይይቶችን (High Level Panel Discussions) ጨምሮ፣ የቢዝነስ ተቋማት እርስ በእርሳቸውና ከመንግሥት አካላት ጋር የተገናኙባቸው የኢንቨስትመንት አማራጭ ማስተዋወቂያ እና የልምድ ልውውጥ መድረኮች፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ጉብኝቶች፣ ኤግዚቢሽኖችና ተዛማጅ መርሃ ግብሮች ተካሂደዋል። በዓለም አቀፍ ደረጃ ስመጥር የሆኑ የቢዝነስ ተቋማት ስራ አስፈፃሚዎችም ልምዳቸውን አካፍለዋል።

ከወሳኝ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና ከዚህ ቀደም ከኮሚሽኑ ጋር ግንኙነት ከነበራቸው አካላት ጋር የመግባቢያ ስምምነቶችና የኢንቨስትመንት ውሎች ተፈርመዋል። ለአብነትም ኮሚሽኑ ከአንድ ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ዶላር በላይ የኢንቨስትመንት ስምምነት ከአምስት ኩባንያዎች ጋር ተፈራርሟል። የ‹‹ቱሉ ካፒ›› የወርቅ ልማት ፕሮጀክትን የሚያከናውነው ‹‹ከፊ ሚኒራልስ›› (KEFI Gold and Copper) ኩባንያ ‹‹ፒ ደብሊው ማይኒንግ›› (PW Mining) ከተባለው ድርጅት ጋር በጋራ ለመስራት የተፈራረመው ስምምነትም የዚሁ ማሳያ ነው።

የኢፌዴሪ የገንዘብ ሚኒስትር አቶ አህመድ ሺዴ ፎረሙ አገራዊ ምጣኔ ሀብቱ ካጋጠሙት ውጫዊና ውስጣዊ ተግዳሮቶች እየወጣ ባለበት ወቅት መዘጋጀቱ ፋይዳውን የጎላ እንደሚያደርገው ተናግረዋል። እርሳቸው እንዳሉት፣ ባለፉት አራት ዓመታት መንግሥት ዘርፈ ብዙ የምጣኔ ሀብት ማሻሻያ መርሃ ግብሮችን ተግባራዊ አድርጓል። ከእነዚህ መርሃ ግብሮች መካከል አንዱ አምራች የሆነውን የሠው ኃይል የሚሸከም የሥራ እድል እና የተረጋጋ የማክሮ-ኢኮኖሚ ከባቢ በመፍጠር እንዲሁም የግል ዘርፍ መር (Private Sector-Led) የሆነ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በመገንባት ዘላቂና ፈጣን የምጣኔ ሀብት እድገት ማስመዝገብን ዓላማው ያደረገው አገር በቀል የምጣኔ ሀብት ማሻሻያ መርሃ ግብር (Home-grown Economic Reform Program) ነው።

ከዚህ በተጨማሪም የኢንቨስትመንት አዋጅና የንግድ ሕግ ማሻሻያዎች፣ ብሔራዊ የንግድና ቢዝነስ ስራ አመቺነት ማሻሻያ መርሃ ግብር (National Ease of Doing Business Initiative) እንዲሁም ከዓለም አቀፍ የግብይት ስርዓት ጋር ዘመናዊ ትስስር ለመፍጠር የፋይናንስ ዘርፉ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት እንዲሆን የተላለፈውን ውሳኔ ለመተግበር እየተደረጉ ያሉ ዝግጅቶች የምጣኔ ሀብት ማሻሻያ መርሃ ግብሩ አካል ናቸው።

‹‹ኢትዮጵያ ፈጣን እድገት እያስመዘገበች ነው። በአፍሪካ ለኢንቨስትመንት ምቹ ከሆኑ አገራት መካከል አንዷ ሆናለች። በአገሪቱ በርካታ የኢንቨስትመንት እድሎች አሉ። የኢኮኖሚ ፖሊሲዎቿ አሳታፊና አካታች እንዲሆኑ መንግሥት ጠንካራ ሥራ እየሠራ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተደረጉ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት ጨምሯል። ኢትዮጵያ ላይ ኢንቨስት ማድረግ ማለት በአፍሪካ ኢንቨስት ማድረግ ነው›› ብለዋል። የኢትዮጵያ መንግሥት ለግሉ ዘርፍ የሰጠውን ትኩረት በአግባቡ በመጠቀም ባለሀብቶች በኢትዮጵያ በስፋት በኢንቨስት ስራዎች ላይ ቢሰማሩ ተጠቃሚ እንደሚሆኑና መንግሥትም አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር ወይዘሮ ሌሊሴ ነሜ በበኩላቸው ኢትዮጵያ እያስመዘገበች ያለችው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት መንግሥት ለኢንቨስትመንት ዘርፍ የሰጠው ትኩረት ውጤት መሆኑን ገልፀዋል። ኮሚሽነሯ እንደተናገሩት፣ የኢንቨስትመንት ዘርፉን ለማሳደግ መንግሥት በርካታ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን አድርጓል፤ ዘርፉ በአገራዊ ምጣኔ ሀብት እድገት ላይ የሚኖረውን ሚና ለማሳደግ ቀዳሚ ትኩረት የተሰጣቸውን ዘርፎች ለይቷል። በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች በመንግሥት የተገነቡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ለኢንቨስተሮች የተሟሉ መሰረተ ልማቶችንና ማበረታቻዎችን በማቅረብ የኢንቨስትመንት ፍሰቱ እንዲጨምር ከፍተኛ አስተዋፅዖ እያበረከቱ ይገኛሉ። የምርቶችን የእሴት ሰንሰለት በማጠንከር የምርት መጠንን ለማሳደግና በወሳኝ የምጣኔ ሀብት ዘርፎች ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት ፓርኮቹን የማስፋፋትና የማዘመን ተግባራት ይከናወናል።

አገሪቱ በታዳሽ የኃይል ምንጭ ዘርፍ ልማት እያከናወነች ያለችው ተግባር ለኢንቨስትመንት ተግባራት አስተማማኝ የኃይል ምንጭ ለማቅረብ የሚያሥችል ነው። በኢንቨስትመንት ዘርፍ የተደረጉ የሕግ ማሻሻያዎች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ለመሳተፍ የሚፈልጉ ባለሀብቶች ቁጥር እንዲጨምር ያስችላሉ። የኢንቨስትመንት ፍሰቱን ፈጣንና ቀልጣፋ ለማድረግ ከተከናወኑ የሕግና መዋቅራዊ ማሻሻያዎች በተጨማሪ ኮሚሽኑ አሰራሩን ማዘመኑንም ወይዘሮ ሌሊሴ ገልፀዋል።

በፎረሙ ላይ ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች የየአካባቢዎቻቸውን የኢንቨስትመንት አቅሞችና እድሎች አስተዋውቀዋል። ለወቅቱ የሚመጥን ዘመናዊ የኢንቨስትመንት አመራርና አስተዳደር በማስፈን የኢንቨስትመንት ፍሰቱን ፈጣንና ቀልጣፋ ለማድረግ እያከናወኗቸው ስለሚገኙ ተግባራትም ገለፃ አድርገዋል።

በደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣ ፕሮሞሽን፣ መረጃና ዳያስፖራ ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ፀጋዬ ዘለቀ ፎረሙ የክልሉን የኢንቨስትመንት አቅም ለባለሀብቶች ለማስተዋወቅ እድል የፈጠረ እንደነበር ሲናገሩ፤ ‹‹የክልሉን የኢንቨስትመንት እድሎች ለባለሀብቶች አስተዋውቀናል። ክልሉ ለግብርና፣ ለማምረቻና ለአገልግሎት ዘርፎች ምቹ እንደሆነ ገለፃ አድርገናል። ከግብርናና ማምረቻ ዘርፎች በተጨማሪ ክልሉ አስደናቂ የሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶችና የብዝኃነት ባለቤት በመሆኑ ለቱሪዝም ኢንቨስትመንት የተመቸ እንደሆነ ማብራሪያ ሰጥተናል ሲሉ ገልጸዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ባለሀብቶች ለኢንቨስትመንት ወደ ክልሉ ሲመጡ ማሟላት የሚጠበቅባቸውን መስፈርቶችና ግብዓቶች ምን እንደሆኑ እንዲሁም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ይዘው እንዲመጡ ነግረናቸዋል›› ብለዋል። ‹‹ያለግል ባለሀብቶች ተሳትፎ ዘላቂ ልማትን ማሳካት አይቻልም›› የሚሉት አቶ ፀጋዬ፣ ኢንቨስትመንት የብዙ ተቋማትን ትብብርና ቅንጅት የሚጠይቅ በመሆኑ የክልሉ የኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ እያንዳንዱ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር ለባለሀብቶች ጥያቄዎች ምላሽ እየሰጠ እንደሚገኝም ገልፀዋል።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመሬትና ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ አቶ አመንቴ ገሺ ፎረሙ የኢንቨስትመንት ባለድርሻ አካላትን ያገናኘ መሆኑን ጠቅሰው፣ የኢንቨስትመንት አቅሞችን ለማስተዋወቅ እድል የሚፈጥር ከመሆኑም በተጨማሪ የዘርፉን ችግሮች በትብብር ለመፍታት የሚያግዝ እንደሆነም ገልፀዋል።

እርሳቸው እንዳሉት፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል እምቅ ሀብትና ሰፊ የኢንቨስትመንት አማራጮች ያሉት በመሆኑ ፎረሙ የክልሉን የኢንቨስትመንት ዘርፍ ለማሳደግ አወንታዊ ሚና ይኖረዋል። ክልሉ በግብርና፣ በማምረቻ፣ በማዕድናት (የድንጋይ ከሰል፣ ወርቅ፣ እምነበረድ፣ ግራናይት) እና በሆቴልና ቱሪዝም መስኮች በርካታ የኢንቨስትመንት አማራጮች አሉት።

አቶ አመንቴ በክልሉ ለኢንቨስትመንት ሊተላለፍ የሚችል ከ69ሺ ሄክታር በላይ ለም መሬት እንዳለ ጠቅሰው፣ የዓባይ ግድብ ለክልሉ ተጨማሪ የኢንቨስትመንት እድሎችን እንደሚያመጣ ይጠበቃል ሲሉም ገልጸዋል። ‹‹የክልሉ መንግሥት በሀብት አጠቃቀም ላይ ጠንካራ የሪፎርም ስራዎችን ሰርቷል። መሬት ወስደው ወደ ስራ ካልገቡ ባለሀብቶች መሬቱ ተወስዶ ማልማት ለሚችሉ ባለሀብቶች ተሰጥቷል። ቢሮክራሲው በሚፈለገው ልክ አጥጋቢና የተሳለጠ ነው ባይባልም ብዙ መሻሻሎች አሉ›› በማለት ገልፀዋል። ከዚህ በተጨማሪም ‹‹የፀጥታ ችግር ተቀርፏል። በአሁኑ ወቅት የፀጥታ ጉዳይ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ችግር አይደለም›› በማለት በክልሉ ተከስቶ የነበረው የሰላም መደፍረስ ተወግዶ መረጋጋት መስፈኑንም አቶ አመንቴ ተናግረዋል።

የትግራይ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ዳንኤል መኮንን በበኩላቸው ፎረሙ በሰሜኑ ጦርነት የተጎዳውን የትግራይ ክልል የኢንቨስትመንት ዘርፍ ለማነቃቃት አወንታዊ ሚና እንደሚኖረው ጠቁመዋል። እርሳቸው እንዳሉት፣ በሰሜን ኢትዮጵያ የነበረው ጦርነት የክልሉን ኢንቨስትመንት ስለጎዳው ዘርፉን ማነቃቃትና መልሶ መገንባት ይገባል። የወደመውን ሀብት መልሶ ለመገንባት ባለሀብቱ ትልቅ ሚና አለው። ኮሚሽነሩ፣ ‹‹ኢንቨስትመንት ሰላም፣ መሰረተ ልማት፣ ፋይናንስና የገበያ ትስስር ይፈልጋል። ትግራይ ክልል በበርካታ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ከፍተኛ አቅም ያለው ክልል ነው። መሰል ፎረሞችን በክልሉ በማዘጋጀት የተጎዳውን ኢንቨስትመንት ማነቃቃት ይገባል ብለዋል።

ለወቅታዊው ሁኔታ የሚመጥን የኢንቨስትመንት አስተዳደር እውን ለማድረግ የሕግ ማሻሻያ ስራዎችን እየሰራን እንገኛለን ሲሉም ጠቅሰው፣ የኢንቨስትመንት ዘርፉን ለማነቃቃት ለሰራተኞቻችን ስልጠናዎችን እየሰጠን ነው›› ይላሉ።

አቶ ዳንኤል ከጦርነቱ በፊት በክልሉ ከ13ሺ በላይ ፈቃድ የወሰዱና የተመዘገቡ ኢንቨስተሮች እንደነበሩ አስታውሰው፣ እነዚህ ባለሀብቶች ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ ተመልሰው ለመምጣት ፍላጎት እያሳዩ መሆናቸውንም አስታውቀዋል፤ ሌሎች ባለሀብቶችም ወደ ስራቸው እንዲመለሱ ልዩ እገዛ ሊደረግላቸው እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

# የቆሞቀር አስተሳሰብ መወገድ - ለኢትዮጵያ ሰላም

**ሙሉቀን ታደገ**

ለብዙ ወራት ተሰውሮ የነበረው ወፈፌው ይልቃል አዲሴ ከዚህ ቀደም በተለየ መልኩ በተከታተይ ቀናት ሰማይ የአህያ ሆድ ሲመስል እየተነሳ በሰፈራችን ከሚገኘው ዋርካ ስር ቆሞ መጮሁን አብዝቷል። ዛሬም እንደ ወትሮው ሁሉ እየጮኸ ነው። ሰዓቱ የሰፈራችን ሰዎች ወደ «በተስኪያን» የሚሄዱበት ነው። ይሁንና የዛሬው የይልቃል አዲሴ ጩኸት ከዚህ ቀደሙ የተለየ በመሆኑ በሰፈራችን የሚገኝ ማንኛውም ሰው ከህጻን እስከ አዋቂ «በተስኪያን» መሄዱን ትቶ ይልቃል አዲሴ ወደሚጮህበት ዋርካ ተሰበሰበ። ሰዎች በመሰባሰብ ላይ እያሉ ይልቃል አዲሴም በተደጋጋሚ «ከርሞ ጥጃ፤ ከርሞ ጥጃ፤ ከርሞ ጥጃ» እያለ ይጮህ ነበር።

የሰፈራችን ሰዎች ወደ ዋርካው ተሰባስበው ቦታ ቦታቸውን መያዛቸውን ከተመለከተ በኋላ ይልቃል አዲሴ ራሱን ለንግግር እያዘጋጀ እህ..እህ...ብሎ ጉሮሮውን ጠራረገ። ንግሩንም እንዲህ ሲል ጀመረ፤... ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ዓለማችን ሁሉም ነገሯ በፍጥነት ሲለዋወጡ እየተመለከትን ነው። ዛሬ ላይ አዲስ ሆነው ያየናቸው ኩነቶች ከሳምንት በኋላ ያለፈባቸውና አሮጌ ሆነው እናገኛቸዋለን። ዛሬ ላይ የተሰራ ድንቅ ስራ ከወር በኋላ በአዲስ ተተክቶ ይቀርባል። ይህ አካሄድ የዚህ ዘመን ሁነኛ መገለጫ ነው።

ፖለቲካውም በዚሁ ልክ ሆኗል። ትናንት ላይ የነበሩ ዓለምን ያሳጨበጨቡ አስተሳሰቦችና መላው የዓለም ህዝብ የገዛቸው ሃሳቦች ዛሬ ላይ አርጅተው ተጥለው በአዲስ ሲተኩ እየተመለከትን ነው።

ለምሳሌ ትናንት በወታደራዊ መንግስት ሲተዳደሩ ነበሩ አገራት ዛሬ ላይ ሁሉ ነገራቸውን ጥለው ወደ አዲስ ምዕራፍ ተሸጋግረዋል። ትናንት ላይ በስፋት ሲስተዋል የነበረ የፓርቲ አመሰራረት ዛሬ ካለው ፈጽሞ የተለየ ነው። ዛሬ ላይ ፓርቲዎች የሚታገሉበትና ህዝብን የሚያታግሉበትም ስልት ከትናንትናው ፈጽሞ የተለየ ነው። ትናንት ላይ ሲንጸባረቁ የነበሩ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለሞች ዛሬ የሉም፤ በአዲስ ተተክተዋል። በአጠቃላይ ትናንት የነበሩ በርካታ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ኩነቶች ዛሬ ላይ የሉም ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ይሁን እንጂ በእኛ አገር የሚገኙ በርካታ ፖለቲከኛ ነን ባይ ወገኖች ግን የአገራቸውን ነባራዊ ሁኔታ ምኑንም ሳያገናዝቡ ትናንት ከእነ ማርክስ እና ሌኒን እንደወረደ የተዋሱትን ንድፈ ሃሳብ እንደዘወትር ፀሎት እየደጋገሙ በማኘክ እና ራሳቸውን በፖለቲከኛ ማማ ላይ በማስቀመጥ፤ ከእነሱ ውጭ በአገሪቱ አዋቂ እንደሌለ እና ሁሉም የአገሪቱ ችግር የሚፈታው በእነርሱ እና በእነርሱ ብቻ እንደሆነ በማሰብ በ1960ዎቹ በተከፈቱ ዘፈኖች እስከዛሬ ድረስ እየጨፈሩ ይገኛሉ። እነኝህ ወገኖች በቆሙበት ደርቀው ቀርተዋል ቢባል ማጋነን አይደለም።

የእነርሱ ተከታዮች እና ደቀመዛሙርቶቻቸውም ታላላቆቻቸውም የሰሩትን የከፋት ፖለቲካ እንደ ፖለቲካዊ ጥበብ በመቁጠር ዛሬም ላይ የአገራችን ሁለንተናዊ መስተጋብር በከፍተኛ ደረጃ ሲያውኩት ይስተዋላሉ። የአገራችንን ሁለንተናዊ ህግጋት መጠበቅ እና ማክብር የሚባለውን ነገር ፈጽሞ አያውቁትም። የአገራችንን ሁለንተናዊ ህግጋት መጠበቅ እና ማክብር እንደ ኋላቀርነት ይቆጥሩታል።

በእርግጥ የማርክሲስቶችን ሃሳብ ወስደው አገራቸውን በአወንታዊ መልኩ የቀየሩ በርካቶች ናቸው። ይሁን እንጂ በእኛ አገር የሚገኙ ፖለቲከኛ ነን ባዮች ግን አገራችንን ለማፍረስ ከመጋጋጥ ውጭ ለአገራቸው አንድም ጠብ የሚል ነገር ሲሰሩ አልተስተዋለም።

በእኔ እይታ ለዚህ ሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች ያሉ ይመስለኛል። አንደኛ ከእነ ማርክስ ምንም ሳያላምጡ የወሰዱትን ንድፈ ሃሳብ አብዛኛውን በቅጡ አልተረዱትም። ለምሳሌ ብሔርን በተመለከተ በእነ ማርክስ የፍልስፍና የተሰጠው ትንታኔ እና የእኛ አገር ፖለቲከኞች የተረጎሙበት ሂደት ፈጽሞ የጠራራቀ ነው። እነ ማርክስ አንድ ማህበረ ሰብእ ብሔር ሊባል የሚችለው ስድስት ነገሮችን ሲያሟላ መሆኑን ይናገራሉ። ከስድስቱ አንድ እንኳን ቢጎድል ብሄር ሊባል እንደማይችል ትንታኔ ይሰጣሉ። የእኛ አገር ፖለቲከኞች ደግሞ አንድን ማህበረሰብ ብሔር የሚሉት እነ ማርክስ ከጠቀሷቸው ስድስት ቅድመ ሁኔታዎች አንዱን የሆነውን ቋንቋን ብቻ መሰረት አድርገው ነው። የእኛ አገር ፖለቲከኞች ዋነኛ ችግር የፖለቲካ ፍልስፍና መነሻቸው አገር በቀል ካለመሆኑም ባለፈ ከሌሎች የቀዱትን እንኳን በቅጡ መገንዘብ አለመቻላቸው ነው። በዚህም አሁን ላይ በቆሞ ቀሮች ከ1960ዎቹ እስካሁን ድረስ አገራችንን እያስከፈሏት ያለው ዋጋ ምን እንድሚመስል የአደባባይ ምስጢር ነው።

> **ዝናብ ለሰጠ ጌታ ውሃ ነፈጉት እንዲሉ ኢትዮጵያ ላይ ግፍ እያደረሱ ያሉት እነዚህ ኃይሎች ኢትዮጵያ የምትበላው ሳይኖራት ለምና እና ተበድራ ያስተማረቻቸው ናቸው።**

ሁለተኛው ምክንያት ቆሞ ቀሮቹ የእነ ማርክስን ፍልስፍና ሲቀዱ የፍልስፍናውን ሙሉ ሀሳብ አልወሰዱም። የወሰዱት ለራሳቸው የትግል ስልት ይጠቅመናል ያሏቸውን ንድፈ ሃሳቦች እና በራሳቸው ልክ አጣመው መስፋት የሚችሉትን ብቻ ንድፈ ሃሳቦች ነው። ለምሳሌ የፓርቲ አመሰራት፤ የብሄር ብሄረሰቦች መብት ፣ ፌደራሊዝም ፣ ወዘተ ናቸው።

ሶስተኛ የእኛ ፖለቲከኞች የወሰዱትን ንድፈ ሃሳብ መሬት ላይ መተግባበር አልቻሉም። ለዚህ ዋነኛ ምክንያት ደግሞ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረወው የማርክሲዝምን ጽንሰ ሀሳብ በቅጡ ካለመረዳት የመነጨ ነው።

ዝናብ ለሰጠ ጌታ ውሃ ነፈጉት እንዲሉ ኢትዮጵያ ላይ ግፍ እያደረሱ ያሉት እነዚህ ኃይሎች ኢትዮጵያ የምትበላው ሳይኖራት ለምና እና ተበድራ ያስተማረቻቸው ናቸው። ብድሯን መክፈል ሲገባቸው ጽንፍ ረግጠው ህዝቦቿን እርስ በርስ እያባሉ ይገኛሉ። መማር እንደዚህ ከሆነ ልጆቻችሁን ትምህርት ቤት አትላኩ! ይቅርባችሁ።

ንድፈ ሃሰቦችን በቅጡ ካለመረዳት ጋር ተያይዞ ሁሌም የማልረሳው አንድ የደርግ ባለስልጣን አለ። ስለሱ ትንሽ ልበላችሁ። በአንድ ወቅት ይህ የደርግ ባለስልጣን አብዮተኛ ነን ባይ በመንግስት እያመጹ ያስቸገሩ ተማሪዎችን ለማወያየት በሰፈራችን ከሚገኘው የትምህርት ቤት አዳራሽ ይሰበስባቸዋል። ተማሪዎቹም በማርክሲዝም ፍልስፍና ያበዱ ነበሩ። ለቡና መጠጫ የሚወሩ ቀልዶችን እንኳን ሲያወሩ የማርክሲዝምን ፍልስፍናዎች ቀላቅለው ካላወሩ የሚጨቃንቸው አይነት ናቸው ።

ተማሪዎችን የሰበሰበው የደርጉ ባለስልጣን ደግሞ ከውትድርና ቤት እንዲሁ አፈ ቀላጤ ስለሆነ ባለስልጣን የሆነ እንጂ እብዛም ቀለም የዘለቀው አልነበረም ። ነገር ግን እሱም እንደተማሪዎች የእነ ማርክስን ስም ካልጠራ ህዝብን ማስተዳደር እና አብዮቱን ማስቀጠል የሚችል አይመስለውም ። የሚገርመው ሚስቱም ባሏን እየሰማች ማርክስ እና ሌኒን ማን መሆናቸውን እንኳን ሳታውቅ ማርክስዬን ፤ ከማርክስዬ ይነጥለኝ ፤ የሌኒንዬን ስጋ ያስበላኝ እያለች ስለምትምል የሰፈሩ ሴቶች የማርክስ እናት እያሉ ይጠሯት ነበር ።

ወደ ጀመርኩት የተማሪዎች ስብሰባ ልመልሳችሁ። ስብሰባውም አብዮታዊት ኢትዮጵያ የማርክስ እና ሌኒን ሃሳቦች በመተግበር ወደፊት በሚል መፈክር ተጀመረ። በመፈክሩም ሁሉም ተማሪዎች የግራ እጃቸውን ከፍ አድርገው መፈክሩን አሰሙ። ስብሰባውን የሚመራው ሰው ግን የቀኝ እጁን ነበር ለመፈክር ከፍ ያደረገው። ይህን የተመለከተው አንድ አብዮተኛ ነኝ ባይ ተማሪ ‹‹ጌታዬ! የእነ ማርክስን መፈክር ለማሰማት እንዴት የቀኝ እጅዎት ከፍ ያደርጋሉ !? ይህ የአብዮቱን አካሄድ የሚጻረር ነው» ብሎ አፈጠጠባቸው ። ሰብሳቢውም አለማወቃቸውን ለመደበቅ «በደንብ ጠላትን መቀጥቀጥ የሚችለውን እጅ የማውቀው እኔ ነኝ!» ሲሉ መለሱ።

የሆነው ሆኖ ስብሰባው ተጀመረ፤ ባለስልጣኑ ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ነገሮችን ሳያበዛ ከተናገረ በኋላ ተማሪዎች እንዲናገሩ እድል ሰጠ። አብዮተኛ ተማሪዎችም እየተነሱ የደርጉ ባለስልጣን ሊገነዛባቸው የማይችላቸውን የማርክሲዝም እና የሌሎች ሶሻሊስት ፈላስፋዎችን ንድፈ ሃሳቦች በማንሳት ማርክስ ‘እንዳለው’ ፣ ሌኒን ‘እንዳለው’ እከሌ ‘እንዳለው’ እያሉ ፖለቲካዊ ትንታኔ ሰጡ።

ይህን የተመለከተው የደርጉ ጥራዝ ነጠቅ ባለስልጣን ተማሪዎች ማርክስ፣ ሄንግልስ ፣ሌኒን እንዳለው እያሉ ሲናገሩ አቶ እንዳለው የሚባሉ ሰው እነ ማርክስን ፣ሄንግልስንና ሌኒን የወለዳቸው መስሎት ምን ቢል ጥሩ ነው! ‹‹አብዮቱ እዲፋጠን እና ፍሬ እንዲያፈራ እነኝህን የመሰሉ ብርቅዬ ልጆች የወለዱትን አቶ እዳለውን መሸለም አለብን›› ብሎ አረፈው።

ይህ ፖለቲካን በቅጡ ሳይረዱ መተንተን ዛሬም ላይ እንደከፉ በሽታ ተጣብቶን ይገኛል። አሁን ላይ በእኛ አገር በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች የሚለቀቁ ቧልቶችን እየሰበሰቡ እና እየቃረሙ ራሳቸውን እንደፖለቲካ በመቁጠር አገር የሚያተራምሱ ኃይሎች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።

የሚገርመው እነኝህ አካላት አገር አፍራሽ እንቅስቃሴ እያደረጉ እያለ በአገረ መንግስት ግንባታው ሂደት ራሳቸውን እንደሁነኛ አካል አድርገው መቁጠራቸው ነው።

ወፈፌው ይልቃል አዲሴ ይህን ንግግር እያደረገ እያለ ሁሉም የሰፈራችን ሰዎች ጸጥ እረጭ ብለው እያዳመጡ ነበር ። ነገር ግን ሁሌም ሳይፈቀድለት የሚናገረው አብሿሙ ከንፈ ጉደታ፣ በይልቃል አዲሴ ንግግር ላይ ተደርቦ የይልቃል አዲሴን ንግግር አቋረጠው ።

ባለፈው እንደነገርኳችሁ የሰፈራችን ሰዎች ከንፈ ጉደታን አብሿም ይበሉት እንጂ ከንፈ ጉደታ የእውነት አብሾ መጠጣቱን በእርግጠኝነት መናገር የሚችል ሰው የለም።

የይልቃል አዲሴን ንግግር ያቋረጠው አብሿሙ ከንፈ ጉደታ «ይልቃል አዲሴ ያደረጋቸው ንግግሮች በሙሉ እውነታ አላቸው ። እኔም ከሱ ሃሳብ ላይ የምጨምረው ነገር አለኝ» አለና ንግግሩን እንዲህ ሲል ጀመረ ....‹‹ቆሞ ቀሮች እውቀት የሌላቸው እና ወና ስለሆኑ ለውጥ የሚባል ነገርን አብዝተው ይፈሩታል። ምክንያቱም ለውጥ የአዋቂዎች ነውና ። በነገራችን ላይ ተፈጥሮ በራሷ ለውጥን ስለምትፈልግ ወናነትን አብዝታ ትጠየፋለች ። ስለሆነም ተፈጥሮ የምትፈልገው ከጊዜው ጋር አብሮ የሚዘምንን እና የሚለወጥን ነው ።

አብሿሙ ከንፈ ጉደታ ንግግሩን ቀጠለ ....አዋቂ ማለት ንድፈ ሃሳብን ሸምድዶ የሚያነበንብ አይደለም ። ንድፈ ሃሳብን በተግባር ላይ የሚያውልን እንጂ። ለውጥ ለማምጣት ከተፈለገ ንድፈ ሃቦችን ብቻ ማውራት ተገቢነት የለውም። ለዚያ ነው ፍሬድሪክ ኤንግልስ «ከአንድ ቶን ንድፈ ሃሳብ አንድ ወቂት ተግባር የበለጠ ዋጋ አለው !» ያለው። ይሄን አስተሳሰብ የሚደግፈው ሎይድ ጆንስ «ምንም ነገር ለመስራት ሳይሞክሩ ከተሳካላቸው ይልቅ አንድ ነገር ለማድረግ ሞክረው ያልተሳካላቸው ሰዎች ያለጥርጥር የተሻሉ ናቸው ! »ያለው ።

የቆሞ ቀሮች ዋነኛ መታወቂያ ንደፈ ሃሳብን ከማንም በላይ መናገር መቻላቸው ነው ። ነገር ግን ተግባር ላይ ይህ ነው የተባለ ስራ መስራት የሚችሉ አይደሉም ። ከሚያውቁት ንድፈ ሃሳብ አንድም ነገር በተግባር መሬት ላይ ማውረድ የማይችሉ ናቸው ።

በዓለም ላይ ብሄር የሚባለው ነገር የተመሰረተው ከፊውዳሊዝም መጥፋት እና ከካፒታሊዝም መመስረት ጋር ተያይዞ ነው። ፊውዳሊዝምን አጥፍቶ ካፒታሊዝምን የማዳበር ሂደት በሌላ አነጋገር ህዝቦችን በብሄር የመመስረት ሂደት ነው ። ይሁን እንጂ በምዕራብ አውሮፓ እና በምስራቅ አውሮፓ ብሄር የተመሰረተበት ሁኔታ እጅጉን ይለያያል። በምዕራብ አውሮፓ የተለያዩ ግዛቶች የተለያዩ ብሄሮች ሲሆኑ ፤ በምስራቅ አውሮፓ ግን የተለያዩ ብሄሮች የተለያዩ ግዛቶችን እደፈጠሩ ፖለቲከኞች እና የታሪክ ምሁራን ያስረዳሉ። ይሁን እንጂ አንድ ማህበረ ሰብእ ብሔር ለመባል ማሟላት የሚገባቸውን ነገሮች ያሚሉ ናቸው ።

በእኛ አገር ያሉ ብሄርን የፖለቲካ መጫወቻ ካርድ ያደረጉ ኃይላት ግን በእኛ አገር የተፈጠሩ ብሄሮች የየትኛውን አገር የብሄር አመሰራረት መሰረት ያደረጉ ናቸው ? ተብሎ ቢጠየቁ ለጥያቄው መልስ አይኖራቸውም።›› ብሎ ወደመቀመጫው ተመለሰ ። የሰፈራችን ሰዎች አብሿሙ ከንፈ ጉደታ ንግግር ተገርመው ሞቅ አድርገው አጨበጨቡለት ።

አብሿሙ ከንፈ ጉደታ ንግግሩን ሲጨርስ ወፈፌው ይልቃል አዲሴ ንግግሩን ከአቆመበት ቀጠለ .... እንደእነዚህ አይነት ሰዎችን አድሃሪ (Reactionary) የለውጥ ተቃዋሚ የሚለው የፖለቲካ ቋንቋ በትክክል ይገልጻቸዋል። አድሃሪ የሚለው ቃል ድኅሮት፣ ድኀረ ከተሰኙ የግዕዝ ቋንቋ የተወሰደ ሲሆን፣ ትርጉሙም ወደኋላ መቅረት፣ መጨረሻ መሆን፣ ባሉበት መቆየት ማለት ነው። ማርክሲስቶች አድሃሪ የሚለውን ቃል በአንድ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኝን ማህብረሰብ ጊዜው የሚፈልገውን አይነት እርምጃ ወይም ለውጥ ደግፎ ወደፊት መጓዝ ሲገባው በቀደመ አስተሳሰብ ተቸንክሮ ጊዜው የሚፈልገውን ለውጥ ወደኋላ ጎትቶ ለማስቀረት የሚሞክር ነው። ይህን የሚያደርጉትም በዋናነት ከኋላቸው በገንዘብ እና በሌሎች ጥቅም የሚጋልቧቸውን አለቆቻቸውን ለማስደሰት ሲሉ ነው።

ከቀደመው ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የምናያቸው አብዛኛው በአገራችን ፖለቲካ ተዋናኝ ፖለቲከኞች አገራችን ወደፊት ማራመድ እንዳትችል ትናንትም ዛሬም አንድ አይነት ሃሳብ እንደ ፀሎት መጽሐፍ እየደጋገሙ እዚያው ባሉበት አሉ።

የሚገርመው እነኝህ ግትር ፖለቲከኞች ራሳቸውን የማርክሲስት ፍልስፍናዎችን አንብበው ራሳቸውን በፖለቲካው መድረክ ተዋናይ ያደረጉ ቢሆንም ማርክሲዝም ከሚታወቅባቸው አንዱ እና ዋንኛው የሆነውን ዲያሌክታዊ (DIALECTICS) አስተሳሰብን እናራምዳለን የሚሉ ሜታ ፊዚክስን የሚተቹ ቢሆንም በተግባር ግን ዲያሌክታዊ (DIALECTICS) አስተሳሰብን የረሱ ሜታ ፊዚክስን የሚደግፉ አይነት ሰዎች ናቸው ።

እነኝህ አካላት ራሳቸውን የማርክሲዝም ፍልስፍና ፈትፋች አጉራሽ ያድርጉ እንጂ በተፈጥሮ ያሉ ክስተቶች ሁሉ በማያቋርጥ እንቅስቃሴ ላይ መሆናቸውን እና የማያቋርጥ ለውጥም እንደሚያደርጉ የሚያስተምረውን የማርክሲዝም ፍልስፍና የሆነውን ዲያሌክታዊ (DIALECTICS) አስተሳሰብ በፍጹም የዘነጉ ናቸው። ስለሆነም ለኢትዮጵያ ሰላም እነኝህን ቆሞ ቀሮች አጥበቀን ልንፋለማቸው ይገባል ! ብሎ ንግሩን ሲጨርስ የሰፈራችን ሰዎች በጭብጨባ አጀቡት። ስብሰባውም በዚሁ ተቋጨ።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# የጥላሁን ገሰሰ - ሰበበኛ ዜማዎች

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

1933 ዓ.ም ዕለተ መስቀል። ለአቶ ገሰሰ ቤተሰብ አውደዓመት ሆኖ ብቻ አላለፈም። ከቀኑ መከበር ጋር ለጎጇቸው ሌላ የምሥራችን ይዞ ደረሰ። እማወራዋ ጌጤ ጉሩሙ ወንድ ልጅ ከነቃጭሉ መገላገላቸው በቤቱ ታላቅ ደስታን ፈጥሮ ዋለ። በዓሉ ለመላው ቤተሰብ ዕጥፍ ድርብ ሆኖም ቀኑ በተለየ ስሜት ታሰበ።

እነሆ በዚህ ቀን የተገኘው ፍሬ ለመላው ቤተሰብ የአዲሱ ዓመት ታላቅ ስጦታ ሆኖ ተበረከተ። በትዳር ለተጣመሩት ጥንዶች የዓይን ማረፊያ የሆነው ብላቴና ውሎ አድሮ መጠሪያ ስም ተቸረው። ጥላሁን ገሰሰ ተባለ።

ታዳጊው ጥላሁን አዲስ አበባ ልዩ ስሙ «ጠበንጃ ያዥ» ከተባለ አካባቢ እንደ እኩዮቹ ሆኖ አደገ። ለሚያዩት ሁሉ ልጅነቱ የሚያጓጓ፣ መልኩ የሚያምር፣ ቁመናው የሚማርክ ነበር። ጥላሁንና አዲስ አበባ በአብሮነት እምብዛም አልዘለቁም። አስራ አራተኛ ዓመቱን ባከበረ ማግስት ከተማውን ለቆ ወሊሶ ሊገባ ግድ ሆነ። ወሊሶ አያቱ ይኖራሉ። የጥላሁን ዕጣ ፈንታም በእሳቸው ቤት ሊሆን ተወስኗል። በወቅቱ የአዲስ አበባው ልጅ የመማር ዕድል አልተነፈገም። በአካባቢው ከሚገኝ የራስ ጎበና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፊደል እንዲቆጥር ተመዘገበ።

ጥላሁንና ትምህርት ወሊሶ ላይ በአካል ተገናኙ። የእሱ ፍላጎት ከቀለሙ አልሆነም። ውስጡ ያደረው የሙዚቃ ፍቅር ይታገል፣ ያሸንፈው ያዘ። ይህን ያስተዋሉት አያት ሁኔታውን አልወደዱም። በትምህርቱ ብቻ እንዲያተኩር መከሩ፣ ወተወቱ። የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ ሱዳናዊው ሼድድ ግን ጥላሁንን በተለየ አስተውሎት አይተው ትኩረት ቸሩት። ችሎታውን መዝነውም ወደ ሱዳን ሄዶ ሙዚቃ እንዲያጠና ምክር ለገሱት። ጥላሁን የተባለውን ባያደርግም ከራሱ ስሜት ሲታገል ሲሟገት ቆየ።

አንድ ቀን ግን የጥላሁንን ታሪክ ሊለውጥ የሚችል አጋጣሚ ተከሰተ። በወቅቱ የሀገር ፍቅር ቲያትር ባለሙያ የነበሩ ባለሙያዎች በትምህርት ቤታቸው የሙዚቃ ትዕይንት ለማሳየት ተገኙ። ይህ አጋጣሚ ለጥላሁን መልካም ሆነ። አቶ ኢዩኤል ዮሐንስን ቀረብ ብሎ ያለውን ችሎታና ፍላጎቱን አስረዳቸው። ኢዩኤል ጆሮ ሰጥተው አደመጡት። ፍላጎቱ ካለውም አዲስ አበባ መምጣት እንደሚችል ጠቆሙት። እንግዶቹ ከወሊሶ ከተሸኙ በኋላ ጥላሁን ዕንቅልፍ ይሉት አጣ። ትምህርቱን መማር፣ መከታተል ተሳነው።

አንድ ማለዳ የጥላሁን ልብ ቆርጦ ተነሳ። ማንም ሳያየው ከቤት ጠፍቶ ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ጀመረ። ሁኔታውን ያወቁት አያት ለዘመድ ነግረው ሰላይ ላኩበት። አስራ አምስት ኪሎ ሜትር በእግሩ የተጓዘው ጥላሁን ቱሉ ቦሎ ሲደርስ አዳሩ ከአክስቱ ቤት ሆነ። ማግስቱን ጉዞ ከመቀጠሉ በፊት ግን ተይዞ ወደ ወሊሶ ተመለሰ።

በአስገዳጅነት ተመልሶ ወሊሶ የገባው ጥላሁን በሆነበት ሁሉ አዘነ። እልህና ቁጭት ያዘው። በውስጡ ያደረውን የሙዚቃ ፍቅር ያደናቀፉበትን በሙሉ በክፉ ዓይን አያቸው። በቤቱ ከአንድ ቀን በላይ አልቆየም። በጭነት መኪና ተሳፍሮ ዳግም ጉዞ ጀመረ። አዲስ አበባ ያደረሰው እግሩ ከአገር ፍቅር ቲያትር አገናኘው። የጥላሁን ምኞት ዕውን ሆነ። የውስጡ ፍላጎትና የሙዚቃው ፍቅር ገጠሙለት።

የትናንትናው የወሊሶ ጉብል አዲስ አበባ ላይ ታዋቂ ለመሆን አልዘገየም። እንዳሻው የሚታዘዝለት ድንቅ ጉሮሮው የሰጡትን ግጥምና ዜማ እያንቀረቀረ በርካቶችን ይማርክ ያዘ። ጥላሁን ገሰሰ የዘመኑ ተወዳጅ ድምጻዊ በመሆን ቀዳሚው ሆነ። ጥቂት ጊዜያትን በሀገር ፍቅር የቆየው ጥላሁን ለሌላ ዕድል መታጨቱ አልቀረም። ወደ ክቡር ዘበኛ ተዛውሮ ከአንጋፋና ታዋቂ የሙዚቃ ሰዎች ጎን ተሰለፈ።

የላቀ ዝነኝነቱን ተከትሎ ግን ፈተና አላጣውም። በታኅሣሥ ግርግር ሰሞን ዘፍኖታል የተባለ ዜማ ትርጉም ተሰጥቶት ለእስር ዳረገው። ጥላሁን ገሰሰ ያልነካው የሕይወት ጫፍ፣ ያላነሳው የዓለም እውነታ የለም። ክፋትና ደግነት ፣ ኀዘን ደስታ፣ ሕይወትና ሞት፣ በጥላሁን አንደበት ተዳሰዋል። ገንዘብ፣ ማግኘት ማጣት፣ ሀብትና ድህነት፣ በዜማዎቹ ተነስተዋል።

ስለጥላሁን ገሰሰ ዜማዎች አንድ በአንድ መዘርዘር «ዓባይን በማንኪያ» እንደሚሉት ይሆናል። ጥላሁን ያላነሳቸው የሕይወት እውነታዎች የሉምና አንዱን ከሌላው አወዳድሮ መለየቱ በእጅጉ አስቸጋሪ ነው። በዛሬው ዳሰሳችን ጥላሁን በምክንያትና በሰበብ አዚሟቸዋል ተብለው ከሚታወቁት መካከል እጅግ ጥቂቶቹን ብቻ በወፍ በረር እንዳስሳለን።

**ዋይ! ዋይ! ሲሉ**

ወቅቱ ኢትዮጵያ አገራችን ባጋጠማት ድርቅና ርሀብ የከፋ ችግር ላይ የወደቀችበት ዘመን ነበር። ይህ ጊዜ መላው ዓለም ኢትዮጵያን ርዕስ አድርጎ ስለከፋው ርሀቧ፣ በየዕለቱ እንደ ቅጠል ስለሚረግፈው ምስኪን ሕዝቧ በእጅጉ የሚያወራበት፣ አስከፊው 1967 ዓ.ም። ጥላሁን ገሰሰ እና የሙያ አጋሮቹ በሙያቸው ሕዝቡን ለመድረስ ወደሰሜኑ የአገራችን ክፍል ተጉዘዋል። በስፍራው ሲደርሱ ግን ያዩት እውነት ከተባለውና ከተነገረለት በላይ እጅግ አስከፊ ነበር። ጥላሁን ታዲያ ይህን አይደበቄ ገጽታ በዓይኑ አይቶ፣ በውስጡ አንብቶ ብቻ አላለፈውም። በእጁ የገባውን ግጥም ከዜማ አዋህዶ ለሁሉም «ይድረስልኝ» ሲል በታላቅ ኀዘንና ለቅሶ አንጎራጎረው።

**ዋይ !ዋይ ሲሉ፣**
**የርሀብን ጉንፋን ሲስሉ።**
**እያዘንኩ በዓይኔ አይቼ፣**
**ምን ሳድርግ አለፍኳቸው ትቼ።**
**ወይ እማማ ወይ አባባ፣**
**ብስው ሲሉ ሆዴ ባባ።**
**አስጨነቀኝ ጭንቀታቸው፣**
**ምንስ ሆኜ ምን ሳርጋቸው።**
**ሳያቸው ዓይኔ አፍጥጦ፣**
**ተሰየኝ ልቤ ደንግጦ፣**
**ተብረከረከ ጉልበቴ፣**
**ምን ሳድርግ ዋ! ድህነቴ»**
**በርሀብ ስቃይ ቸነፈር፣**
**ግማሹ ጎኔ ሲቸገር።**
**ክው ብሎ ደርቆ አፋቸው፣**
**የእግዜር ውሀ ሲጠማቸው።**

ጥላሁን በዚህ ዜማው አገር ቤትን ጨምሮ በባህር ማዶ ያሉ ወገኖችን ለእርዳታ አንቅቷል። ወገን ለወገኑ እንዲደርስ፣ አስከፊው የርሀብ ጊዜ እንዲታውስ አድርጓል። ይህ አይረሴ ዜማ ለመላው ኢትዮጵያውያን የክፉ ቀን ማስታወሻ እንደሆነ ዓመታትን ተሻግሯል።

**አልማዝን አይቼ**

ይህ ሙዚቃ በዘመነ ደርግ በነበረው የሥልጣን ሹምሽር ጊዜ የወጣ ዜማ ነበር። ይሁን እንጂ ግጥሙ የያዘው መልዕክት በዘመኑ ለነበሩ ባለሥልጣናት የተመቸ አልነበረም ይባላል። አድማጩም ቢሆን ሦስቱን አልማዞች ከወቅቱ ሦስት የደርግ ባሥልጣናት ጋር አመሳስሎ የራሱን ትርጓሜ መስጠት ይዞ ነበር። ታሪክ እንደሚነግረን ደግሞ እነዚህ ሦስት ሰዎች የኢትዮጵያን የፖለቲካ ታሪክ የመቀየር ገጽታን ተላብሰው ነበር። ሰፊ ትርጉም የተቸራቸው የጥላሁን ገሰሰ ሦስቱ አልማዞች ደግሞ እንዲህ ተዚመዋል።

**አልማዝን አይቼ፣አልማዝን ባያት፣**
**ሦስተኛዋ አልማዝ ብትመጣ ድንገት።**
**ሁለቱን አልማዞች ስላስረሳችኝ ፣**
**ምርጫዬ በምርጫ ተበላሸብኝ።**
**ሦስቱንም አልማዞች ባያቸው ባያቸው፣**
**እቺም፣ያቺም አልማዝ- አልማዝ አልማዝ ናቸው።**
**ሰው የተቸገረው በሌላ ሌላ ነው፣**
**እኔን ያስቸገረኝ የአልማዞች ምርጫ ነው።**

በዚህ ዜማው ላይ ጥላሁን ሦስቱንም አልማዞች በወጉ አይቶ፣ ፈትሾ እንዳላዋጡት ይገልጻል። እንዲህ መሆኑ ደግሞ ምርጫው ወደሌላ እንዲያደላና በመጨረሻ ጥሩወርቅ ከተባለችው ላይ እንዲያርፍ መገደዱን ጭምር ይነግረናል። በወቅቱ ሦስቱ አልማዞች እነማን ናቸው? ጥሩወርቅስ ? ለሚለው ትርጉሙ እንደተባለው ፖለቲካ ፣ አልያም የተለመደው ጸጉር ስንጠቃ ሊሆን ይችላል። ጥላሁን ግን ያለውን ብሎ የውስጡን ስሜት ተነፍሷል።

**ጃፓኗን ወድጄ**

ይህ ሙዚቃ የባህር ማዶን የፍቅር ታሪክ ያስታውሳል። ጥላሁን በዜማው እንደገለጸውም አንድ ኢትዮጵያዊ ሩቅ ምሥራቅ ሳለ ከአንዲት የጃፓን ወጣት ጋር በፍቅር መውደቁን የሚያሳይ ሀቅ አለው። ይህ በዜማ የተገለጸው ስንኝ የአርቲስት ሃምሳ አለቃ ሸዋንዳኝ ወልደየስ እውነተኛ ታሪክ ነው።

ሸዋንዳኝ ለሥራ ሩቅ ምሥራቅ በሄዱበት አጋጣሚ ከአንዲት ጃፓናዊት ጋር ፍቅር ይጀምራሉ። ቆይታቸው አልዘለቀም። ወደመጡበት መመለስ ነበረባቸው። ጊዜያቸውን አጠናቀው ወደ አገርቤት ሲገቡ ግን ያሳለፉት የፍቅር ጊዜ አይረሴ ትዝታ ይጥልባቸዋል። ይህኔ ግጥሙን ጽፈው ዜማውን ከሌሎች ጋር ተባብረው ያዘጋጁታል። ጥላሁን ገሰሰ አሳምሮ እንደሚጫወተው እርግጠኛ ነበሩ። ጥላሁን አላሳፈራቸውም። በሚያምር ተስረቅራቂ ድምጹ ጃፓኗን ወድጄ ሲል እንዲህ አንጎራጎረው።

**ሩቅ ምሥራቅ ሳለሁ ጃፓኗን ወድጄ፣**
**ትዝ ትለኛለች በፍቅሯ ነድጄ።**
**የወይን ዘለላ አበባ የመሰለች፣**
**ውበቷ ግሩም ነው ሲያይዋት ታፈዛለች።**
**ማክበር ልማዷ ነው እናትና አባቷን፣**
**በፍቅር ታንጿል እዩት ሰውነቷን።**
**መች እጠግባት ይሆን ናፍቆቷን ተርቤ፣**



**በሕይወቴ እስካለሁ አትወጣም ከልቤ።**

ጥላሁን ይህን ዜማ ሲጫወተው በውስጡ ናፍቆትን ብቻ አልገለጸበትም። አድማጭን በሀሳብ ከባህር ማዶ አድርሶ ከጃፓኖች ባህልና ወግ ጋር አጨባብጧል። በአገሬው የሙዚቃ ቃና በፍቅር አስምጦ እውነተኛውን ትዝታ አሳይቷል።

**ስትሄድ ስከተላት...**

በጥሉሁን ገሰሰ ድንቅ አንደበት ከተዜሙት መሀል ስትሄድ ስከተላት የሚለው ሙዚቃ አንዱ ነው። ይህ ታሪክም የሃምሳ አለቃ ሸዋንዳኝ ወልደየስን ታሪክ የሚነካ እንደሆነ ይነገራል። አርቲስት ሸዋንዳኝ ከአሁኗ ባለቤታቸው የልጆቻቸው እናት ጋር ከመጋባታቸው በፊት መልካም ይሉት የፍቅር ጊዜን አሳልፈዋል። ሁልጊዜም ትዝታ እየተመላለሰ የሚፈትናቸው ሸዋንዳኝ ታዲያ ጥላሁን ባማረ ድምጹ የልባቸውን ሀሳብ እንዲገልጽላቸው፣ ትዝታውን እያስታወሰ እንዲያዜምላቸው ግጥሙን እነሆ! አሉት። ጥላሁንም እንዲህ ብሎ የልባቸውን ሀሳብ ሞላው።

**ይገርማል! ስትሄድ ስከተላት፣**
**በጎን እያየችኝ፣**
**አማላጅም ብልክ፣**
**ጨክና እምቢ አለችኝ።**
**ተሞኘሁ! ተሞኘሁ፣**
**ደግ ነሽ እያልኩኝ፣**
**ባንቺ ሳይ ስመካ፣**
**አኝጀት የምትቆርጪ፣**
**ጨካኝ ሴት ነሽ ለካ።**

ጥላሁን የሚታይባቸው መድረኮች ሁሌም የደመቁ ሆነው ይውላሉ። የእሱ አድናቂና ወዳጆች በእጅጉ የበረከቱ ናቸውና ፍቅርና አክብሮታቸውን ያሳዩታል። ከዚህ ባሻገር ደግሞ ጥላሁን በትግል ሜዳ አዋጊ ጀግና በመሆን ይታወቃል።

በተገኘባቸው የጦር አውድማዎች ጀግናን ማወደስ፣ ወታደሩን ማጀገን ያውቅበታል። በጦርነት መሀል ተገኝቶ ወደፊት በሉለት ይለይለትን አዚሟል። የጀግና ሰው ክብሩ ዳር ድንበሩ ሲል አነቃቅቷል ዘማች ነኝን ዘፍኗል። ከሁሉም ግን የውትድርና ሕይወትን መሠረት አድርጎ ለጀግኖች ኢትዮጵያውያንና ቤተሰቦቻቸው መታሰቢያነት ያንጎራጎረው ይህ ዜማ ፍጹም አይረሴነትን እንደያዘ እስከዛሬ ቀጥሏል።

**ስአገሬ ስታገል ስድንበሯ**

**ከአገሬ ስታገል ስድንበሯ፣**
**ተኝቻለሁ እኔ ከአፈሯ።**
**ስስድል ታሪኬን ስታወሱ፣**
**ቤተሰቦቼን ግን እንዳትረሱ።**
**እንዳይራቡብኝ አስታውሱልኝ፣**
**እንዳይራቆቱ አልብሱልኝ።**
**እንዳይቸገሩብኝ ልጆቼ፣**
**አደራ ብያለሁ ወገኖቼ።**

ጥላሁን ገሰሰና የአገር ፍቅር ፈጽሞ አይነጣጠሉም። ጥላሁን ተፈጥሮው ሆነና ሆደ ቡቡ የሚሉት ዓይነት ነው። ስለአገሩ ካሉት ደግሞ የዕንባው ነገር ይለያል። አገሩን እያነሳ አልቅሶ ታዳሚውን ጭምር ያስለቀሰባቸው አጋጣሚዎች በርካታ ናቸው። ከጥላሁን የዕንባ ዜማዎች መካከል ስለነፃነት ያዜመው ስንኝ እንዲህ ይታወሳል።

**ነፃነት**

**እንኳንስ ደስታዬን -የሰውነቴን ሰው፣**
**እንኳን ነፃነቴን- ጸጋ ክብሬን ትቼው።**
**በእናት አገር ምድር - በሚያውቀኝ፣**
**በማውቀው ፣**
**ስቃይ መከራዬን ካንቺው ዘንድ ያድርገው።**

ጥላሁን ገሰሰ በአማርኛ ከተጫወታቸው እጅግ በርካታ ዜማዎች በተጨማሪ በኦሮምኛና ሱዳንኛ ዘፈኖቹ ጭምር ይታወቃል። ሁሉም በሚባል መልኩም ዜማዎቹ ተወዳጅና ተደማጭ እንደሆኑ ዓመታትን ተሻግረዋል።

የኢትዮጵያ የሙዚቃ ንጉሥ የሚባለው ጥላሁን በሕይወት ዘመኑ በርካታ ውጣውረዶችን አልፏል። በ1985 ዓ.ም በአንገቱ ላይ የደረሰበትን ጉዳት ጨምሮ በስኳር ህመሙ መነሻ ባጋጠመው ህመም አንድ እግሩን እስከመቆረጥ ደርሷል። እንዲያም ሆኖ ከመድረክ የመለየት ፍላጎት አልነበረውም። ሁሌም ቢሆን ሙያውን ማሳየት፣ ለአድናቂዎቹም ፍቅሩን መግለጽ ይሻል። ጥላሁን በሕይወት ካለፈ በኋላ በአገር እንዲታወስና በሙያው እንዳይረሳ እንዲህ ሲል አዚሞ ነበር።

**ትንፋሼ ተቀርፃ**

**ትንፋሼ ተቀርፃ ይቀመጥ ማልቀሻ፣**
**ይህ ነው የሞትኩኝለት የእኔ ማስታወሻ።**
**ውበቷን ሳሞግስ -የስምስም አገሬን፣**
**ማንም አይዘነጋው በጨኸት መኖሬን።**
**ዜማ እንጉርጉሮዬን የግሌን ቅላጼ፣**
**ተቀርፃ ይቀመጥ ታሪኬ ነው ድምጼ።**
**ድምጻዊ ዘፋኝ ነኝ አንጎራጉራለሁ፣**
**ይኸው ነው ታሪኬ ሌላ ምን አውቃለሁ።**

ጥላሁን ገሰሰ ዕድሜውን ሙሉ ለአገሩ ባበረከተው የኪነጥበብ ሥራዎች ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት አግኝቷል። እንዲሁም ከኢትዮጵያ የኪነጥበብና የብዙኃን መገናኛ ሽልማት ድርጅት የሙሉ ዘመን ተሸላሚ ለመሆን ችሏል። ጥላሁን ገሰሰ ከሚወዳት አገሩ፣ ከሚያከብረው መድረክና በፍቅር ከተንበረከከለት ሙያው በድንገት የተለየው ሚያዝያ 11 ቀን 2001 ዓ.ም በዕለተ ፋሲካ ሌሊት ነበር።

«ከመሞት አልድንም፣ መለያየት ሞት ነው» ባለበት አንደበቱ በአይቀሬው ሞት በተነጠቀ ጊዜ የብዙኃን አድናቂዎቹ ልብ በታላቅ ኀዘን ተሰብሯል። ጥላሁን ከመሞቱ አስቀድሞ አገሩን ሊያመሰግንበት የነበረው ድንቅ ዜማ በሥርዓተ ቀብሩ ላይ በሙያ አጋሮቹ ተቀንቅኗል። እነሆ! በጥቂቱ።

**ቆሜ ልመርቅሽ**

**ቆሜ ልመርቅሽ - ተቀበይኝ እማ**
**ሕይወትን መርቀሽ -ሰጥተሽኝ እኔማ**
**ይህ ቀረኝ የምለው- የሚቆጨኝ በዓለም**
**ኢትዮጵያ ዕድሜ ላንቺ- ያላየሁት የለም**
**አንገትሽ ራስሽን - ችሎ ልየውና**
**ማግስቱን ይውሰደኝ- አስር ሞት ይምጣና**

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ትኩረት ለኦቲዝም !

**ሰሳማዊት ውቤ**

‹‹ገና የሁለት ዓመት ዕድሜ እያለ ነበር የትኩረት ማጣት ችግር የተስተዋለበት፡፡ ትኩረቱን ወደ እኔ እንዲያደርግም ብዙ ጥሬያለሁ፡፡ ግን በፍፁም ዓይኔንም፤ ፊቴንም ለማየት አልቻለም›› ይላሉ የኦቲዝም ታማሚ ልጅ ያላቸው ወይዘሮ የሺወርቅ አጥላው፡፡

ዛሬ ላይ ሃያ ዓመቱን የደፈነው የያኔው ጨቅላ ልጃቸው እንደ ሕፃን አልቅሶ እናቱን ጡትም ሆነ ጡጦ ጠይቋቸው አያውቅም፡፡ ጭራሽ እናቱ እንደሆኑ ያለመለየቱም ነገር ግራ ሲያጋባቸው ቆይቷል፡፡ በተለይ ሁለት ዓመቱ አካባቢ ዓይኖቹ እንደቦዘዙ ከእሳቸው በስተጀርባ ባለ ቀይ ነገር ላይ ተተክለው ለረጅም ጊዜ መቆየታቸውን ያስተውሉ ነበር፡፡

‹‹እውነት ለመናገር ልጄ ቀዩን ነገር ራሱ ለማየቱ እርግጠኛ አልነበርኩም›› ይላሉ ወይዘሮ የሺወርቅ፡፡ ቀዩን ነገር ስለማየቱን ለማረጋገጥ ፊቱ ላይ ምንም ስሜት ይታይ እንዳልነበርም ይገልፃሉ፡፡ ብዙ ነገሮች ቢያንቃጭሉለት፣ ሲያንኳኩ ቢውሉ እንቅስቃሴው አለመለወጡና ጆሮው መስማቱን ሁሉ ያጠራጥሯቸው እንደነበርም ያስታውሳሉ፡፡

ወይዘሮ የሺወርቅ ስለልጃቸው መግለፅ ሲጀምሩ እንባ አቆርዝዘው የነበሩ ዓይኖቻቸው ዘለላውን ዱብ ዱብ ያደርጋሉ፡፡ ሕፃን ልጃቸውን ወደ ሆስፒታል የወሰዱትም እነዚህን ሁሉ ምልክት ካዩበት በኋላ ነበር፡፡

‹‹ይህ የበርካታ በኦቲዝም የተጠቁ ልጆች እናቶች ገጠመኝ ነው›› ይላሉ በአርሲ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የአእምሮ ጤና ባለሙያና የኦቲዝም ሀኪም የሆኑት ሲስተር ካሰች ለታ፡፡ ሲስተር ካሰች እንደሚሉት፣ ኦቲዝም አንድ በሽታ አይደለም፡፡ ይልቁንም ኦቲዝም የሚለው ስያሜ ራሱ ከአእምሮ እድገት መዛባት ብሎም ሰው ከመለየት ጋር የተያያዘ የአእምሮ ጤና ችግር ያለባቸው ሰዎች የሚጠሩበት የጋራ ስያሜ ነው፡፡ ሰዎች በአብዛኛው ውስጣዊውንና ውጫዊውን ወይም ደግሞ የራሳቸውንና ከሌሎች ጋር ያላቸውን ዓለም አመጣጥነው ይኖራሉ፡፡ በኦቲዝም የተጠቁ ሰዎች ግን አኗኗራቸው እንደዚህ አይደለም፡፡

በሕክምናው ሙያ እንደተጠናው የኦቲዝም ህመምተኞች በአብዛኛው በራሳቸው ውስጥ በፈጠሩት ምናባዊ ዓለም ብቻ ይሽከረከራሉ፡፡ በእኔነት ወይም በራሳቸው ዛቢያ ውስጥ እየተሽከረከሩም ነው የሚኖሩት፡፡ እነርሱ ልክ ባዶ ቤት ወይም ትንሽ ሳጥን ውስጥ ተቆልፎባቸው ለብቻቸው የተቀመጡ ያህል ነው የሚሰማቸው፡፡ ሁሌም በራሳቸው ጭንቅላት ውስጥ ብቻ ነው ያሉት፡፡ ከዚህም የተነሳ ለሰው ግራ የሚያጋባና ለመረዳት አስቸጋሪ የሆነ የባህርይ፣ የቋንቋና የማህበራዊ ግንኙነት ሁኔታዎች አብዝተው ይስተዋሉባቸዋል፡፡

ከንግግር ውጪ በሆኑ የመግባቢያ ችግሮችም የተጋለጡ ናቸው፡፡ በሚያስገርም፤በሚያስደነግጥና በሚያሳስብ ሁኔታ ይወድቃሉ፡፡ የገዛ ወላጆቻቸውንም ሆነ የሌሎች የቤተሰቡን አባለት ብሎም እንግዶችን ዓይን በፍፁም ላይመለከቱ ይችላሉ፡፡ እርስ በእርስ የመተያየት የግንኙነት መስተጋብር በኦቲዝም ለተጠቁ ልጆች አይሠራም ወይም አይታወቅም፡፡

ሲስተር ካሰች እንደሚሉት ብዙ ወላጆች የኦቲዝም ተጠቂ ልጆቻቸው ፊታቸውን ለማየት እንደማይደፍሩ ሲገልፁ መስማታቸውንና ሆኖም የአባትና እናታቸውን ፊት ገጽታ ለማየት የማይደፍሩት ፈርተው እንዳልሆነ ያስረዳሉ፡፡ ፊታቸውን የማያዩት በኦቲዝም የተጎዳው አእምሯቸው ስለወላጆቻቸው በነሱ አጠገብ መኖር ምንም ዓይነት መረጃ ስለማይሰጣቸው እንደሆነም ያብራራሉ፡፡ ይሁንና ሁሉም በበሽታው የተጠቁ



ሲስተር ካሰች ለታ

ልጆች አንድ ዓይነት ባህርይና ምልክት እንደማያሳዩ ይጠቁማሉ፡፡

የተወሰኑት በበሽታው የተጠቁ ልጆች ፍላጎት የሚያሳዩባቸው ውሱን ጉዳዮች ብቻ ይኖራሉ፡፡ ለምሳሌ የሆነ ቀለምን ውስጣቸው ስለሚረዳው ለዛ ቀለም ተመሳሳይና ተደጋጋሚ ትኩረት የሚሰጡበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ ቀሪዎቹ ደግሞ ሌላ ዓይነት ነገር ላይ ትኩረት ሊያደርጉ ወይም ምንም የትኩረት ስሜት ላይኖራቸው ይችላል፡፡ አንዳንዶቹ ራሳቸውን መግለጽም ሆነ የሌሎችን ሁኔታ መረዳት ይከብዳቸዋል፡፡

በምልክትም ሆነ በንግግር መግባባትም ያስቸግራቸዋል፡፡ ተደጋጋሚ የሆነ ትርጉም የማይሰጥም ሆነ የማይገባ ቃላት ወይም ድምጽ ወይም እንቅስቃሴ ይደጋግማሉ፡፡ ውስን ቢሆንም ስሜታዊነትም ሊታይባቸው ይችላል፡፡ በጥቅሉ በኦቲዝም የተጠቁ ልጆች (ሰዎች) ለምንም ዓይነት ነገር ምንም ዓይነት መረዳትና ምላሽ ላይሰጡ ወይም ከሚገባው በላይ ምላሽ ሊሰጡ የሚችሉበት ሁኔታ እንዳለም ነው ሲስተር ካሰች የሚገልፁት፡፡

ኦቲዝም አንድ ዓይነት ብቻ አይደለም የሚባለውም ከዚሁ ተጠቂዎቹ ከሚያሳዩት ባህርይ ወይም ምልክት በመነሳት እንደሆነ ሲስተር ካሰች ያስረዳሉ፡፡ ኦቲዝም አምስት የተለያዩ መጠሪያ ዓይነቶች እንደነበሩትም ገልፀው፤ ነገር ግን ከጊዜ በኋላ አምስቱም በአንድነት ‹‹ኦቲዝም ስፔክትረም ዲስኦርደር›› ተብሎ መጠራት እንደጀመረ ይጠቅሳሉ፡፡

ከነዚህ ውስጥ አንዱ የሆነው ‹‹ሪት ሲንድሮም›› በሴቶች ላይ ብቻ የሚታይ ሲሆን በጣም ታዋቂው ምልክት ከወሊድ በኋላ ባሉት የመጀመሪያዎቹ አምስት ወሮች ውስጥ መደበኛ እድገት በኋላ የሕፃኑ ጭንቅላት ከጊዜ ወደ ጊዜ ስፋቱ (ዲያሜትር) መቀነስ ነው፡፡

ስለምልክቶቹም ሲስተር ካሰች ሲያብራሩ እነዚህ ሕፃናት እጆቻቸውን ለተወሰነ ዓላማ መጠቀም ያቆማሉ፡፡ እንዲሁም የተለመደውን የእጅ እንቅስቃሴዎችን ይተዋሉ፡፡ የንግግርና በእግር መጓዝ ችግሮችም ይስተዋልባቸዋል፡፡

በመሆኑም ሁሉም ዓይነት ችግር ያለባቸውን የኦቲዝም ተጠቂዎችን የማገዙ ተግባር የዘርፉ ሞያተኞች ተግባር ብቻ ሳይሆን የእያንዳንዱ ኅብረተሰብ ክፍል ኃላፊነትም ጭምር እንደሆነና ስለ ኦቲዝም ሁሌም መወራት እንዳለበትና ለጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶ መሠራት እንዳለበት ሲስተር ካሰች ያሳስባሉ፡፡

# ዓለም አቀፍ

## የናይጄሪያ ባለሥልጣናት ‘በኢንዶሚ ኑድልስ‘ ሳይ ምርመራ ማድረግ ጀመሩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ናይጀሪያ የምግብ እና መድኃኒት ቁጥጥር መሥሪያ ቤት በካንሰር የመያዝ ዕድልን የሚያስከትል ንጥረ ነገር ይዟል በተባለው የኑድልስ ምርት ላይ ምርመራ እያደረጉ መሆኑን ቢቢሲ ዘግቧል፡፡

ተቆጣጣሪው መሥሪያ ቤት “ኢንዶሚ” በተባለው የኑድልስ ምርት ላይ የቀረበውን ጥያቄ ለማጣራት «ፈጣን እርምጃ» እየወሰደ መሆኑን አሳውቋል፡፡

የምግብ እና መድኃኒት ቁጥጥር መሥሪያ ቤቱ ባወጣው መግለጫ ላይ እንዳለው «የኢንዶሚ ኑድልስ ምርት የተለያዩ ናሙናዎችን እና ቅመማ ቅመሞቹን በመውሰድ» ኢቲሊን ኦክሳይድ የተባለው ለጤና ጎጂ ንጥረ ነገር እንዳለበት ምርመራ እያደረገ ነው፡፡



በተጨማሪም ከተጠቀሰው የኑድልስ ምርት በተጨማሪ ምርመራው በናይጄሪያ ገበያ ውስጥ በሚገኙ በሌሎችም ተመሳሳይ ምርቶች ላይ ምርመራ እንደሚያደርግ አሳውቋል፡፡

የምግብ እና መድኃኒት ቁጥጥር መሥሪያ ቤት ይህንን ምርመራ ማድረግ የጀመረው ባለፈው ሳምንት ማሌዢያ እና ታይዋን ውስጥ «ልዩ የዶሮ ጣዕም» አለው የተባለው ምርት ናሙናዎች ላይ አደገኛው ንጥረ ነገር ተግኝቷል ከተባለ በኋላ ነው፡፡

በሁለቱ የእስያ አገራት ውስጥ በተጠቀሰው የኑድልስ ምርት ላይ ለጤና ጎጂ የሆነው ንጥረ ነገር በመገኘቱ ምርቶቹ ከገበያ እንዲሰበሰቡ ተደርጓል፡፡

ኢንዶሚ የተባለውን ኑድልስ የሚያመርተው የኢንዶኔዢያው ግዙፍ የምግብ አምራች ተቋም የሆነው ኢንዶፉድስ ግን የምግብ ምርቱ ጤናማ መሆኑን በመግለጽ እየተከራከረ ነው፡፡

የናይጀሪያ የምግብ እና መድኃኒት ቁጥጥር መሥሪያ ቤት ጨምሮም የተጠቀሰው የምግብ ምርት ዓይነት በአገሪቱ ውስጥ እንዲሸጥ ያልተመዘገበ እና ፈቃድ ያላገኘ መሆኑን ገልጿል፡፡

ስለዚህም የኢንዶሚ ኑድልስ ምርት ወደ ናይጀሪያ የሚገባባቸው የወደብ ባለሥልጣናት ምርቱ እንዲገባ እንዳይፈቅዱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል፡፡

ተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤቱ ክስ ከቀረበበት ከኑድልስ ምርት ጋር በተያያዘ «በፋብሪካው እና ለገበያ በሚቀርብበት ሁኔታ ጭምር ምርመራ» በማካሄድ ውጤቱን ይፋ እንደሚያደርግ ገልጿል፡፡

ፓስታ በሚመስለው ኑድልስ በመባል በሚታወቀው የምግብ ምርት ውስጥ ተገኘ የተባለው ኢቲሊን ኦክሳይድ ንጥረ ነገር በምግብ አምራች ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

ይህ ንጥረ ነገር ከተገቢው መጠን በላይ በምርቶች ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ በሰዎች ጤና ላይ አደጋን ያስከትላል፡፡ ዓለም አቀፉ የካንሰር ጥናት ተቋም እንደሚለው ኢቲሊን ኦክሳይድ ካንሰር አምጪ ከሆኑ ንጥረ ነገሮች መካከል የሚመደብ ነው፡፡

## በአውስትራሊያ የጠፋው ዓሣ አስጋሪ በአዞ ሆድ ውስጥ ተገኘ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አውስትራሊያ ውስጥ አንድ ዓሣ አስጋሪ ከጠፋ ከቀናት በኋላ አስከሬኑ በአዞ ሆድ ውስጥ ተገኝቷል፡፡

ይህ ግለሰብ ከጓደኞቹ ጋር ዓሣ ሲያሰግር ከቆየ በኋላ ጠፍቶ እንደነበር ቢቢሲ ዘግቧል፡፡

ኬቨን ዳርሞዲ የተባለው ይህ ግለሰብ ለመጨረሻ ጊዜ የታየው በኩዊንስላንድ ግዛት ባለፈው ቅዳሜ ኬኔዲስ ቤንድ የአዞዎች ማዕከል ውስጥ ነበር፡፡

በአካባቢው ለሁለት ቀናት ሙሉ ፍለጋ ከተደረገ በኋላ ፖሊስ ሁለት አዞዎችን በጥንቃቄ ራሳቸውን እንዲስቱ በማድረግ ያለ ስቃይ ከተገደሉ በኋላ ሆዳቸው ሲበረበር በአንዱ አዞ ውስጥ የጠፋው ግለሰብ አስከሬን ተገኝቷል፡፡

ይህ በአዞው ውስጥ የተገኘው አስከሬን በትክክል የጠፋው ኬቨን ዳርሞዲ ስለመሆኑ በሳይንሳዊ መንገድ መረጋገጥ ቢኖርበትም፣ ፖሊስ ግን የ65 ዓመቱ ዓሣ አስጋሪ አስከሬን ስለመሆኑ ጥርጣሬ እንደሌለው አመላክቷል፡፡

ኬቨን ዳርሞዲ የዓመታት ልምድ ያለው ዓሣ አስጋሪ እንደነበረ ባልንጀሮቹ ይመሰክራሉ፡፡ በኬፕ ዮርክ አካባቢም በማኅበረሰቡ ዘንድ በደንብ የሚታወቅ ሰው ነበር፡፡

ሁለቱ አዞዎች ቁመታቸው 4.1 ሜትር እና 2.8 ሜትር ሲሆን እንዲገደሉ የተደረገው ሰኞ ዕለት ነው፡፡

አዞዎቹ የተገኙት ግን ሟች ለመጨረሻ ጊዜ ከታየበት ሥፍራ 1.5 ኪሎ ሜትር ርቆ ባለ ቦታ ነው፡፡

ከሁለቱ አዞዎች ውስጥ የሰው አስከሬን የተገኘው በአንደኛው አዞ ሆድ ውስጥ ብቻ ነው፡፡

ነገር ግን የዱር አራዊትና እንስሳት ባለሙያዎች ሌላኛውም አዞ በሰውየው ግድያ ውስጥ እጁ ሳይኖርበት አይቀርም ነው የሚሉት፡፡

በአካባቢው የነበሩት የሟች ባልደረቦች ዳርሞዲ ጥቃት ሲደርስበት እንዳልተመለከቱ ተናግረዋል፡፡ ነገር ግን የጩኸት ድምጽ መስማታቸውን እና ከዚያ በኋላ ደግሞ የውሃ



መንቦራጨቅ ድምጽ መከተሉን መስክረዋል፡፡


«ድምጹን ወደሰማሁበት ቦታ ሮጬ ሄድኩ፤ ነገር ግን እርሱ ከዚያ ቦታ ስለመኖሩም ምንም ምልክት አልነበረም፡፡ ቱታው ብቻ እዚያ ስፍራ ተቀምጦ ነበር» ብሏል ጆን ፔይቲ የተባለ የሟች ወዳጅ ለኬፕዮርክ ዊክሊ ጋዜጣ፡፡

አዞዎች በአስውስራሊያ ሰሜናዊ ክፍል በቁጥር በርካታ ናቸው፡፡

ነገር ግን ሰዎች ላይ ጥቃት መሰንዘራቸው ብዙም የተለመደ አይደለም፡፡ ዳርሞዲ በአዞ ተበልቶ ሲሞት ከአውሮፓውያኑ 1985 ወዲህ 13ኛው ሰው ነው፡፡

በ2017 አንዲት ጎልማሳ ሴት በፖርት ዳግላስ አካባቢ ጠፍታ የቀረች ሲሆን፣ ምናልባት በአዞ እንደተበላች ይጠረጠራል፡፡

# ስፖርት



# ኢትዮጵያ በዓለም ስፔሻል ኦሊምፒክ ትሳተፋለች

አለማየሁ ግዛው

የዓለም ስፔሻል ኦሊምፒክ ለተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች የውድድር እድልን በመፍጠር አካታች ስፖርታዊ ውድድር የሚደረግበት ትልቅ መድረክ ነው። የዘንድሮው ስፔሻል ኦሊምፒክ ውድድር በጀርመን በርሊን ከሰኔ 9-17/2015 ዓ.ም ይካሄዳል። በውድድሩ በሺዎች የሚቆጠሩ የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ስፖርተኞች ይሳተፋሉ።

ኢትዮጵያም በውድድሩ እንደምትሳተፍ የስፔሻል ኦሊምፒክ ኮሚቴ አስታውቋል። የኢትዮጵያ ስፔሻል ኦሊምፒክ ብሄራዊ ቡድንም በጥር ወር 2015 ዓ.ም በተካሄደው አገር አቀፍ ውድድር መመረጡ ታውቋል። ኢትዮጵያ የምትሳተፈው በአትሌቲክስ ስፖርት ሲሆን ከነዚህም ውስጥ አጭር ርቀት፣ሪሌይ (ዱላ ቅብብል)፣ ርዝመት ዝላይ ዋንኞቹ ናቸው።

ብሄራዊ ቡድኑ ዝግጅቱን ከግንቦት ወር አጋማሽ ጀምሮ ያደርጋል። በተቻለ አቅም ውጤት እንዲመዘገብ የሚያስችል ዝግጅት በመደረግ ላይም ይገኛል። ለዚህም አራት በውድድሩ በቀጥታ የሚሳተፉና አራት ተጠባባቂን ጨምሮ ቡድኑ በአጠቃላይ ስምንት አትሌቶችን አቅፎ ዝግጅቱን የሚያደርግ ይሆናል።

ብሄራዊ ቡድኑ ጠቅልሎ በአንድ ቦታ ስልጠና ያልጀመረው ባለበት የፋይናንስ እጥረት ምክንያት ሲሆን በፊት የሚደግፉት አካላትም በመዳከማቸው




ድጋፎች እንዳጠሩ ታውቋል። ስፖርተኞቹ ባሉበት ቦታ በሳምንት ሁለት ጊዜ ልምምዶችን እንዲያደርጉ ስፖርቱን የሚመራው አካል ሁኔታዎችን እያመቻቸ ሲሆን ከደጋፊ አካላት በሚያገኙት ድጋፎች ውድድሩ ቀረብ ሲል ለአስራ አምስት ቀናት በውድድሩ ህጎችና መሰረታዊ ነገሮች ጠንከር ያሉ ስልጠናዎችን በመስጠት ዝግጅት እንደሚያደርግ ተጠቁሟል።

የኢትዮጵያ ስፔሻል ኦሊምፒክ ኮሚቴ ናሽናል ዳይሬክተር አቶ ገበየሁ ሙሉጌታ፤ ኮሚቴው የሚሰራው የአእምሮ እድገት ውስንነት ባለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ እንደሆነ ይናገራሉ። ብዙ ጊዜ በስፖርቱም ይሁን በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ልዩ ድጋፍ የሚፈልጉ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እንደማይሆኑ የጠቆሙት አቶ ገበየሁ፣ በማህበረሰቡ ዘንድ የግንዛቤ እጥረት ስለሚኖር ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ አደባባይ የማያወጡበት ሁኔታዎች እንዳሉ ያስቀምጣሉ።

በዋናነት የኢትዮጵያ ስፔሻል ኦሊምፒክ ኮሚቴ፣ የአፍሪካ እና የዓለም ስፔሻል ኦሊምፒክ ኮሚቴ ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ ያሉት ተደብቀው ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ወደ አደባባይ ወጥተው እንደማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል እኩል ተጠቃሚና በስፖርቱም እራሳቸውን መዝናናትና አገራቸውን በመወከል ውጤት ማምጣት እንዲችሉ ለማድረግ መሆኑን ዳይሬክተሩ ያስረዳሉ።

ከዚህ አንጻር ኮሚቴው በርካታ ስራዎችን አቅዶ ወደ ስራ የገባ ሲሆን፣ ከዚህ ቀደም አቡዳቢ ላይ በተደረገ ውድድር ብሄራዊ ቡድኑ ውጤት አስመዝግቦ መመለስ እንደቻለ ይታወሳል። እንደ አቶ ገበየሁ ገለፃ፣ ዘንድሮ በጀርመን በሚደረገው ውድድር ኢትዮጵያን የሚወክለው ብሄራው ቡድን ካለው ልምድ ጋር ጥሩ ዝግጅት በማድረግ ውጤት ለማስመዝገብ ጥረት እየተደረገ ነው። ስፖርተኞቹ ልዩ ትኩረትና እንክብካቤ ስለሚያስፈልጋቸው የሚያሳዩትን ባህሪ ተቋቁሞ የሚያሰለጥን ባለሙያ ግን አስፈላጊ ነው። በዚህ ዘርፍ እንደ አገር የሰለጠነ ባለሙያ እጥረት ቢኖርም፤ ያሉት አሰልጣኞች በዚህ ሂደት ውስጥ ያለፉና ቤተሰብ በመሆናቸው ልጆቹን በመንከባከብ ከፍተኛ ልምድን ያካበቱ ናቸው። በመሆኑም በሚሰጣቸው እንክብካቤና ስልጠና ረገድ የሚገጥም ችግር ይኖራል ተብሎ አይጠበቅም።

እንደ ዳይሬክተሩ ማብራሪያ ኮሚቴው ከተመሰረተ የሶስት ዓመታት እድሜ ብቻ ያለው ሲሆን ትኩረት አድርጎ የሚሰራው የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች ከቤት ወጥተው እንደሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው። ኮሚቴው አሁንም በየቤቱ ብዙ ተደብቀው የሚገኙና ልጆችን ያካተተ የተለያየ ፌስቲቫልና ፎረሞችን ለማድረግ አብሮት የሚሰሩ አካላትን ይፈልጋል። የሚታዩ ስራዎችን እየሰራ ወላጆች ልጆቻቸውን እንዲያወጡም ያበረታታል። የህብረተሰቡ ግንዛቤ ሲቀየርና ልጆቹን ሲያወጣ በቂ ባለሙያ ማፍራት ላይ ይሰራል።

በአእምሮ እድገት ውስንነት በዓለም ከ25 በላይ ስፖርቶች ውድድር ይካሄድባቸዋል። ኢትዮጵያም በነዚህ መድረኮች በውስን ስፖርትና ስፖርተኞች ትሳተፋለች። በቀጣይ ግን ቢያንስ በሶስትና አራት የስፖርት አይነቶች ለመሳተፍ በእቅድ እየተሰራ ነው። የተሳትፎ መጠን እና ተሳታፊን ለማብዛት በቂና የሰለጠነ ባለሙያን ማፍራት ግን የግድ ይላል። በባለሙያ ላይ ያለውን ክፍተት ለመሙላትም በሐምሌ 2015 ዓ.ም ከሁሉም ክልል ለተወጣጡ ባለሙያዎች ትልቅ የሆነ የአሰልጣኞች ስልጠናን በአዲስ አበባ ለመስጠት ታቅዷል። ለስልጠናው ከአፍሪካ ዳይሬክተሮች ጋር ግንኙነት በመደረግም ፍቃደኝነት ታይቷል።

አቶ ገበየሁ አሁን ከተመረጡት ስፖርተኞች ውስጥ ልምድ ያላቸው እና ባሉበት ቦታ ጠንካራ ልምምድ በማድረግ ላይ የሚገኙ በመሆናቸው በጀርመኑ ውድድር ውጤት እንደሚጠብቁ ይናገራሉ። ‹‹አትሌቲክሱ በሌላውም የህብረተሰብ ክፍል ውጤት ስለሚመጣበት ጠንክረን ከሰራን ውጤት የማናመጣበት ነገር አይኖርም›› ሲሉም ተናግረዋል።


## የሥራ ቅጥር ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ከዚህ በታች ባለው የሥራ መደብ ላይ ሠራተኞች አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል።

**በመሆኑም መስፈርቱን የምታሟሉ ተወዳዳሪዎች ከታች በተገለፀው አድራሻ ቀንና ሰዓት መጥታችሁ እንድትመዘገቡ እናሳውቃለን።**

| ተራ ቁጥር | የስራ መደብ መጠሪያ | ተፈላጊ የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ | ደረጃ | ደመወዝ | ተፈላጊ የሰው ሀይል ብዛት | የቅጥር ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የእንክብካቤ አገልግሎት ሠራተኛ(ሞግዚት) | በቀድሞ 12ኛ/10ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቀና 4 ዓመት የሥራ ልምድ ወይም የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤት 10+1 ያጠናቀቀ እና 2 ዓመት የሥራ ልምድ ወይም የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤት ዲፕሎማና 0 ዓመት የሥራ ልምድ ወይም የሙያ ምዘና ወስዶ የደረጃ II የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው 0 ዓመት የሥራ ልምድ | VI | 2,799 | 2 | በቋሚነት |
| 2. | የጤና ባለሙያ | በነርስ ሙያ የኮሌጅ ዲፕሎማ 0 ዓመት የሥራ ልምድ | IX | 4,609 | 1 | በኮንትራት |

**የምዝገባ ቦታ፡-** መገናኛ 3ኤም ህንፃ ትራንስፖርት ቢሮ 6ኛ ፎቅ በሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የሥራ ክፍል

**የምዝገባ ቀንና ሰዓት፡-** ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ5 ተከታታይ የሥራ ቀናት ጠዋት ከ2፡30-6፡30 ከሰዓት በኋላ ከ7፡30-1፡00 ሰዓት ድረስ፤

**ስምዝገባ የሚያስፈልጉ፡-** ኦርጅናል የትምህርት መረጃ ከማይመለስ ፎቶ ኮፒ ጋር ይዘው መምጣት ይጠበቅባችኋል፡፡

**ማሳሰቢያ፡**

* ሴት አመልካቾች ይበረታታሉ፡፡

* ፈተና የሚሰጥበት ቀን በውስጥ ማስታወቂያ ወይም በስልክ ይገለፃል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ቢሮ**